በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ
ቅዱሳን በሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ዋና ክፍል በመጽሔት
ዝግጅት ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዐተ እምነትና
ክርስቲያናዊ ትውፊትን ጠብቆ የሚወጣ

መዝሙረ ተዋሕዶ

መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን
ለደመራ በዓላችን የምንለጠው ትኩረት
ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል . . . . . ፪
በረከተ ወንጌል
ሊከተለኝ የሚወድ መስቀሌን ተሸክሞ
ይከተለኝ . . . . . ፫
ተለእኮ ዘሣልሳይ ሺሕ
ከደመራው በፊት የሚለኮሱት
ደመራዎች . . . . . ፭
ትምህርተ ሃይማኖት
በፍጽም ወበእንግድዓ በአፃብዕ ወበመዝራዕት
ትእምርተ መስቀል ናንሶሱ . . . . . ፯
የናስ እባብ . . . . . ፲፩
የጥያቄዎቻችሁ መልስ
አምልኮ ባዕድ ለምን ትፈጽማላችሁ? . . . . . ፲፮
መስቀሉን ስታከብሩ የተሰቀለውን ለምን
ትረሳላችሁ? . . . . . ፲፯
ምዕራፍ . . . . . ፳፪
ከመጻሕፍት . . . . . ፳፬
ኪነ ጥበብ
ወደ ምን ወደቀ? . . . . . ፳፯
ሦስቱ ዛፎች . . . . . ፳፱
እናስተዋውቃችሁ
ቅድስት ዕሌኒ . . . . . ፴
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
በዓለ መስቀል በቆሎ ተማሪዎች . . . . . ፴፬
ምዕራፍ . . . . . ፴፯
አቡጊዳ የግእዝ ቋንቋና የቅኔ ትምህርት
ቤተ ቅኔ . . . . . ፴፰
በግእዝ እንማማር . . . . . ፴፱
መንገደኛው
መስቀሉን በመሳለቂያ ሥፍራ . . . . . ፵

ዋና አዘጋጅ
ዲያቆን ማለደ ዋስይሁን

ም/ዋና አዘጋጅ
ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ

አዘጋጅ
ጎሩይ ስሜ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ጌታቸው በቀለ

ሪፖርተሮች
ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ
ሕይወት ቦጋለ

የገጽ መልክእ ሌይ አውት ዲዛይነር
ርብቃ ኃይለማርያም

ረ/ገጽ መልክእ ሌይ አውት ዲዛይነር
ወይንሸት ወልደጻድቅ

ጸሐፊዎች
ጸዳሉ ሁንዴሳ
ልደት አስፋው
ደብረወርቅ ተክለጽዮን

የዝግጅት ክፍሉ
ስልክ 0111553442
E-mail - hamermk08@gmail.com
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት
0116554776
፲፰ኛ ዓመት ቁጥር ፮ መስከረም ፳፻፫ ዓ.ም

መስከረም

ለመስቀል ደመራ በዓላችን የምንሰጠው ትኩረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል

የኢትዮጵያን የክርስትና ሃይማኖት ጥንታዊነት ታሪካዊነትና በጽና መሠረት ላይ የመቆሙ ማሳያ የመስቀል ደመራን የመሰሉ ታላላቅ በዓላትን ለረጅም ዘመ ናት በማክበር የምስራቹን /የወንጌልን/ ቃል በአደባባይ ሲመሰክር መኖሩ ነው። የደመራ በዓል በመላው ኢትዮጵያ ባሉ ሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ በተመሳሳይ ሰዓ ትና ሥርዓት በየአካባቢዎቹ ባሉ መስቀል አደባባዮች ተገኝተው የሚያክ ብሩት ነው። ይህም የክርስቲያኖች አን ድነት የሚገለጽበት ማራኪ በዓል ሲሆን ለቤተ ክርስቲያናችን አንድነትና ጽናት ታላቅ ድርሻ አለው። በዓሉ የክርስቶስን መስቀል በሚሰብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማዳን ጌትነትና አምላክነቱን የምንመሰክርበት ከፍተኛ ሐዋርያዊ አገልግሎትም ነው።

በዓለ መስቀል በሮም ክርስቲያናዊ መንግሥት ቤተሰብ ውስጥ ታላቅ ስፍራ በነበራት ንግሥት ዕሌኒ ጌታችን የተሰ ቀለበትን እውነተኛ መስቀል ከተቀበረ በት በማውጣት፣ የጌታችን ደም የፈሰ ሰበትን' ሥጋው የተቆረሰበትን ዕፀ መስ ቀል በማክ በር የሠራቸውን የትሩፋት ሥራም የምንዘክርበት ነው። በዚህም ምክንያት ዓለም አቀፋዊት ከሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አካልና ተባባሪ መሆናችንን የምናሳይበት ነው። ክርስቶ ስን በእውነት በመውደድ' ፍቅራቸውን በመግለጥ ከቆሙ ቅዱሳን ሁሉ ጋር ዘር እና ድንበር ሳይገድበን በማክበር የምን ተባበር፣ ለገድላቸውም ክብር የምንሰጥ መሆናችንን የምንገልጥበት ነው። ስለዚህ ደመራ ፍቅርና አንድነት እምነትና አገ ልግሎት ነው።

በአንድ የመስቀል የደመራ ሥርዓት ዙሪያ ምእመናን ተሰባስበን መገኘ ታችን ባንዱ ጌታ በአባታችን በክርስቶስ ፊት ያለንን ልጅነት በማክበር የምንመላለስ መሆናችንን ያሳያል።

የመስቀል ደመራ በዓል ካለው ሃይማ ኖታዊ ዋጋ ሌላ ሀገራዊ ጥቅምም አለው። በዓሉ በኢትዮጵያ ብቻ ከመከበሩ ጋር ተያይዞ በዚያ የሚማረኩ ከሌሎች ሀገ ራት የሚመጡ በርካታ ጎብኚዎችን ይስ ባል። የመስቀል ደመራ በዓል ከሚከ በርበት የዓመቱ የመጀመሪያ ወር የመስከረም የተፈጥሮ ልምላሜና ተስትሎም በተከ ታታይ በመላው ሀገራቱ በድምቀት እየተከበረ ከሚቆየው የመስቀል በዓል ጋር ተዳ ምሮ ደመራ የበዓላችን ድምቀት ማዕከል ነው። በመሆኑም ከተፈጥሮው ልምላሜ እንዲሁም የመስቀል በዓልን በየቤታችን ከምናከብርበት ሥርዓት በላይ ደመራ ጎብኚዎችን የመሳብ ከፍተኛ ኃይል ስላለው ሀገርና ወገን የሚጠቀሙበት ዘርፈ ብዙ መንገድ አለ። የውጭ ሀገር ዜጎችና ሌሎች ተመልካቾች በበዓሉ ሥርዓት ተማ ርከው ኢትዮጵያውያን የተሰቀለውን ክርስቶስን ለመስበክ ያላቸውን ትጋት በማየት በጌታችን ማዳን አምነው ሲሳቡና ሲጠመቁም ይታያል። በመሆኑም ሁላችንም ሕዝበ ክርስቲያን በዚህ በዓል አማካኝነት ቤተክርስቲያናችን የምትሰጠው መንፈሳዊ አገል ግሎት፣ በእምነትም የምናገኘውን ኃይልና በረከት ከማጽናትና በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያናችን ለሀገር የምታበረክተውን አስተዋጽኦ ከማስቀጠል አንጻር ለበዓሉ አከባበር ተገቢውን ትኩረት ልንሰጥ ይገባል።

ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ለሚታደመው ሕዝበ ክርስቲያን ከፋቅም ከቅርብም ለመጡ እንግዶች የበዓሉን አከባበር ሥርዓት 'የሥነ ሥርዓቱንም ምስጢር' መነሻ ምቹንም በዚህ ረገድ ሊነሡ የሚገባቸውን የዓለም አቀፋዊነትና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ታዳሚዎች ሁሉ ሊረዱባቸው በሚችሉ ቋንቋዎች በግልጽ ማብራ ራት ይገባቸዋል። በተለይም ዛሬ ዛሬ «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ወን ጌልን አታስተምርም» እያሉ ማሩን ለሚያመሩ፣ ወተቱን ለሚያጠቁሩ መናፍቃ ንና የመናፍቃን ተላላኪዎች የመስቀል ደመራ በዓል በስብከተ ወንጌል ያለውን ድርሻ በመግለጥና ወደ ክርስቶስ ፍቅር የሚያቀርብ ሥርዓት መሆኑን በማሳየት የቅ ሰጣ ተግባራቸውን መግታት ይኖርባቸዋል።

በበዓሉ ጉልሕ ተሳትፎ ያለን ስንበት ተማሪዎችና ማኅበራት በዓሉን ለማድመቅ ከምናደርገው ጥረት ጎን ለጎን ተፈላጊው መንፈሳዊ አገልግሎት መሰጠቱን፣ በመክሊ ታችንም ማትረፋችንን ማረጋገጥ ይገባናል። ይህ በዓል በእጻባባይ እውነተኛ የሃይ ማኖታችንን አስተምህሮ የገለጥንበት፣ መናፍቃንን ያሳፈርንበት፣ የደከሙትን ያበረ ታንበት፣ የጠፉትን የመለስንበት፣ የራሳችንን አንድነት ለሌሎችም አገልግሎቶች የጸናንበት መሆኑን ልናረጋግጥ ይገባል።

በአጠቃላይ ሕዝበ ክርስቲያን የመስቀል ደመራ በዓል ሃይማኖታዊ መሠረት ይኑረው እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚከበር በዓል ከመሆኑ የተነሣ ሀገራዊ ጥቅ ሙም የጎላ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። በመሆኑም ክርስቲያኖች ታላቅ በዓላችን እንደመሆኑ ከሚኖረን ጉልህ ድርሻ ሌላ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችም ቢያንስ ከሚኖረን ሀገራዊ ጥቅም አንፃር እስከዛሬ በሚፈጸምበትና ከዚያም በተሻለ መንገድ እየተከበረ እንዲኖር ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማበረታታት ይገባናል።

ለቤተክርስቲያናችንም ሆነ ለሀገራችን የሚፈለገውን ጥቅም ማግኘት እንድንችል እርስ በእርስ መከባበር፣ ለበዓሉ ድምቀት አስተዋጽኦ በማድረግ ለእንግዶች ክብር መስጠት፣ አጽራረ ቤተክርስቲያንም ከበዓሉ ጋር እያያዙ የሚፈጽሙትን ቅሰጣ በማጋለጥ ስለነገረ መስቀሉም በመመስከር የበዓሉን ሥርዓትም በማስከበር በትጋት ልንንቀሳቀስ ይገባል። በዚህ ረገድ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ከትውልድ ትውልድ እንዲጠበቅ የቤተ ክርስቲያንን ክብር፣ ታሪክና አገልግሎትም ቀጣዩ ትውልድ የማየት እድል እንዲኖረው በእግዚአብሔር ረድኤት ተደግፎ አገልግሎት እየሰጠ ያለው ማኅበረ ቅዱሳን ለዚህ ከሚተጉ ሁሉም የቤተክርስቲያናችን ወገኖች ጋር ለመሥራት ያለውን ዝግጁነት በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል።

«ሲከተለኝ የሚወድ... ሐሳቡን አሸክሙ ይከተለኝ»

ማቴ.፲፮፥፳፬

ቀሲስ ፋሲል ታደሰ



መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ፍቅር ስለገለጠበት ሕማምና ሞቱ ለደቀመዛሙርቱ ባስተማረበት ወቅት ለእነርሱም «እኔን ሊከተል የሚወድ ራሱን ይካድ ጨክኖም መስቀሌን ተሸክሞ ይከተለኝ» ብሏቸዋል። አስቀድሞ «የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል» በማለት ነገረ ድኅነትን የሚፈጽምልን በዕፀ መስቀሉ እንደሆነ ተናግሯል። ጊዜው ሲደርስም በቀራንዮ በመስቀል ላይ ዋለ። በገዛ ፈቃዱ ስለ ሰው ልጆች መዳን ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው ለየ። በአካለ ነፍስ ወደ ሲዖል ወርዶ ነፍሳትን ወደ ገነት አሸጋገረ፤ የዲያብሎስንም ሥራ በመስቀሉ ድል ነሣ፥ ሰላምን አደረገ። «በእኛ የሰበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም /ዲያብሎስ/ በመስቀሉ ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል» እንደሚል/ቆላ. ፪፥፲፬/።

ቅዱስ ዮሐንስ «ወበዝንቱ ተዐውቀ ፍቅሩ ለእግዚአብሔር፤ የእግዚአብሔር ፍቅሩ በዚህ ታወቀ» በማለት እንደገለጸው አምላካዊ ፍቅሩን በሕማማተ መስቀሉ አሳይቶናል /፩ኛ ዮሐ ፬፥፲/። ሕግን የጣስን ቅጣትም የሚገባን የሰው ልጆች ሆነን ሳለ፤ ነገር ግን ከቸርነቱ ብዛት «የሚቹን ሞት አልወድም» በማለት በዘለዓለም ሞት ተቀጥተን እንድንኖር አልወደደምና በሕማማተ መስቀሉ «ደዌያችንን ተቀበለ ሕማማችንን ተሸከመ፤ ስለ እኛም ታመመ... በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን» /ሕዝ ፲፰፥፴፪፤ ኢሳ ፶፫፥፬/።

የእግዚአብሔር ፍቅር በመስቀል እንደተገለጠ ሁሉ የሰው ልጆችም እርሱን የመውደዳችን መገለጫ መስቀሉን በመሸከም መከተል እንደሆነ በአምላካዊ ቃሉ አስተምሮናል። ይህም ማለት እንደ ጌታችን ረጅምና ክብደት ያለው ዕፀ መስቀልን በትከሻችን ተሸክመን ቀራንዮ እንድንንዝ ሳይሆን፤ መከራ መስቀሉ ስለ እኛ ሲል የፈጸመልን መሆኑን በማመን እና ተከታዮቹ በመሆናችን የሚመጣብንን መከራ በመታገሥ መኖር እንደሚገባን ሲያመለክተን ነው። በዚህም መሠረት «መስቀል መሸከም» የተባለው በዓለም ስንኖር በክርስትና ምክንያት የሚገጥመንን መከራ ነው። «በዓለም ግን መከራ ትቀበላላችሁ፤ ነገር ግን ጽኑ እኔ ዓለሙን ድል ነስቼዋለሁና» እንዲል /ዮሐ ፲፮፥፴፫/። በወቅቱ ይህ ቃል የተነገራቸው ቅዱሳን ሐዋርያት መስቀሉን በመሸከም ማለትም ስለ ክርስትና ኑሮ የመጣባቸውን መከራ በመታገሥ እና ድል በመንሳት ኑረዋል፤ ለዚህም ነው። «መንግሥተ ሰማያት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» በማለት በቃልም በተግባርም የገለጹት /ሐዋ. ፲፬፥፳፪/።

የክርስትና ጉዞ እንደ ቀራንዮ ጉዞ መከራ የበዛበት ነው። ፈቃደ ሥጋን እየ ታገሱ ለፈቃደ ነፍስ እየኖሩ፤ ዓለምን፣ ዲያብሎስን እየተዋጉ እስከ ሞት በመጽናት ተጉዘው የክብር አክሊል የሚቀዳጁ በት ሕይወት ነውና « እስከ ሞት ድረስም የታመንህ ሁን የሕይወት አክሊልንም እሰጥሀለሁ» ተብሎ እንደተጻፈ /ራእ. ፪፥፲/።

መከራ ከየት ይመጣል?

፩/ ከዲያብሎስ - ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ የሰው ልጅን በኃጢአት መጣል ቋሚ ሥራው ነው። ይልቁንም የመስቀሉን ዓላማ የያዙ ክርስቲያኖችን ይከታተላል። በተለያዩ ወጥመዶችም ለመያዝ እና መከራ ለማጽናት ይሞክራል። ቅዱስ ጴጥሮስ «ጠላታችሁ ጋኔን የሚውጠውን ፈልጉ እንደሚያገሳ አንበሳ ይዞራልና» ሲል ቅዱስ ጳውሎስም «ሰልፋችሁ ከጨለማ ገዦች... ከክፋዎች አጋንንት ጋር ነው» በማለት ውግያውን ገልጾታል። ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ መጽሐፉም በሰ ይጣን አማካኝነት የተለያዩ መከራ ዎች እንደሚመጡ ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል «ትቀበለውም ዘንድ ስላለህ መከራ አትፍራ፤ እነሆ እንድትፈተኑ ሰይጣን ከእናንተ አንዳንዶችን ወደ እስር ቤት እንዲገቡ ያደርጋል...» /ራእ.፪፥፲/። ቅዱሳን ከዲያብሎስ የመጣባቸውን መከራ በመታገሥ ለክብር እንደበቁ ገድላት ምስክሮች ናቸው። «ክርስቶስን በመከራ ትመስሉት ዘንድ ደስ ይበላችሁ» እንደ ተባለው ቅዱሳን የመጣባቸውን መከራ በጸጋ በመቀበል ጌታቸውን መስለዋል /፩ኛ ጴጥ. ፬፥፲፫/።

ጠላታችን ዲያብሎስ ፈቀደ ሥጋን በማስወደድ፣ በደካማ ጉናችን በመፈታ ተን፤ በሥጋዊ ምኞት ለመጣል መከራ ያመጣብናል። ለእኛ አብነት እንዲሆነን በተፈጸመው የገዳመ ቆሮንቶስ የዲያብሎስ ፈተና እንደምንገነዘበው፤ «ዛሬም ለእኔ ብትሰግድ፣ ብትገዛ...» በማለት በምኞት ዓለም በማስጐምጀት ከእግዚአብሔር ሊያርቀን ይታገለናል። ስለሆነም ጌታችንን በክብር የምንመስለው መስቀሉን



በመሸከም ከመሰልነው እንደሆነ በማስ ተዋል ከዲያብሎስ በተለያዩ መንገዶች የሚመጡብንን መከራዎች በመታገሥ እና ድል በመንሣት ለመኖር መዘጋጀት ይጠበቅብናል። መስቀሉን የመሸከም መገለጫም የሚደርስብንን የተለያየ መከራ መታገሥ እንደሆነም በማስታወስ፤ ክብሩን በማሰብ፤ ክርስቲያናዊ ፈተናን ለመ ቋቋም እንበርታ። «ካለው ክብር ጋር ሲመዛዘን መከራው ምንም እንዳይደለ እናውቃለን» እንደሚል /ሮሜ. ፰፥ ፲፰/።

፪/ በራሳችን ክፉ ምኞት- አንዳንድ ጊዜ ከመንፈሳዊነት ርቀን የምናውጠነ ጥነው ክፉ ምኞት በራሳችን ሕይወት ላይ መከራ ሲያመጣብን ይስተዋላል። ቅዱስ ያዕቆብ «በእናንተ ዘንድ ጥልና መጋደል ከወዴት ይመጣሉ? በሰውነታችሁ ውስጥ የሚሠራውን ዝሙት ከመውደድ የተነሣ ከዚህ አይደለምን..» በማለት ከራስ ክፉ ምኞት መከራ እንደሚመጣ ያስገዝበናል። በመንፈስ ስንዝል ኃጢአት ወደ እኛ ሳይሆን እኛ ወደ ኃጢአት መጓዝ እንጀ ምራለን። አምኖን በገዛ ምኞቱ ተፈትኖ በዝሙት እንደወደቀ ሁሉ ዛሬም በራ ሳችን ክፉ ምኞት በመገፋፋት በኃጢ አት በመውደቅ ዳግማዊ አምኖን እንዳ ንሆን ያስፈልጋል /፪ኛሳሙ. ፲፫፥፩/።

በአብዛኛው ያለፈቃዳችን የምንሠራው ኃጢአት እንደሌለ ልናጤን ይገባናል። ይህንንም «ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል» እን ዲል /ያዕ ፩ ፥ ፲፬/።

በመሆኑም ለክፉ ምኞት ተጋላጭ የሆነውን ጎሊናችንን በመግዛት፤ ለመል ካም ሥራ መነሣሣት መታገል በራሱ መስቀል መሸከም መሆኑን ዘወትር ልን ዘነጋ አይገባንም። በፈቃደ ሥጋ ለተዘ ፈቅንም ከዚህ ለመውጣት የሚደረገው ትግል ተገቢ መሆኑን በመረዳት መንፈሳዊ ተጋድሎውን ልናፀና ይገባናል። «ሰውነቱን በመከራ የሚያሰቃያትን አመስግኑት» /ኢሳ. ፶፬፥፯/ ተብሎ እንደተጻፈ የፈ ቃደ ሥጋ ምኞት የሆኑትን ዝሙት፣ ሰሰኝነት፣ መዳራት.. የመሳሰሉትን ድል ለመንሣት መታገል የሚያስመሰግን ተግ ባር ነው። ስለዚህም የሥጋን ሥራ በመንፈሳዊ ሥራ በመተካት ከራሳችን ምኞት ፈተና እንዳይጸናብን መንገዱን ለመዝጋት እየጣርን በጾም በጸሎት ረድ ኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ እናድርግ። «እንደ እግዚአብሔር ፈቃደ መከራን የሚቀበሉ ሰዎችም መልካም ሥራን በመ ሥራት ለታመነ ፈጣሪ ነፍሳቸውን አደራ ይስጡ» ተብሏልና/ ፩ኛጴጥ. ፬፥፲፱/።

፫/ ካላመኑ ወገኖች-በክርስትና ኑሮ ላይ መከራ ከሚመጣበት አንድ ካለመኑ ወገኖች ነው። ከዘመነ አበው ጀምሮ በአምልኮተ እግዚአብሔር የጸኑ ሰዎች እግዚአብሔርን ከማያምኑ ወገኖች መከራ ሲመጣባቸው ኖሯል። የግብጹ ፈርዖን እሥራኤል ላይ መከራ ማጽናቱ እና ከዐሥሩ የቅስፈት ዓይነቶች አለመማሩ ያለማመኑ ውጤት ነው። በመሆኑም እሥ ራኤል ባሕረ ኤርትራን ሲሻገሩ ፍጻሜው ስጥመት ሆኗል። ቅዱሳን ሐዋርያትን አይሁድ፣ ጣዖት አምላኪዎች እና ጠንቋ ዮች መከራ ያጸኑባቸው እንደ ነበር በሐ ዋርያት ሥራ ተመዝግቧል። ለምሳሌ ኤል ማስ የተባለ ጠንቋይ ወንጌልን እንዳይሰ ብኩ ሲፈታተናቸው፤ ሌሎች ደግሞ መጽሐፎቻቸውን በማቃጠል የአገልግ ሎት እንቅፋት ሆነውባቸዋል። እንደዚ ሁም በማሳደድ እና በመግረፍም ሄሮድ ስና ሌሎችም ዐላውያን ነገሥታት መከራ ያመጡባቸው ነበር። /ሐዋ ፲፫፥፮፤ ፲፱፥፲፱/ ለዚህም ነው። «መከራ ተቀብለን ተንገላ ተን ወንጌልን ተናገርን» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ መከራቸውን ገለጸው /፩ኛተሰ. ፪፥፪/ በተጨማሪም ስደት፣ መራብ፣ መጠ ማት፣ ነቀፋ.. እና የመሳሰሉት በአገልግሎ ታቸው ጊዜ የተለመደ መከራ ስለ



መሆኑ እና ነገር ግን የቅዱሳን አበው ጭንቀት ከሌሎች ስለሚመጣው መከራ ሳይሆን የአብያተ ክርስቲያናት ሐሳብ ስለመሆኑ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ አስገንዝቧል /፪ኛቆሮ. ፲፩.፳፰/። የዘመነ ሰማዕታት ቅዱሳን ሰዎች ኑሮም እንደሚያስረዳው በየዋሻው እምነታቸው ውን የገለጡበት እና ደማቸውን ስለ ክር ስትና ያፈሰሱት እንደእነ ዲዮቅልጥያኖስ እና መስሎቹ ካመጡባቸው መከራ የተ ነሣ መሆኑን የቤተክርስቲያን ታሪክ ማስ ረጃ ነው። በዘመናችንም በተለያዩ መን ገዶች በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አም ላክነት ካላመኑ ወገኖች መከራ ሊመጣ ይችላል። አይሁድ የክርስቶስን መስቀል እንደቀበሩ፣ የቤተክርስቲያንን ትውፊትና ሥርዓተ ትምህርት ለመቅበር በመሯሯጥ በተዋሕዶ እምነታቸው የዳኑትን ምእመ ናን እና አገልጋዮችን የሚፈታተኑ ተረፈ አይሁድ በየዘመኑ ይነሣሉና። «በመጣባችሁ መከራ አትደነቁ» እንደተባለ፣ ስለ ሃይ ማኖት ከሚያምኑ /ከተጠራጣሪዎች/ በሚ መጣው ፈተና ሳንታወክ በመንፈሳዊ ሕይወት እና በተዋሕዶ ትምህርት ልን ጸና ይገባናል።

ከላይ የጠቀስናቸውን የመከራ ምን ጮች መሠረት አድርገን በዘመናችን ስላለው መከራም ልናተኩር ይገባናል። በክርስትና ኑሮ ላይ እየተፈታተኑን የሚገኙትን የመከራ ዓይነቶች ከራ ሳችን እና ከውጪ ብለን ብንጠቀም ለመረዳት ግልጽ ይሆናል። ለአብነት ያህልም ከራሳችን ከሚመጡብን የወቅቱ ችግሮች ሁለቱን እንመልከት።

፩/ ዓለማዊነት- «ወንድሞች ሆይ ይህን ዓለም አትውደዱ፤ ዓለምን መውደድ ከእግዚአብሔር ጋር ጥል ነው።» ይላል ነገር ግን ከሰይጣን ግፊት ወይም ከራ ሳችን ከደካማ ጐን የተነሣ በመውደቅ ለዓለም ምርኮኛ መሆን የተለመደ ሆኗል። ዓለማዊነት ስንልም በዓለም ውስጥ የሚገኝ የኃጢአት ተግባራት መፈጸምን ነው በዘመናዊነት እና በሥልጣኔ ሰበብ ብዙ ዎች ለዕውቀትና ለልማት የሚሆነውን በጐ ነገር ከመቅሰም ይልቅ ኃጢአታዊ ተግባራት ላይ ሲያተኩሩ ይታያል። ለም ሳሌ ከመጸም መብላትን፣ ከማስቀደስ መተኛትን፣ ከመዝሙር ዘፈንን፣ በሥር ዐት ከመልበስ ፋሽን መከተልን.. የመሳ ሰሉትን ማዘውተሩ በዓለማዊ ምኞት የመጠመድ መገለጫ ነው። በአንድ ወቅት እሥራኤል ከሞዓብ መንደርና ተግባር በመተባበራቸው በጣዖት አምልኮ በዘፈን እና በዝሙት ሲወድቁ ለቅሰፈት ተዳ ርገዋል። ዛሬም ቢሆን በክርስትና ኑሮ የሚንዙ አርቶዶክሳዊያን ዕውቀት፣ ገን ዘብ እና ሀገር መለወጥ ሲገጥማቸው በጐ ውን ከመጠቀም ይልቅ የሥልጣኔ ትር ጓሜ ባለመረዳት የክርስትና ሕይወትን በዓለማዊነት ሲለውጡ፣ በአነጋገር፣ በአ ለባበስ በውሎ... በመሳሰሉት ሞዓዊ ሥራ መሥራት እየተበራከተ መጥቷል /ዘኁ.፳፭/። ስንቶቻችን ነን ከዓለማዊነት ሸክም ርቀን ስለ እግዚአብሔር ፍቅር መስቀሉን ተሸ ክመን ለመኖር የተዘጋጀን? ዛሬ ዛሬ ከዓለማዊነት የተነሣ ቤተክርስቲያንን መከተል ሳይሆን ቤተክርስቲያን እንደ እነርሱ ፍላጐት እንድትከተላቸው የሚፈ ልጉ አይጠፉም። ለሥርዐት ከመገዛት ይልቅ «ምን አለበት፣ ምን ችግር? አለው» በሚል ቃላት ተደልለው ለቀኖና ቤተ ክርስቲያን ቸልተኛ ከመሆን እስከ ኑፋቄ መድረስ እየተለመደ ነው። ስለዚህም ለሥጋ ሥራ የሚያተጋውን ዓለማዊነትን አርቀን ለመንፈስ ፍሬዎች የሚያበቃ ውን ነገረ መስቀሉን እያሰብን ጌታችንን በእውነት ልንከተለው ይገባናል።

፪/ ፍቅረ ንዋይ- ባለንበት ወቅት በፍቅረ እግዚአብሔር እንዳንጸና ከሚፈታ ተነን አንዱ ገንዘብ ወዳድ መሆን ነው። ይሁዳ እንደ ሌሎቹ ደቀመዛሙርት መስቀሉን ተሸክሞ እንዳይከተል ጠልፎ የጣለው ኃጢአት ፍቅረ ንዋይ መሆኑ የታወቀ ነው። ዛሬስ ለምን በዐሥራት አልታመንም? ሰንበትና በዓላትን አላከበ ርንም..? ብለን ራሳችንን ብንመረምር ያለኝ ይበቃኛል የሚለውን ምክር ወደ

ጐን ትተን በፍቅረ ንዋይ መጠመዳችንን የሚያሳይ ነው። የሙስና መብዛት፣ አጭበርባሪነት መበራከት፣ በንግድና በተ ለያዩ ዘርፎች አታላይነት ከመጠን ማለፉ ፍቅረ ንዋይ ሲጸና ውተን እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ቅዱስ ጳውሎስ «ገንዘብ መውደድ የክፉት ሁሉ ሥር ነው» በማለት እንደ ገለጸው ለገንዘብ ሲባል በየቤቱ፣ በየቢሮው፣ እና በተለያዩ ቦታዎች የክፋ ሥራ መበራከት የሰላም መጥፋት የአደባባይ ምስጢር አይደለምን? /፩ኛ ጢሞ ፮፥፲/

ከውጪያዊ አካላት የሚመጡብንን የክርስትና ሕይወት እንቅፋቶች ለመዘርዘር ይህ አጭር ጽሑፍ በቂ አይሆንም። ነገር ግን ለአብነት ያህል አንዱን እንመልከት-

፩/ የሐሰት ክስ /ስም ማጥፋት/- ዲያብሎስ የታወቀው እና ሥራውን የጀመረው በሐሰት ንግግር መሆኑ ይታወቃል። በዓለመ መላእክት «እኔ ነኝ ፈጣሪ» ማለቱ እና አዳምና ሔዋ ንን በሐሰት ትምህርት ማጥመድ የሐሰት አባትነቱን አረጋ ግጦለታል። ጥንትም ሆነ ዛሬ በሐሰት አንደበት የግብር ልጆቹ የሆኑ ሐሳዌውያን እውነተኞችን በሐሰት ሲከሱ እና ስማቸውን ሲያጠፉ ይገኛሉ። በእግዚአብሔር ቃል ጸንተው እውነትን ይዘው የሚታገሉትን ከሚገጥማቸው ፈተና አንዱ ከሐሰተኞች የሚሰነዘር ስም ማጥፋት ዘመቻ መሆኑ እየተለመደ መጥቷል። በመሠረቱ አይሁድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሐ ሰት መክሰሳቸውን ያስተዋለ ክርስቲያን በዚህ ሊደነቅ አይገባውም። በዘመነ ብሉይ ሶስናን ብናስታውስ ያልፈጸመችውን እንደ ፈጸመችው አድርገው በሐሰት ከሰዋት ለፍርድ ያበቁት ረበናት ለጊዜው ስም ማጥፋቱ ቢሳካላቸውም እውነቱ ሲገለጥ ግን ውርደቱ እና ቅጣቱ በእነርሱ ላይ ሆኗል። ዛሬም በቤተክርስቲያን አገልግ ሎት የተጠመዱትን ከአባቶች እስከ ምእ መናን በሚገኙ አገልጋዮች ላይ ስም ለማ ጥፋት የሚሯሯጡ ውሉደ ሐሰት ተበራ ክተዋል። ንስሐ ካልገቡ ፍጻሜያቸው እንደ ረበናቱ ይሆናል። ቅዱስ ጳውሎስ «በሌላ ትፈርድ ዘንደ ማነህ?... እርሱን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና» /ሮሜ ፲፬፥፬/ በማለት እንዳስተማረው ሐሰ ተኞች የፈረዱባቸው ወገኖች አጥፍተው እንኳን ቢሆን ንስሐ ገብተው እንደሆነ ምን እናውቃለን? በውኑ የአገልግሎት ማኅበራትን አባቶችን የቤተክርስቲያን ሓላፊዎችን... ለማዋረድ በመሞከርስ የሚ ገኘው ጥቅም ምን ይሆን?

አንዳንድ ጊዜ የምንታማበት ነገር እውነት ከሆነም የታማው /ዩተተቸው/ አካል ልቡ ያውቃልና ራሱን ሊመረምር ይገ ባል። ሆኖም ግን ሐሰተኞች /ሰዳቢዎች/ ሊገነዘቡ የሚገባው ለሃይማኖት በመቅናት ከሆነ አገላለጹ ይህ እንዳልሆነ ተረድተው ይልቁንም ክርስቲያን ከባቴ አበሳ መሆን በፍቅር እና በቅርበት ስሕተተኞችን በምክርና በጸሎት በማገዝ ቢሆን የዓመፃ ሳይሆን የእውነት መሆኑ ግልጽ ይሆናል።

ማጠቃለያ

የክርስትና ኑሮ አልጋ በአልጋ እንዳልሆነ ከልብ ከተረዳን እውነትን የያዘ ሁሉ ፈተና ሲገጥመው «መስቀሉን ይሸከም» የሚለውን ቃል ሊያስተውል ይገባል። የሚገጥመንንም መከራ በሚከተሉት ነጥቦች ድል መንሣት እንችላለን።

፩/ ትዕግሥት- «ኢዮብ ታገሠ እግዚአብሔርም ሰማው» /ያዕ፭፥፲፩/ ተብሎ እንደተጻፈ ትዕግሥት ይኑረን። የማይፈተን የተባረከ ነው አልተባለም፤ በፈተና የሚጸና እንጂ። በመሆኑም ከጌታችን እና እርሱን መስለው ከተገኙ ከቅዱሳን በመማር መስቀሉን በትዕግሥት ተሸክመን ልንጓዝ ይገባል። ቅዱሳን ሐዋ ርያትን መከራ አጽንተውባቸው በሸንጐ ሲያቆሟቸው በትዕግሥት ተቀበሉት። «በሸንጐ ፊት ስለተናቁ ደስ ብሏቸው ወጡ» እንደሚል መከራን በጸጋ ተቀበሉ /ሐዋ. ፭፥፵፩/።

፪/ ፍቅር- «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት» /ሮሜ ፰፥፴፭/ እንደተባለ ፍቅር ያለው መከራን ይታገሣል /፩ኛ ቆሮ ፲፫፥፯/። ሊያ ስፈራን የሚገባ ከእግዚአብሔር መለየት እንጂ፣ በእግዚአብሔር መንገድ ሆነን የሚ ገጥመን መከራ መሆን የለበትም። የክርስትና ሕይወ ትም ሆነ ፍቅረ እግዚአብሔር ዋና መገለጫው መከራ መቀበል መስቀሉን ተሸክሞ በፍቅር መኖር ነውና። በመሆኑም በትክክለኛ መንገድ ዓላማውን ተረድቶ


ለክፉ ምኞት ተጋላጭ የሆነውን ኅሊናችንን በመግዛት፤ ለመልካም ሥራ መነሣሣት መታገል በራሱ መስቀል መሸከም መሆኑን ዘወትር ልንዘነጋ አይገባንም።

የመጣ አገልጋይ አስፈሪ ነገሮች እንኳን ቢገጥሙት ወደኋላ አይሸሽም፤ ቅዱሳን ሁሉን ትተው እንደተከተሉት ፍቅረ እግዚአብሔር ራስን እስከ መስጠት ያደርሳልና /ማቴ ፲፩፥ ፲፩/።

፫/ ጽናት- እያንዳንዱ አገልግሎት የራሱ የሆነ ችግር አለው። ውጤቱም ጽናቱ ላይ ነው «እያንዳንዱ በራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል» የተባለው እንዲፈጸምልን ጽናት ወሳኝ ነው። «በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤.. እንሰደ ዳለን እንጂ አንጣልም..» ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ለአገልግሎት ያለንን ቁርጠኝነት በጽናት ልንገልጽ ይገባናል።

በአጠቃላይ የክርስትና ሕይወት መከራው ብዙ ዋጋውም እጅግ ብዙ ነውና በትዕግ ስት፣ በፍቅር፣ በጽናት ሆነን እንትጋ በመከራ ጽናት መስለነው መስቀሉን ተሸክመን እስከሞት ከተጓዝን ክብርን ያቀዳጀናልና። በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል እንደሚል /ማቴ. ፲፥፳፪/።

መስብሐት ለእግዚአብሔር



ሐመዱ ተዋሕዶ

የሺ፲፲፪ ዓ.ም የሐመር መጽሔት ልዩ ዕትም መጽሐፍ

መረጃ ሰጪና አስተማሪ መልእክቶች የተካተቱበት
የሐመር መጽሔት ዝግጅት ክፍል ልዩ ሥራ

- "ተሐድሶን በአውሮፓ ምን ወለደው?
- "ተሐድሶ" የሕንድን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ጎዳት?
- በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ጉዳት እያደረሰ ያለው "ተሐድሶ" የተባለው ሚረር ቡድን ማንነትና ምንነትን እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመጉዳት የሚከተላቸውን ስልቶች የሚያስገነዝብ ጠቃሚ ሰነድ።

የሐመረ ተዋሕዶ ልዩ ዕትም በሌሎችም ፅንሰ ሐሳቦች ላይ ማብራሪያዎችን ይዟል።

- ሀብትና ድህነት በክርስትና ሕይወት ውስጥ
- የከሰረው የአዝጋሚ ለውጥ ቲዎሪ ሂደትና ያለበት አሳፋሪ ደረጃና ሌሎችም ጉዳዮች የተቃኙበት አስፈላጊ መጽሐፍ

የሐመርን ልዩ ዕትም
በአዲስ አበባና በክፍለ ሀገር በሁሉም የማኅበረ ቅዱሳን ማስፋፊያዎች
በሌሎችም የቤተ ክርስቲያናችን ጋዜጣ፣ መጽሔትና መጻሕፍት
ማከፋፈያ ድርጅቶች ያገኙታል።

ስልክ 0920959592/90/91/99 / 0111246184

የሐመር ልዩ ዕትም ለምእመናን የቀረበ የአዲሱ ዓመት ልዩ ስጦታ

ሐመርና ስምዐ ጽድቅን ያንብቡ፤ ያስነብቡ፤ በሐመርና ስምዐ ጽድቅ ይጻፉ፤ ይሳተፉ

ከደመራው በፊት የማይለኮሱት ደመራዎች

ዲ/ን ሄኖክ ኃይሌ



መምህር ዕንቈ ባሕርይ ተከስተ

ምኛ ክፍል ጋዜጠኛ ሲናገርበት ባደገው በኦሮምኛ ቋንቋ ይህን መንፈሳዊ መልእክት በመስማቱ ልቡ ተነክቶ ዕንባውን አፈሰሰ። ስሜቱን ተቆጣጥሮ ለመጣበት ሥራ ጉዳይ ቃለመጠይቅ ለማድረግ ከሚዘምሩት ወጣቶች አንዱ ቱን ጠርቶ በኦሮምኛ ቋንቋ ጥያቄውን ማቅረብ ጀመረ። ተጠያቂዋ ወጣት ገሊላ የምትባል የምእራፉ ቅዱሳን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋይ ስትሆን እንደምታስተባብራቸው ወጣቶች ሁሉ እርስዋም በኦሮምኛ መዘመር እንጂ በኦሮምኛ መናገር አትችልም ነበር። ይህ ገጠመኝ የተፈጸመው ከዓመታት በፊት ከደቡብ ክፍለ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ወጣቶች በአንድነት መዝሙር ያጠኑበት በነበረው በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ነበር።

የመስቀል በዓል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሥፍራ ከሚሰጣቸውና በታላቅ ድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መንፈሳዊያት አንዱ ነው። የመስቀል በዓል ከሁሉም በላይ ትኩረትን የሚስበው ደግሞ ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ እስከ አበው ሊቃነ ጳጳሳት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ዲያቆናት በተገኙበት ምእመናንና በርካታ የሀገር ውስጥና የውጪ ጎብኚዎች በተገኙበት የሚከበር በመሆኑ ነው። በዚህ ክብረ በዓል ላይ ታዲያ የድምቀቱ መንሥኤ የሆኑ የምስጋና ችቦን ይዘው ከደመራው በፊት የሚ ያበሩ በሺህዎች የሚቆጠሩ የሰንበት ትምህርት ቤቶችና የማኅበረ ቅዱሳን ወጣቶች ናቸው። የእነዚህ ወጣቶችን ጎብረ ትር

ኮታላላ ፈኖ ዋቀዮ ራጂሳ
ጃማ ዋኒ ኒአርገኒ ጉሪንደጌኜ
ኢንደጋኒ
ዱኩባ ጎጋ ኒቁልቁላሁ ገረሳኒን
ዱፋኒ
(ኑ እዩ የመስቀሉን ተአምራት
ዕውራንም ያያሉ የማይሰሙም
ይሰማሉ፤
ለምጻሞችም ይነጻሉ
ወደ እርሱ የመጡ ሁሉ)

ይህንን መዝሙር በኦሮምኛ ቋንቋ ወጣ ቶች ሲዘምሩ የሰማው የራዲዮ ፋና የኦሮ

ዒት አይቶ ያላደነቀና ያላመሰገነ አለ ለማለት ቢቸግርም ከዚህ ጎብረ ዝማሬና ትርዒት በስተጀርባ ስላለው ውጣው ረድና ደካም ግን የሚያውቁ ጥቂቶች ናቸው።

‹መስቀል ብርሃንዩ ንዅሉ ዓለም መሠረቲዩ ናይ ቤተ ክርስቲያን ሠላም ዝህብዩ መድኃኔዓለም መስቀል መድኀኒዩ ንዝአመና ሰባት› (ትግርኛ)

የመስቀል ደመራ በዓል ከንጉሡ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ በማእከላዊ ሥፍራ መከበር እንደጀመረ የሚነገር ሲሆን ከዚያም በኋላ በነበረው መንግሥታዊ ሥርዓት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ምቹ ያልነበረ በመሆኑ የደመራ በዓል አንድ ጊዜ ጃንሜዳ አንድ ጊዜ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፊት ለፊት ባለው በዐጤ ምኒልክ አደባባይ ሲከበር እንደነበር የነበሩ ይናገራሉ። የመንግሥት ለውጥ ከተደረገበትና አንጻራዊ ሰላም ከሰፈነበት ከ፲፱፻፹፫ዓ.ም. በይፋ በመስቀል አደባባይ መከበር ጀመረ። የበዓሉ አከባበር በተቀናጀና ብዙኃንን ባሳተፈ መልኩ ተጠናክሮ መከበር የጀመረው ግን ከ፲፱፻፹፮ዓ.ም. ጀምሮ ነበር።

የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደረጃ መምሪያ በሥሩ ያሉትን በስድስት ምድብ የተከፈሉ ወጣቶች ለዚህ በዓል መዝሙሮችን አጥንተው ትርዒቶችን እንዲያቀርቡ ያደርጋል። የወጣቶቹ ምድብ የአራቱ መዓዘናት (ሰሜን ደቡብ ምሥራቅና ምዕራብ) ክፍለ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ጎብረት፣ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ጎብረት እንዲሁም በማደራጃ መም ሪያው ሥር ያለውና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችንና ምሩቃንን በሥሩ የሚያቅፈው የማኅበረ ቅዱሳን መዘምራን ናቸው።

ማደራጃ መምሪያው ለመስቀል ክብረ በዓል ለሚያቀርቡት ወጣቶች በየአጥቢያቸው አማካይ በሆነ ቅጥረ ቤተ ክርስቲያን ተሰባስበው ከሦስት ሳምንታት ለሚበልጥ ጊዜ መዘመርና የሚያሳዩትን ትርዒት እንዲያጠኑ የሚያ ደርግ ሲሆን የወጣቶቹ የመንገጭ ወጪ በሚመጡበት ቤተ ክርስቲያን የሚሸፈን ነው። በአደባባዩ የሚታየውን ትርዒት በወረቀት ከመንደፍ ጀምሮ ከጸደቀ በኋላም የሚያስጠኑት ከየሰንበት ትምህርት ቤቶቹ የተውጣጡት ወጣቶች ናቸው። የትርዒት ቁሳቁስና የአሰልጣኞች መንገጭ ወጪ ደግሞ በሀገረ ስብከቱ የሚሸፈን ነው። በዚህ ትርዒት የሚሳተፉት ወጣቶች ከየሚነሡበት ቤተ ክርስቲያን እስከ መስቀል አደባባይ በሚያደርጉት ረኻቦም ገዞ በየጎዳናው እያመሰገኑና ትርዒት እያሳዩ ባማሩ እግሮቻቸው መልካሙን የምሥራች እያወሩ ነው።

ይህንን በዓል ከሁሉ በላይ ልዩ የሚያደርገው ደግሞ ከየአቅጣጫው የሚመጡት ወጣቶች በግእዝ፣ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በአገውኛ፣ በጉራጊኛ፣ በእንግሊዘኛ እየዘመሩ ቤተ ክርስቲያን ኩላዊት

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



‹በፍጽም ወበእንግድዓ በአዕምሮ ወበመዝራዕት ትእምርተ መስቀል ጻዊረነ ናንሰሱ›

ዲ/ን ሄኖክ ኃይሌ



በገነት ካሉት ዕፅዋት መካከል እንዳይበላው ታዝዘ የነበረው ዕፀ በለስ በመብላት ከክብሩ የተዋረደውና ልጅነቱን ያጣውን አዳምን ሰው ሆኖ እንደሚያድነው ቃል በገባለት ወቅት ‹ወእትቤዘወከ በመስቀልየ ወበ ሞትየ› ‹በመስቀሌ (በመከራዬ) እና በሞቱ እቤዝሃለሁ› ብሎ ቃል ገብቶ ለት እንደነበር መጽሐፈ ቀለምንጦስ ያስረዳል። በመሆኑም ሰውን ለማዳን መሥዋዕት የሆነው አምላክ በሰይፍ፣ በስለት፣ በመቃጠል በመሳሰሉ መን ገዶች ሳይሆን በመስቀል ላይ በመ ሰቀል መሥዋዕት ሆኗል።

ስለዚህም አዳም ቀጥፎ በበላው ዕንጨት ምክንያት ያጣውን ጸጋና ክብር እግዚአብሔር በእንጨት ላይ ተሰቅሎ በመካስ አድኖታል። አበው ‹ዕዕ ይቀትል ወዕዕ የሐዩ› (ዕዕ ይገ ድላል፤ ዕዕም ያድናል) የሚሉት ይህንን በማስተዋል ነው።

መስቀል ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለበት ጊዜ አስቀድሞ በመስቀሉ ድኅ ነትን እንደሚሰጠንና ኃይሉን እንደሚገ ልጥ፣ ትእምርተ መስቀል ትእምርተ መዊዕ (የማሸነፍ ምልክት) እንደሆነ ትንቢቶች ተነግረዋል፤ አምሳላትም ተመስለዋል።

በመፈጠር ከሰው የሚቀድሙት ቅዱ ሳን መላእክት ይልቁንም ከእነርሱ በቅዳሴ የሚያገለግሉት ሱራፌል ነቢዩ ኢሳይያስ ያየው ራእይ እንደገለጠው ነገረ መስቀሉን በተግባር የሚያወሱ ናቸው። ‹‹እግዚአብ ሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት የልብሱም ዘርፍ መቅ ደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር ለእያንዳንዱም ስድ ስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር በሁለቱም ክንፍ ይበርር ነበር።››› (ኢሳ.፮፥፪) በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙት ሱራፌል ፊታቸውን መሸፈ ናቸው ‹ፊትህን ማየት አይቻለንም› ሲሉ፤ እግራቸውን መሸፈናቸው ‹በፊትህ መቆም አይቻለንም› ሲሉ ግራና ቀኝ ክንፎቻቸውን መዘርጋታቸው ደግሞ ‹ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ቢሄዱ የማትገኝ ረቂቅ ነህ› ሲሉ ሲሆን ተመስጦአቸ ውን፣ ትሕትናቸውንና ለተልዕኮ መፋጠና ቸውን የሚያስረዳም ነው። እንዲሁም ከስድስቱ ክንፎቻቸው አራቱን ራሳቸውን ለመሸፈን ማዋላቸው የመላእክቱን ትሕ ትና የሚያሳይና እግዚአብሔርን ለማመ ስገን የሚቆሙ ሁሉ ራሳቸውን መሸፈንና የእግዚአብሔርን ክብር መግለጥ እንደ ሚገባቸው አብነት የሚሆን ነው።

ይህን የመላእክት አቅዋም ኢትዮጵያ ዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ከሩቅ አይቶት ኖሮ እንዲህ ሲል ተርጉሞታል። ‹‹እልክቱ ይከድኑ ገጾመ ወእገሪሆመ በአርኢያ ትእምርተ መስቀል ከመ ይድኃኑ እም እሳት ዘይወጽእ እመለኮተ ወልድኪ›› ‹‹እነዚያ ከልጅሽ መለኮት ከሚወጣው እሳት ይድኑ ዘንድ ፊታቸውንና እግሮ ቻቸውን በትእምርተ መስቀል አምሳያ ይሸፍናሉ›› (አንቀጸ ብርሃን) በመ ሆኑም እነዚህ መላእክት በመስ ቀል ምልክት በፊቱ ለምስጋና መቆማቸው ‹በዚህ ተሰቅለህ ዓለ ሙን ታድነዋለህ› ሲሉ ሲሆን እኛም እነርሱን አብነት አድርገን መስቀልኛ ለብሰን ስሙን እናመ ሰግናለን። በሥርዓተ ጸሎትም ሰፊሐ ዕድ (እጅን መዘርጋት) የሚ ታዘዘው ይህንን የመላእክት አሠረ ፍናት ለመከተል ነው።

የቃየን ምልክት ከመስቀል ምሳ ሌዎች አንዱ ነው። የዋህ ወንድ ሙን በግፍ የገደለ ቃየንን እግዚ አብሔር በፈረደበት ጊዜ ያገኘኝ ሁሉ ይገድለኛል ብሎ በተሰቀቀ ጊዜ ‹‹እግዚአብሔር ቃየንን ያገ ኘው ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገለት›› ይላል። (ዘፍ.፬፥፲፭) ይህ ምልክት ያገኙን ኢጋንንት ያሻቸውን እንዳያደርጉን የተሰጠን የትእምርተ መስቀል ምሳሌ ነው። ይህንን ምልክት ነቢዩ ሕዝቅኤልም በራእዩ ተመ ልክቶት ‹‹‹ሽማግሌውንና ጎበዙን ቆንጆ ይቱንም ሕፃናቱንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ› ሲል ሰማሁ›› ብሎ ተናግሯል። (ሕዝ.፱፥፮) ትእምርተ መስ ቀል እኛ ክርስቲያኖች ከኢጋንንት ፍላጻ የምንድንበት ምልክት ነውና እነዚህ ቀደምት ምልክቶች የመስቀሉ ምሳሌዎች ናቸው። ቅዱስ ዳዊትም ‹‹ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው ወዳጆችህ እንዲድኑ›› ብሎ የተናገረው ስለ መስቀልም ነው። (መዝ. ፶፱፥፬)

በታላላቆች አርእስተ አበው በኖኅ፣ በአብርሃም፣ በነ ይስሓቅና በነያዕቆብ ታሪክም ውስጥ የመስቀል ምሳሌዎች አሉ። ጻድቁ ኖኅ ከነቤተሰቡ ከጥፋት ውኃ የዳነባት ከእንጨት የተሠራች መርከብ ጌታ ዓለሙን ከመርገም ከፍዳ

ባዳነበት በመስቀሉ ይመሰላል፡፡ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ‹‹ወይቤሎ ለኖኅ አመ አይኅ ንሣእ እዕዕ ዘኪያነቅዝ ግበር ታቦተ በዘኮድኑን እስመ በገዘንቱ ዕዐ መስቀል በዘቦቱ ተሰቅለ እግዚእነ ናክብሮ በዘቦቱ ረከብነ መድኃኒተ በኃይለ መስቀሉ ንመ ውዕ ዐረነ›› ‹‹ጌታችን በተሰቀለበት በዚህ ዕዐ መስቀል ኃይል ጠላታችንን እናሸን ፋለን፡፡ ለኖኅ በጥፋት ጊዜ ከማይነቅዝ እንጨት የምትድንበትን መርከብ ሥራ ብሎታልና በእርሱ መድኃንን ያገኘንበትን መስቀሉን እናክብረው፡፡›› ብሏል፡፡ (ድጓ ዘመስቀል)

በአባታችን በአብርሃም ዘመን ደግሞ የመስቀል ምሳሌ የሆኑ ክስተቶች አሉ፡፡ ከነዚህ አንዱ አብርሃም እግዚአብሔርን ያገኘበት የመምሬ አድባር ዛፍ ነው፡፡ (ዘፍ.፲፰፥፩) አብርሃም በቀትር ጊዜ እግዚአብሔር በመምሬ አድባር ዛፍ ሥር የተገለጠለት ሲሆን እርሱም ይህን ታላቅ ራእይ ተመልክቶ እግዚአብሔርን በቤቱ አስተናግዶአል፡፡ አብርሃም እግዚአብሔርን በቀትር ያየበት ይህ ዛፍ ጌታችን በቀትር ስድስት ሰዓት የተሰቀለበት የመስቀሉ ምሳሌ ነው፡፡ በመስቀሉ ጥላ ስናርፍም ምሥጢራት ይገለጡልናል።

አብርሃም የሚወድደውን አንድ ልጁን ይሠዋለት ዘንድ እግዚአብሔር በጠየቀው ወቅትም ልጁን ይስሐቅን አሸክሞት የወጣው እንጨት ጌታችን ወደ ቀራንዮ ተሸክሞት የወጣው የመስቀሉ ምሳሌ ሲሆን ይስሐቅ በባሕርይው ሞት የሌለበት የመለኮት፣ በይስሐቅ ፈንታ የተሠዋው በግ ደግሞ መለኮት የተዋሐደው ደሙ በመስቀል ላይ የተቆረሰው የጌታችን ሥጋ ምሳሌ ነው፡፡

ወደ ያዕቆብ ታሪክ ስንመጣ ደግሞ መስቀሉን በያዕቆብ ራእይ በመሰላል ተመስሎ እናገኘዋለን፡፡ ያዕቆብ በተኛበት በሎዛ መንገድ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ደርሶ መላእክት ሲወጡና ሲወርዱበት ተመልክቶአል፡፡ ይህ ራእይ ለራሄ ትርጓሜ ያለው ሲሆን ለመስቀልም ይተረጎማል፡፡ መስቀል ከምድር እስከ ሰማይ የደረሰ መሰላል በላዩም ላይ ክርስቶስ የቆመበት መሸጋገሪያ ነው፡፡ ቅዱስ ጀሮም ስለዚሁ የያዕቆብ መሰላል በመስቀል ስለመመሰሉ ጉዳይ ከመላእክቱ መወጣት መውረድ ጋር አያይዞ ሲያብራራ ‹‹መስቀሉ በእርግጥም መሰላል ነው፤ ቅዱሳን መላእክት ከፍ ከፍ የሚሉበት ርኩሳን መላእክት (ሠራዊተ አጋንንት) የሚዋረዱበት፤ የምናምን ሰዎች ወደ እርሱ የምንደርስበት የማያምኑ አይሁ ግን ወደ ሲኦል የሚወርዱበት መሰላል ነው፡፡›› ብሏል፡፡ ሳይዛሪየስ (ሳዊሮስ) የተባለ አባት ደግሞ ‹‹ያዕቆብ የመሰላሉን ራእይ ያየው የሚወድዳት ራሔል ከማ ግኑቱ አስቀድሞ ነበር፡፡ ክርስቶስም ሙሽራይቱን ቤተ ክርስቲያንን ከመመስረቱ አስቀድሞ በመስቀል ተሰቀለ›› ብሏል፡፡

ቅዱስ ያዕቆብ የልጅ ልጆቹን ኤፍሬምና ምናሴን የባረከበት መንገድ ደግሞ የመስቀል ምልክት ለመባረኪያነት የሚውል ለመሆኑ እንደማስረጃ ሊጠቀስም የሚችል ነው፡፡ ልጁ ዮሴፍ ይባርክለት ዘንድ ኤፍሬምን በስተግራው በዙፋን ምናሴን በስተቀኙ አቆመለት፡ ያዕቆብ ግን በስተግራው ወዳለው የቀኝ እጁን በስተ ቀኝ ወዳለው የግራ እጁን በማድረግ እጆቹን አስተላለፈ፡፡ ይህንን ሲያደርግ በተመሳቀሉት እጆቹ ትእምርተ መስቀልን ሠርቶ ነበር። ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍ እጆቹን እንዲያስተካክልና ቀኝ እጁን በበኩር ልጁ ላይ እንዲያሳርፍ ቢጠይቀውም ነገሩ ምሥጢር ያለው ነውና በጀ አላውም፡፡ (ዘፍ.፲፰፥፲፬- ፲፱)

ወደ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ዘመን ስንመጣ ደግሞ ግብፃዊውን ገድሎ የመስቀል ምሳሌ ከቀበረበት ጥፃ ባሕር (የባሕር አሸዋ) ይጀምራል፡፡ ሙሴ ለእስራኤላዊው ወግኖ በጠንካራ ክንዱ መትቶ በአሸዋ የቀበረው ግብፃዊ ጌታ አዳምን ነፃ ለማውጣት በመስቀሉ ገድሎ የጣለው የዲያብሎስ ምሳሌ ሲሆን አሸዋው ደግሞ የመስቀል ምሳሌ ነው፡፡ (ዘጸ.፪.፲፪) እስራኤል ከግብፅ ባርነት ነፃ ይወጡ ዘንድ ተአምራት በተፈጸመበት በመጨረሻው ቀን ዋዜማ የፋሲካውን



በግ አርደው ጠብሰው ሲበሉም ወገቦቻቸውን እንዲታጠቁ፣ ጫማቸውን አድርገው በእጃቸው በትር እንዲይዙ መታዘዛቸው ለመስቀል ምሳሌ ነበር። ቅዱስ ዳዊት ‹‹በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል›› ብሎ መስቀልን በትር አለው። (ዘጸ.፲፪፥፲፩፤ መዝ.፳፫፥፬)

ሙሴ ብዙ ተአምራትን የፈጸመባት በትርም እንዲሁ የመስቀል ምሳሌ ነበረች። በዚህች በትር ሙሴ ባሕረ ኤርትራን ፈርኦንና ሠራዊቱንም በባሕሩ አሰጠማቸው። ጌታችንም በመስቀሉ እኛን ከኃጢአት ባሕር አሻግሮ ዲያብሎስንና ሠራዊቱን በባሕረ እሳት አስጥሚቸዋል። (ዘጸ.፲፬፥፳፰) ከዚህ በኋላ እስራኤል ወደ ማራ በመጡ ጊዜ የገጠማቸው ውኃ መራራ ነበረ። ውኃው ሊጠጡት የማይችሉት ሲሆን እግዚአብሔር ለሙሴ እንጨትን አሳየው፤ በውኃም ላይ በጣለው ጊዜ ውኃው ጣፈጠ። (ዘጸ. ፲፭፥፳፭) ሙሴ አንሥቶ ወደ ውኃው የጨመረው ውኃውን ያጣፈጠው ይህ እንጨት የመስቀሉ ምሳሌ ነው። በቅዱስ መስቀሉ በሚባረከውና ከጌታ ጎን ወደ ፈሰሰው ማየ ገቦ በሚለወጠው ውኃ ተጠምቀን መራራ ሕይወታችን ጣፋጭ ይሆናልና ነው።

ሙሴ አማሌቃውያንን ድል የነሳበት መንገድ ደግሞ ሌላው የመስቀል ጥላ ነው። አማሌቃውያንን ሊወጉ ሲወጡ ሙሴ ኢያሱን፦ ጎልማሶችን ምረጥልን ወጥተህም ከአማሌቅ ጋር ተዋጋ፤ እኔ ኀን የእግዚአብሔርን በትር በእጄ ይዤ በኮረብታው ራስ ላይ እቆማለሁ አለው።

ኢያሱም ሙሴ እንዳለው አደረገ ከአማሌቅም ጋር ተዋጋ ሙሴና አሮን ሆርም ወደ ኮረብታው ራስ ወጡ። እንዲህም ሆነ ሙሴ እጁን ባሳ ጊዜ እስራኤል ድል ያደርጉ ነበር። እጁንም ባወረደ ጊዜ አማ ሌቃውያን ድል ያደርጉ ነበር። የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር፤ ደንጋይም ወስዱ በበታቹም አኖሩ እርሱም ተቀመጠበት፤ አሮንና ሖርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር ፤ፀሐይም አስክትገባ ድረስ እጆቹ ጠነከሩ። ኢያሱም አማሌቅንና ሕዝቡን በሰይፍ ስለት አሸነፈ። (ዘጸ. ፲፯፥፰-፲፫) የሙሴ እጅ ሲዘረጋ ድል መገኘቱ የሙሴ እጅ ሲታጠፍ ሽንፈት መምጣቱ አጋጣሚ ነውን? አይደለም! ስንይዘው አጋንንትን ድል የምንነሳበት፤ ስንጥለው በአጋንንት ድል የምንነሳበት የመስቀሉ ምሳሌ እንጂ ነው።

ይህ የሙሴ ታሪክ እንደሙሴ እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ ጠላቶቹን በዚህ የመስቀል ምልክት ድል የነሳውን መስፍኑን ሶምሶንን ያስታውሰናል። (መሳ. ፲፮፥፳፱) ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ‹በዝንቱ ትእምርተ መስቀል ትመውዕ ፀረከ› (በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ታሸንፋለህ) የሚል ጽሑፍ ከመስቀል ምልክት ጋር እንደተመለከተ አጋንንትን ድል የምናሸንፍበት መሣሪያችን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ነው።

መስቀል በብሉይ ኪዳን ከተነገረለት ትንቢትና ምሳሌ በተጨማሪ ጌታችንም በመስቀል እንደሚሰቀል ራሱ ትንቢት ተናግሯል። ‹‹ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ›› በማለት። (ዮሐ.፲፪፥፴) ከምድር ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሲል በምን ዓይነት ሞት እንደሚሞት ሲያስረዳ ሲሆን ይኸውም መሰቀሉን ነው። ጌታችን ከፍ ብሎ በመሰቀሉ ሁላችንን ወደ እርሱ ስቦናል አቅርቦንማል። ከሰማይ ዝቅ ብሎ ከምድር ከፍ ብሎ መሰቀሉ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ መሆኑን ያስረዳል። እንዲሁም ከሰማይ ወደ ምድር የተጣሉትን አጋንንት በምድር ተመላልሶ መድረሻ እንዳሳጣቸው በአየራት ያሉትን ደግሞ ከምድር ከፍ ብሎ በመሰቀል ገሥሥአቸዋል።

‹‹እጆቼን ሰልፍ ያስተምራል››

መዝ.፻፵፫፥፩

እግዚአብሔር ከረቂቃን መናፍስት ጋር በምናደርገው ውጊያ ያስታጠቀን ኃይልና ለእጆቻችን ያስተማረው ሰልፍ አለ። ይኸውም በትእምርተ መስቀል ማማተብ ነው። በትእምርተ መስቀል ማማተብ የእኛ የክርስቲያኖች የነገር መጀመሪያ ነው። በሁለተኛው እና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበረው ጠርጡለስ በዘመኑ ስለነበረው የክርስቲያኖች ባህል ሲገልጽ ‹‹በድርጊቶቻችን ሁሉ፤ ስንገባና ስንወጣ፤ ልብሳችንን ከመልበሳችን በፊት፤ ከመታጠባችን በፊት፤ ከገበታ በፊት፤ በማታ ፋኖስ ስናበራ፤ ከመተኛታችንም በፊት፤ ለማንበብም ስንቀመጥ፤ በዕለት ዕለት ጥቃቅን ጉዳዮቻችን ሁሉ በትእምርተ መስቀል እናማትባለን።›› ብሏል።

ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ ደግሞ ‹‹ሶበ ንነውም ተወክለነ መስቀለ ወሶበ ንትነሣእ እምንዋምነ መስቀለ ንዜክር ወሶበ ንወፍር ውስተ ተግባርነ መስቀለ ንዜክር ወፈረነ

ሶበ ነአቱ በስብሐት ወበጸሎት ተወኪለነ መስቀለ ጽዙር» ‹‹በምንተኛ ጊዜ በመስቀል ታምነን ነው፤ ከእንቅልፋችን በተነሣን ጊዜ መስቀልን እናስባለን፤ ወደ ሥራችን በተሠማራን ጊዜ መስቀልን እናስባለን፤ ተሠማርተን በገባንም ጊዜ በምስጋናና በጸሎት እየታመንን መስቀልን እናስባለን›› ብሏል፡፡ (ድጓ ዘመስቀል)

በእርግጥም አባቶቻችን ከሁሉ ነገር በፊት በትእምርተ መስቀል እንድናማትብ ሥርዓት ሠርተውልናል፡፡ ምእመናን በእጃቸው ለማማተብ የማይችሉባቸው ሁኔታዎች ላይ ቢሆኑ እንኳን በዓይነ ኅሊናቸው የመስቀል ምልክት እንዲሠሩ ታዝዘዋል፡፡ አበው እንደሚሉት ከሰው ሚስት የደረሰ ኅልማሳ የሴቲቱ ባል ሲደርስበት የሚደነግጠውን ያህል ዲያቢሎስ ድል የተነሳበትን ትእምርተ መስቀል ሲያይ ክፉኛ ይደነግጣል፤ ይሸሸማል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ለትእምርተ መስቀል ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው መስቀል ከተራ ቁስነት አልፎ በክርስቶስ ደም የከበረ ስለሆነ ነው፡፡ ትእምርተ መስቀሉንም ስንመለከት በላዩ የተሰቀለውን አምላክና በመስቀሉ ያገኘነውን ሰላም እናስባለን፡፡

በሰሙነ ሕማማት በዕለተ አርብ ‹‹ለመስቀልከ ንሰግድ ኦ ሊቅነ ወለ ትንሣኤከ ቅድስት ንሴብሕ ኩልነ›› ‹‹መምህር ሆይ ለመስቀልህ እንሰግዳለን፤ ቅድስት ትንሣኤህንም ሁላችን እናከብራለን›› እያልን እንደምሰግድ ለጌታችን መስቀል የጸጋ ስግደት እናቀርባለን፡፡ ቅዱስ ዳዊት ‹እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን› በማለት ከተናገረላቸው ስፍራዎችም አንዱ ጌታ የተሰቀለበት መስቀሉ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ እንደጠቀሰው ደግሞ አባታችን ያዕቆብ ‹‹በዘንግ ጫፍ ተጠግቶ በእምነት መስገዱ› ለመስቀሉ የሚገባውን የጸጋ ስግደት ያስረዳል፡፡(ዕብ. ፲፩፥፲፩)

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ‹በፍጽም ወበእንግድዓ በአፃብዕ ወበመዝራዕት ትእምርተ መስቀል ጸዊረነ ናንሶሱ› ‹በግንባርና በደረት በጣትና በክንድ የመስቀሉን ምልክት ተሸክመን እንዞራለን፡፡› በማለት እንደተናገረ በኢትዮጵያውያን ምእመናን ዘንድ የመስቀል ፍቅርና የሚሰጠው ሥፍራ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ለኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሊቀ ጳጳስ የነበረው አባ ሰላማ ገና ወደዚህች ሀገር በመጣ ጊዜ ‹ምነው አትቆርቡም? ምነው ካህን የላችሁም?› ብሎ እንዲጠይቅ ያደረገው መስቀለ ክርስቶስን በግንባራቸው እስከመነቀስ የሚያደርስ እምነትን በኢትዮጵያውያን ላይ ስለተመለከተ ነበር፡፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የክርስቶስ መስቀል የወግ ዕቃና ጌጥ ነው፡፡ በከዋክብት ዘንድ ያበራውና ስማይን ያስጌጠው የክርስቶስ መስቀል ለኢትዮጵያውያን ምእመናን ጌጥ በመሆኑም በልብሳቸው ላይ የሚጠልፉት፣ በክንዳቸው የሚነቀሱት መስቀሉን ነበር፡፡ ‹ገብረ መስቀል› (የመስቀሉ ባሪያ) ኃይለ መስቀል (የመስቀሉ ኃይል) ‹ብርሃነ መስቀል› (የመስቀሉ ብርሃን፣ ‹መስቀል ክብራ› (መስቀል ክብሯ) የሚሉት መጠሪያ ስሞችም ለመላዕክ ያላቸውን ስፍራ የሚያሳይ ነበር፡፡

አንዳንዶች ለመስቀሉ የሚሰጠውን ክብር በመንቀፍ ‹እናንተ የተሰቀለውን ትታችሁ የተሰቀለበትን ታከብራላችሁ› ይላሉ፡፡ ያልተረዱት ግን መድኃኔዓለምን የእርሱ የሆኑትን እንደሚያከብር ነው፡፡ በዓለማችን በታሪክ የታወቁ ሰዎች የለበሱት ልብስ የተኙበት አልጋ እና የየዕለት ቁሳቁሶቻቸው ምን ያህል ክብር እንደሚሰጣቸውና በምን ያህል ዋጋ እንደሚሸጡ የየዕለት ዜናዎች ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም ታሪካዊ ቅርሶችን ለመመልከት የሚደረገው ትንቅንቅና ግፊያም አስገራሚ ነው፡፡ መስቀለ ክርስቶስ ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ነው፤ መስቀሉ ከሁሉ በላይ የአምላክ ሥጋ የተቆረሰበት ደሙ የፈሰሰበት ነው፡፡ በዚህ የከበረ በመሆኑም ለመስቀሉ የምንሰጠው አክብሮት ለአንድ ታሪካዊ ቅርስ የምንሰጠው ዓይነት አይደለም፡፡ መስቀሉ አይክበር፣ ተራ ዕቃ ነው ብሎ የሚያቃልል በመስቀሉ መጥፎ ትዝታ ያለው ዲያቢሎስ ብቻ ነው፡፡

ከእዚህ በላይ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበትን የነቢዩ ኤልያስን መጎናጸፊያ ተቀብሎ በነቢዩ ያደረ መንፈስ እጥፍ ድርብ ሆኖ አድሮበታል፡፡ ጌታ ደሙን ያፈሰሰበትን የመስቀሉን አርማ ስንይዝማ ምንኛ እንቀደስ ይሆን? በኦሪቱ ድንኳን የነበሩትን የእንስሳ መሥዋዕት ይሠዋባቸው የነበሩትን ንዋያተ ቅዱሳት እንኳን ‹‹የሚነካቸው ቅዱስ ይሆናል›› ተብሎ ተጽፎ ነበር፡፡ መድኃኔዓለም የዓለሙን ኃጢአት ለማስወገድ የተሠዋበት ይህን ክቡር መስቀል የነካማ ምንኛ ይቀደስ ይሆን?

የክርስቶስ መስቀል እውነተኛ ሥጋና ደሙ የተቆረሰበትና የፈሰሰበት መሆኑን የሚያምን ሰው ትእምርተ መስቀሉን (የመስቀሉን ምልክት) ያከብራል፡፡ በቀራንዮ በመስቀሉ ላይ የተፈጸመውን የሚያምንና የሚያከብር ሰው በቤተ ክርስቲያናችን ያለውን የመስቀሉን አምሳያ ያከብራል፡፡ ነገረ መስቀሉ ‹የእግዚአብሔር ኃይል› መሆኑን የምታውቅ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጉልላቷ ጀምሮ በግድግዳዎቿና በአልባሳቷ ሁሉ፣ በካህናቱ እጅም ታደርጋለች፡፡ በየጊዜውም ‹‹ጸልዩ ቅድመ መስቀል ኩልክሙ መሀይምናን እንዘ ትእኅዝዎ በየማን ወትክህድዎ ለሰይጣን እስመ ተቀደሰ በደመ መለኮት መድኅን›› ‹‹ምእመናን ሁላችሁ ሰይጣንን እየካዳችሁ (መስቀሉን) በቀኛችሁ ይዛችሁ በመስቀል ፊት ጸልዩ፤ በመለኮት ደም ተቀድሷልና፡፡›› እያለች ታውጃለች፡፡

የናሱ እባብ



ቀሲስ ክፍያለው ጥላሁን

ይህን የእባብ ምስል ሙሴ ሊሠራ የቻለበት ምክንያት፣ እስራኤል እግዚአብሔር ባወቀ ለአፍ የሚጥም፣ ለሰውነት የሚጠቅም ሰማያዊ ምግብ፣ እንኳን ተመግበውት ሲያዩት የሚያጠግብ በረዶ የመሰለ መና በነጻ ቢመግባቸው መናውን ንቀው ሌላ ነገር ስለተመኙ ፈርዶ ለማጥፋት የእባብ ሠራዊት ለቀቀባቸው።

እስራኤላውያንም ወደ ነቢዩ ሙሴ ቀርበው ‹‹ከእኛ ክፋትና ኃጢአት፤ ከእግዚአብሔርም ምሕረት አይለይምና ወደ እግዚአብሔር አመልክተህ አድነን›› አሉት። ነቢዩ ሙሴም የተለመደ ጸሎቱን ወደ ፈጣሪው አቀረበ። በዚህ ምክንያት የእባብ ምስል ሠርቶ እንዲሰቅለውና ያን አይተው እንዲድኑ አድርጓል። ይኸውም ምሳሌ አለው።

የእባብ ምስል የክርስቶስ፣ እስራኤልን የነደፈው እባብ የዲያብሎስ፣ የናሱ ብረት ከቆላ ከደጋ ተሰብስቦ እንደተሠራ ክርቶስም ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነውና /ዮሐ ፭፥፬/። የእባቡ አምሳል የተሠራው የናሱ ብረት ውስጡ ክፍት እንደሆነ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስም ኀዳጌ በቀል መሆኑን ያስረዳናል /ማቴ ፲፭፥፳፬/። ብረቱ ንጹሕ እንደሆነ ኢየሱስ ክርስቶስም ንጹሐ ባሕርይ ነው /ዮሐ ፰፥፵፮/ የናሱ ብረት ከእሳት ቢያገቡት በመዶሻ ቢቀጠቅጡት እንዲችል፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ጸዋትወ መከራን ታግሶ ተቀብሏል /ኢሳ ፶፫፥፬/ ።

የናሱ የእባብ አምሳል ተሰቅሎ እባብ የነደፋቸው ኃጢአተኞች እስራኤላዊያን አይተው እንደዳኑ፤ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስም ኃጢአት ሳይኖርበት በኃጢአተኛ አምሳል ተሰቅሎ በዲያብሎስ የኃጢአት መርዝ ተወግተው ወይም ተነድፈው በነፍስ በሥጋ የተጐዱትን አድኗል /ገላ ፫፥፲፫/ ።

የናሱ የእባብ ምስል መርዛማውን እባብ በመልክ እንጂ በባሕርይ እንደማይመስለው፤ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስም እኛ ኃጥአንን በመልክ እንጂ በኃጢአት ግብር አይመስለንም /ዕብ ፬፥፲፭/። በእባብ በተነደፉ ጊዜ የእባቡን ምስል መልኩን አይተው ድምፁን ሰምተው የዳኑት የሐዋርያት ምሳሌ ናቸው።

ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከዋለበት ውለው፣ ካደረበት አድረው ያደረገውን አስደናቂ ተአምራት አይተው ትምህርቱንም ከቃሉ ሰምተው አምላክነቱን አምነዋልና። «ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዐይኖቻችንም ያየነውን፣ የተመለከትነውንም በእጆቻችንም የዳሰስነውን እናወራለን፤ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክራለንም።» እንዲል /፩ዮሐ ፩፥፩/።

ዐይን ለሕይወት ብርሃን ናት። ማየት መቻል ትልቅ ጸጋ ነው፤ ማየት በራሱ ግን ዋጋ የለውም፤ ያዩትን ካላስተዋሉ በቀር «ከማስተዋል መንገድ የሚሳሳት ሰው በሙታን ጉባኤ ያርፋል» ተብሏልና /ምሳ ፳፩፥፲፮/። በባሕርይ አምላክነቱ ማመን እንጂ የክርስቶስን መልክ ማየት ድኅነት አይሆንም። በዘመኑ አይሁድ ሲያዩት፣ ሲሰሙት ይውሉ ነበር። ነገር ግን ድኅነት አልሆናቸውም። «የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም» /ዕብ ፬፥፪/። የእባቡን ምስል ድምፅ ሰምተው የዳኑት ከሐዋርያት ተምረው ያመኑ ምእመናን ምሳሌ ናቸው /ዮሐ ፫፥፲፬/።

ስለዚህ ዘለዓለማዊ ድኅነት ለማግኘት ክርስቶስ ሰው እንደሆነ፤ የባሕርይ አምላክ የሚዳስስ እንደሆነ የሚቀርበው የሌለ ረቂቅ፣ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ራሱ እግዚአብሔር፣ የዳዊት ልጅ መባሉን ብቻ ሳይሆን፤ የዳዊት ፈጣሪ መሆኑን አምነን ኅብስተ ወይን ባልነው ጊዜ በመልከ ጼድቅ ዘንድ፤ ወዳጅ ባልነው ጊዜ ደግሞ በአብርሃም ዘንድ እንደምገኝ ከልብ አምነን የአብርሃምን እምነት፣ የኢዮብን ትዕግሥት፣ የዮሴፍን ንጽሕና፣ የቅዱሳን ሐዋርያትን ፍጹምነትና መንኖ ጥሪት፣ የኤልያስን መንፈሳዊ ቅንዓት ይዘን መስቀሉን እስከ መጨረሻ አንግበን የተዘጋጀልንን ርስተ መንግሥተ ሰማያት ለመውረስ አምላክ ቅዱሳን ይርዳን።

ከደመራው በፊት...

ከገጽ ፱ የዞረ

መሆኗን የሚመሰክሩ በመሆናቸው ነው። ‹‹ይኼማ ሀገር መከፋፈል ነው›› ይላሉ የሚደራጁ መምሪያው ምክትል ሐላፊ መምህር ዕንቁ ባሕርይ ተክስተ በውቅቱ ተነሥቶ የነበረውን የተቃውሞ አሳብ ሲያስታውሱ። ‹‹ብዙ ሰዎች በልዩ ልዩ ቋንቋዎች መዝሙር መዘመሩን ሲሰሙ ‹ይኼማ ሀገር መከፋፈል ነው› ብለው ተቃውመው ነበር፤ ነገሩ ብዙ ውዝግብ ቢያስነሣም በቅዱስ ፓትርያርኩ አርቆ አስተዋይነት ጉዳዩ ይሁንታ አግኝቶ ለጸና ችሏል። ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ናት፣ በዓሉም የሁሉም ነው። ‹አኔ አፍ በፈታሁበት ቋንቋዬ እየዘመርኩ ሌላው በራሱ ቋንቋ አይዘምር› የሚል ሰው ክርስትና ያልገባው ነው። ለወደፊቱም በሌሎች ቋንቋዎችም ያሬዳዊ መዝሙሮች እንዲስፋፉ እንሠራለን።›› ብለዋል።

መራክስ በመስቀሎታ ቀተረው
በመስቀሮታ የሰብትክ ሰላመታ ሀበው
(ጉራጊኛ)

በዚህ ታላቅ ክብረ በዓል ከሁሉም መዘምራን ይልቅ ጎልቶ የሚሰማ፣ መን ፈሳዊ ጆሮ ላላቸው እጅግ የሚመስጥ አንድ ድምፅ አልባ መዝሙር የሚያሰ ሙት በምስክየ ጎዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ተምሮ ማስተማር ሰንበት ትም ህርት ቤት የሚሰባሰቡት መስማት የተ ሳናቸው መዘምራን ናቸው። እስከ ሁለት ሙዩ አምሳ የሚደርሱት ወጣቶች በለዎች ጆሮ የማይሰማ በእግዚአብሔር ፊት ግን ትልቅ ሥፍራ ያለውን ገጦማዬቸውን በምልክት ቋንቋ ያቀርባሉ። መምህር ዕንቁባሕርይ ስለእዝህ ወጣቶች ሲገልጹ ‹‹አካል ጉዳተኞችም የቤተ ክርስቲያኒቱ አካል ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ለእነርሱ ትልቅ ሥፍራ አላት። እኔን ያስተማ ሩኝን የኔታ ሄኖክን ጨምሮ ከታላላቅ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችም ይገኙበታል።» ብለዋል።

ማስቃላይቶ ፖኦክ አላናይታስ ኡባስ
ጦላ ኬታን ሙል ቂዲ ቤቴስ
ላሮታካ ኢሜስ መድኃኔዓለሚ
መስቀላይ ማዬስ አማኒራ አላስ
/ጋሞኛ/

ከ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. ጀምሮ መስቀል ክብረ በዓል ድምቀት አካል የሆኑት ለላ ተሳታፊዎች ደግሞ የጋሞ ብሔረሰብ አባላት ናቸው። በሸሮሜዳ አካባቢ የሚ ኖሩትና በሐመረ ኖኅ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ የሚገ ኙት እዝህ ምእመናን ለዓመታት ተመ ልካች አጥተው በቋንቋቸው የሚያስተ ምራቸው አጥተው በቋንቋቸው ለሚያስተ ምሯቸው መናፍቃን ተጋልጠው ነበር። ኦርቶዶክሳዊያን ከሆኑትም መካከል ትበኺ ያጡት ብዙ ለመሆናቸው ኦርቶዶክ ሳዊ ሆኖ እስከ ዐሥራ አራት ዓመቱ ድረስ ሳይጠመቅ የቆየው አዳጊ ወጣት ቋሚ ምስክር ነበር። ከዚህም በኋላ የማ ደራጃ መምሪያው ሐላፊዎች ባደረጉት ጥረት ያብሔረሰቡን አባላት ባህል ባገናዘበ መንገድ ዘወትር ሰኞ ቀን መንፈሳዊ ጉባኤ ተጀመረላቸው። ይህንንም ተከትሎ በትድስት ሥላሴ፣ በሎስቋም ማርያም፣ በወይብላ ማርያም እና በገነተ ኢየሱስ አብያተ ክርስቲያናት ለብሔረሰቡ አባላት የሚደረጉት ጉባኤያት ቀጠሉ። እነዚህ ምእመናን በአሀጉ ሰዓት ሀያ ሁለት የሚደርሱ ማኅበራት ያሏቸው ሲሆን በመስቀል አደባባይ በየዓመቱ ከጅያ እስከ ጂያ በሚደርስ ቁጥር በግእዝና በቋንቋቸው ገጦማሬን ያቀርባሉ።

Cross is light for all the world
Base of the chuch /3/ it is base of the chuch
/እንግሊዝኛ/

ወጣቶች የቤተ ክርስቲያኒቱ ተስፋዎች እንደመሆናቸው ያላቸው ድርሻ ትልቅ ነው። ‹‹በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዛህ ናት ቁጥር የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ቁጥር ይበልጣል›› ያሉት መም

ወደ ገጽ ፴፫ ዞሯል

የጥያቄዎች ጥያቄ

ዲ/ን ማለደ ዋስይሁን

የአምልኮ ባዕድ ስምን ትፈጽማላችሁ?

እኔ ክርስቲያን ነኝ፣ የማምነውም በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ባዕድ አምልኮን ይከለክላል፤ ማንኛውንም ቅርጽና ሥዕልን በሕይወታችን ውስጥ እንዳንጠቀም ታዘናል፤ ታዲያ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መስቀል፣ ታቦት ቀርጸ፣ የመላእክትን፣ የማርያምን እና የሌሎችንም ሥዕል ሠርቶ የሚሰግደው ለምንድነው? ይህንን በመቃወማቸው ለምን ፕሮቴስታንቶችን ትቃወማላችሁ?

አደፍርስ በየነ
ከአዲስ አበባ

መልስ፦

ጠያቂያችን እርስዎ ሃይማኖቴ መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ ያደርጋል እንዳሉት የኦርቶዶክሳውያንም ሃይማኖት መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ የታወቀ ነው። መጽሐፍ ቅዱስንም የእግዚአብሔር መጽሐፍ መሆኑን ከሌሎች የግኖስቲኮች የተዛቡ መጻሕፍት በጉባኤ ለይተው፣ ቆጥረው ሰፍረው የሰጡን ኦርቶዶክሳውያን ጉባኤዎችና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን ናቸው። ጥያቄ ማንሣት የሚከለከል ባይሆንም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የሌሎችን አካላት /ቤተእምነቶች/ የሃይማኖት መሠረት ለመመርመር መን ፈሳዊ፣ ታሪካዊና ሞራላዊ መሠረት ያለው እንጂ እርሱ በሌሎች የሚመረመር አይደለም።

በመሆኑም «በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምስል ለአንተ አምላክ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» የሚለውን ትእዛዝ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አበክራ ታስተምራለች። /ዘጸ. ፳፬÷፭/ ጣዖትንም የሚያመልኩትን ትቃወማለች። ይህንን እያደረገች ያለችን ቤተክርስቲያን በጣዖት አምልኮ መክሰስ የአምልኮን ምንነት ወይም የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በግልጽና በጥልቅ ካለመረዳት ወይም ሆን ተብሎ ሰዎችን ወደግላችን ሥጋዊና ቡድናዊ ዓላማ ለመሳብ የምንጠቀምበት ሐሳብ ነው።

ጠያቂያቸን ጣዖት አምልኮ እንደሆነ የጠቀሱት ቅዱሳት ሥዕላትን፣ መስቀልና ታቦትን በቤተክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ መጠቀምን ነው። ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉ የተሣሉና የተቀረጹ ንዋየ ቅድሳትን እግዚአብሔርን በማምለክ ሥርዓታችን ውስጥ እንዴት መጠቀም እንዳለብን የያዘውን የማይታበል ቃል አለመረዳት፤ መካድ ወይም አላግባብ መተርጎም የሚያስከትለው ስሕተት ነው። ቤተክርስቲያን ሠራኢና መጋቢ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ መቼም መች የምትመሰክረው ሃይማኖታዊ ነው። ስለዚህ የሚመለክ አምላክ /እግዚአብሔር/ ብቻ በመሆኑ እውነተኛውን ጌታ እግዚአብሔርን ታመልካለች። በአምልኮ ውስጥ ደግሞ ሥርዓተ አምልኮ አለ። ይህ በአዚያችም በሐዋርያትም ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚዘጋጅ ነው። ሌላው ጠያቂያችን ያልተገነዘብ ከው ወሳኝ ነጥብ በአምልኮና በአምልኮ ሥርዓት መካከል ያለውን ልዩነት ነው። አምልኮ ፍጥረታቱን ሁሉ ለፈጠረ ብቻ ውን ለሚኖር አምላክ በሃይማኖት የምንገዛው መገዛት ሲሆን፤ ሥርዓተ አምልኮ ደግሞ ይህ መገዛታችን የሚገለ ጥበት አፈጻጸም ነው። ይህም ይትባህሉን፣ ሰዓቱን፣ ቦታውን፣ ንዋያቱን፣ መሥዋዕቱን ወዘተ ያካትታል። ሁለቱን መረዳት ያልቻሉ ወይም ለመረዳት ዝግጁ ያልሆኑ ወገኖች ደግሞ ኦርቶዶክሳውያንን አማል ክቶቻቸው ብዙ ከተባሉ አሕዛብ ጋር ሲፈርጁ ስለሚገኙ ምስክርነቱ የሐሰት ይሆናል። ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የሃይማኖቴ መሠረት ነው ከሚል ወገን አይጠበቅም። ታቦትን መስቀልንና ሥዕልን በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ መጠቀምን የኦርቶዶክሳውያን ስሕተት አድርገህ ወስደኸዋል፤ በልዩ ልዩ ምክንያት ተከፋፈሉ እንጂ ሐዋርያዊ ውርስ ባላቸው አብያተክርስቲያናት ሁሉ ይህ ሥርዓት እንዳለ ከታሪክ ድርሳናትና ዛሬም እየሆነ ካለው ማየት ትችላለህ።

ውድ ጠያቂያችን እርስዎ መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ እንደሆኑ ስለነገርከን በወንጌልም ጌታችን መጻሕፍትን መርምሩ እንዳለ /ዮሐ. ፭÷፴፱/ መጽሐፍ ቅዱስ የተቀረጹ ወይም የተሣሉ ወይም የተጻፉ ነገሮች እርሱ በሚመለክበት ሥርዓተ አምልኮ ውስጥ እስራኤል እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የሰጠውን ሥርዓት እናስታውስም። መቼም ይህ የኦሪት ነው ተብሎ ሊገፋ አይችልም፤ በኦሪትም በወንጌልም ሕግን የሠራ ያው አንዱ እግዚአብሔር ነውና።

በዘጸአት ምዕራፍ ፳፭ ላይ «የማናቸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ» ብሎ የተናገረ እግዚአብሔር በምዕራፍ ፳፭ ላይ ደግሞ «ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሥራ፤ በስርየት መክደኛውም ላይ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ፤ ከስርየት መክደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሠራዋለህ፤ ሁለቱን ኪሩቤል እንዲሁ በሁለቱም ወገን ታደርጋቸዋለህ፤ ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደላይ ይዘረጋሉ፤ የስርየት መክደኛንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ፤ ፊታቸውም እርስ በእርሱ ይተያያል፤ የኪሩቤል ፊቶቻቸው ወደ ስርየት መክደኛው ይሁን» /ዘፀ. ፳፭÷፲፰-፳/ ይለናል። እነዚህን ሁለት ትእዛዛት የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ነው። ውድ ጠያቂያችን ይህንን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ስታነብ ምን ይሰማሃል። ምስጋና ይግባውና ትእዛዛቱን የሰጠ ጌታችን ተሳሳተ ልንል እንችላለን ወይስ በራሱ ቤተ መቅደስ ውስጥ አምልኮተ ባዕዳንን አጸና እንላለን? ይህ በእውነት ከእርሱ የራቀ ነው። አንተ ባነሣሃቸው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ ስላሉ ሥዕልና ቅርጾች በተመለከተም እንዲሁ ማሰብ

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል

ችሁ መልስ

ጥያቄ መስቀሉን ስታከብሩ የተሰቀለውን ለምን ትረሳላችሁ?

ብዙ አርቶዶክሳውያን የመስቀል ቅርጽ በጣታቸው በማማተብ ወይም የተቀረጸ መስቀልን በአንገታቸው በማድረግ ሲያከ በሩት እናያለን። ይህ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ አይደለም። ይህን ማድረግ ታዲያ ለምን ያስፈልጋል? ትእምርተ መስቀል ክርስቶስን የሚያስረሳ በእርሱም ፋንታ እያከበራችሁት ይመስለኛል፤ ይህ ለምን ይሆናል?

ትዕግስቱ
ከአዲስ አበባ

መልስ ፦

ውድ ጠያቂያችን ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ የሰው ልጆች ን ማዳኑን የምናስብበት ምልክት ነው። ክርስቶስን ማሰብ ደግሞ የሚገባ ነው። ራሱ ጌታችን ይህንን ባደረጋችሁ ጊዜ ሞቴን መከራዬን ታስባላችሁ። ብሎናል እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን «በወንጌል እንደ ምሰብከው ከሙታን ተለይቶ የተነሣ ውን ከዳዊት ዘር የሆነውን ኢየሱስ ክር ስቶስን አስበው» ብሎታል /፪ጢሞ፪፡፰/። ክርስቶስን ደግሞ በነገር ሁሉ ማሰብ የሚገባ ነው። ለእርሱ ምስጋና ይግባውና እርሱ ካደረገው ከተናገረው ስለሰው ልጆችም ከሆነውም ሁሉ እርሱ ደስ ለማይሰኝባቸው ነገሮች ምልክት የሆኑ ነገሮች የሉም። ከተናገረው፣ ካደረገውም በላይ ስለኛ የሆነው፤ ይልቁንም ስለኛ የተቀበለው መከራ፣ ውርደትና ሞት ግን ዋጋው ከምንም በላይ ነው። ይህ ለእርሱ ጥበቡም ኃይሉም ፍቅሩም ትሕትናውም የተገለጠበት ነው። «ስለወዳጆቹ ሕይወ ቱን አሳልፎ የሚሰጥ ያለ እንደሆነ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም።» /ዮሐ. ፲፭፡፲፫/ ብሎ ጌታችን እንደተናገረ እኛ ወዳጆቹ ሳንሆን ጠላቶቹ ሆነን ሳለ ስለኛ ቤዛ አድርጎ ራሱን ያቀረበበት የመስቀል ሞት ከምንም በላይ የክርስትና ሕይወት መሠ ረት ነው።

የሃይማኖታችን ማእከል ደግሞ እርሱ ከሆነ ምልክታችንም ያንን የሚያስታው ሰን የመስቀል ምልክት ሊሆን እንደሚገ ባው ቤተክርስቲያን ታምናለች። ክርስቶ ስንና የማዳን ሥራውን የምናስታውስበት ምልክት ደግሞ የቤተክርስቲያንም ምል ክት ነው፤ እሱ ጌታዋ፣ ራሷ፣ እረኛዋ፣ ተስፋዋ፣ ጠባቂዋ ኃይሏ ነውና።

መስቀል ክርስቶስንና ክርስቶስ ለሰ ዎች ያደረገውን የፍቅር ሥራ ከማስታ ወሱም ሌላ የምንማርበት፤ የምናስተም ርበት ነው። በትእምርተ መስቀል የተ ሰፋውን ቃል /በነብያት የተነገረው ትን ቢት፣ የተመሰለውን ምሳሌ/ መፈጸሙን፤ የክርስቶስን የማዳን ጥበብና ምስጢር የምናስተምርበት ነው።

ትእምርተ መስቀል ጥሪም ነው። ክርስቲያኖች ክርስቶስን በማመን በክር ስቶስ ስም ስለእውነት መከራን መቀበ ልን ሳይሰቀቁ በጽናት እንዲቆሙ የሚቀርብ የሃይማኖት ጥሪ ነው።

ትእምርተ መስቀል ምስክርነትም ነው። ጌታችን ለሐዋርያቱ «ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» እንዳለ በትእምርተ መስቀልም የሰማዕትነት /የምስክርነት/ ተግባርን እን ፈጽማለን። ምስክርነት ደግሞ ከፍተኛው ሐዋርያዊ አገልግሎት ነው። በመሆኑም ክርስቲያኖች በካዱ በአይሁድ ፊት፣ በማያምኑም አረማውያን ፊት በክርስቶስ መስቀል፣ ሞትና ትንሣኤ እንደማያፍ ሩበት ይመሰክራሉ። ይህ ደግሞ ያለማፈር እንድንፈጽመው ጌታችን «በሰው ፊት የሚመሰክርልኝን የሰው ልጅ በእግዚ አብሔር መላእክቱ ፊት ይመሰክርለ ታል» ብሎ የተናገረን ተግባር እንጂ የግብዝነት አካሔድ አይደለም/ሉቃ ፲ ፪፡፰/። በተለይ በዘመኑ ሐዋርያት አይ ሁድ «እኛ ገርፈን በሰቀልነው ያምናሉ» እያሉ ይዘብቱ ስለነበር፤ «እርሱ ሞቷል እንጂ አልተነሣም» የሚሉ፤ መስቀሉንም «እርሱ የተዋረደበት መቅጫ ነው» የሚሉ፤ እርሱን ዙፋን አድርጎ የሰው ልጆችን ሁሉ ያጸነበት መሆኑን የሚያምኑ፤ «በሞት ሞት አይሽነፍም» የሚሉ ዘባቾችና መስተሳልቃን ስለነበሩ የክርስቶስን መከራና ሞት ማሰብ፤ በዚያም መዳና ችንን ማመን ሞኝነት የሚመመስላቸው ነበሩ። በዚያ የጸኑ ክርስቲያኖችንም ያሳድጹ ነበር። ስለዚህ በመስቀሉ ስላ ገኘነው ሕይወት በግልጽ መመስከር አስፈላጊ ነው። ለዚያም ነው ቅዱስ ጳውሎስ «የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚ አብሔር ኃይል ነው» ያለው /፩፡፲፰/። በዚህ ቃሉ መሠረት ስለ ነገረ መስቀሉ መመስከር የሰማዕትነት ፍጻሜ ነበር። ስለዚህ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ያላቸውን ፍጹም ፍቅር አይሁድና ተረፈ አይሁድ የሚጠሉትን፣ ነገረ መስቀሉን በሰዎች ሁሉ ፊት ሳናፍር ልንመሰክር የምንችልበትን ትእምርተ መስቀል መጠ ቀማቸው የሚያስነቅፍ ሊሆን አይች ልም። ለዚህም ነው የዓለም ክርስቲያ ኖች ከዕፅ ወይም ከወርቅ ወይም ከብር የመስቀል ቅርጽ ሠርተው ክርስቶስን በማያምኑ ወገኖች ፊት የሚቆሙት።

በተለይ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሁሉም ሊያየው በሚችል መልክ መስቀ ልን በአንገታቸው በማንጠልጠል፣ በግን ባርና በእጆቻቸው በመሃቀስ፣ በልብሶቻቸው ላይ በመጥለፍ፣ በጣቶቻቸውም በማማተብ፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቱ አድኖናል፣ በዚያም አናፍርም እያሉ በምስክርነት ሕይ ወት ውስጥ ጸንተው የምናገኛቸው። በተናጠል ብቻ ሳይሆን ቢጋራም ደመራን በመሰሉ የመስቀል በዓላት እንደ ሐዋር ያው «አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ፣ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፣ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካ ለን» እያሉ በአደባባይ ያከብራሉ /፩ቆሮ. ፩፡፳፪/። ስለዚህ ትእምርተ መስቀልም ይሁን የመስቀል በዓላት ለዚህ ዓይነት ሃይማኖታዊ ዓላማ ሚና ያላቸው በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም ማለት አይቻልም።

ትእምርትን ወይም ምልክትን መጠ ቀምም በራሱ የሚያስነቅፍ አይደለም።

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል

የአምልኮ ባዕድ ...



ይገባ ነበር። ይህ ግን የሚመለከው እርሱ ሆኖ በቤቱ አምልኮ ውስጥ ስለሚፈጸመው ሥርዓት በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ የገለጸው ሥርዓት ነው። ለእግዚአብሔር ስለሚቀርብ መባዕ፣ ስለቃልኪዳኑ ታቦት፣ ኅብስተ ገጹ ስለሚቀመጥበት ገበታ፣ ስለመቅረዙ፣ ስለተቀደሰው ድንኳን፣ ስለ መሠውያው አሠራር፣ ስለልብሰ ተክህኖ፣ ስለክህነት፣ ስለወርቅ ማዕጠንት፣ መና ስላለባት የወርቅ መሶብ ወዘተ በተና ገረበት የሥርዓተ አምልኮ ሕግጋት ውስጥ ማስተስረያውን ስለሚጋርዱ የክብር ኪሩቤልም ተናግሯል። በዚህም ሕግ መሠረት ሙሴ ቤተ እግዚአብሔርን ሠርቷል። መቅደስ ትሠራልኛለህ፤ በመካከላቸው አድራለሁ፤ በተራራው እንዳሳየሁህ ሁሉ እንደማደረው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ ለእኔ ትሠራለህ እንደተባለ።

ውድ ጠያቂያችን አስተውል፤ ይህ በየትኛውም መንገድ ባዕድ አምልኮ አል ተባለም ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚህ ነገር በጻፈበት የዕብራውያን መልእክቱ ሥርዓቱ፣ ዝግጅቱም እንዲህ ነበር አለ እንጂ ጣዖት አምልኮ ነው የሚል የውግዘት ቃልን አላሰማም። ይህ ምሳሌያዊ፣ የሥጋ እና ጥላ የተባለው ሥርዓት አማናዊ መንፈሳዊ እና አካል በተባለ በአዲስ ኪዳን ሥርዓት መተካቱን ነገረን እንጂ አምልኮተ ጣዖት እንደነበረ፣ በአምልኮተ እግዚአብሔርም እንደተተካ አልተናገረም /ዕብ ፱÷፩-፭/።

ይኸው ሥርዓት ንጉሥ ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ ውስጥም እናገኘዋለን። «ክንፎቻቸውንም ዘርግተው የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ታቦት የሸፈኑትን የኪሩቤልን የወርቅ ሰረገላ ምሳሌ አሳየው፤ ዕውቀት እንደ ተሰጠው የእግዚአብሔርን ቤት ይሠራ ዘንድ ዳዊት በእግዚአብሔር እጅ የተጻፈውን ለልጁ ለሰሎሞን ሰጠው ተብሎ እንደ ተጻፈ» /፩ዜና. ፳፰-፴/ ውድ ጠያቂያችን በእግዚአብሔር እጅ ተብሎ የተጻፈውን ልብ በል፤ ይኸው ሥርዓት ነቢዩ ሕዝቅኤል በራእዩ ባየው ቤተመቅደስ ውስጥም እነዚህን ኪሩቤል አይቶ ነበር /ሕዝ ፵፩÷፲፰/።

ውድ ጠያቂያችን ከዚሁጋ በተያያዘ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ሌላ ታሪክ እናስታውስዎ፤ እስራኤል በምድረበዳ እያሉ በበደላቸው ምክንያት ከመጣባቸው በመርዘኛ እባቦች ተነድፎ የመሞት መቅሰፍት እንዲድኑ ራሱ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሥርዓት አስተውል፤ «እግዚአብሔርም ሙሴን የናስ እባብን ሥርተህ በዓላማ ላይ ስቀል እባቡም ሰውን ቢነድፍ የተነደፈው ሁሉ ይመልከተው፤ ይድናልም አለው፤» ለዚህ የፈውስ ሥርዓት የታዘዘው የናስ እባብ ቅርጽ ሲሆን ዓላማው ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚፈጸምበት ተግባር ማስፈጸሚያ ሆኖ የገባ እንጂ በራሱ በፈጣሪ ፈንታ እንዲመለክ የሰጠው ቅርጽ ወይም ሥዕል አይደለም /ዘኍ ፳፩÷፩፱/።

«ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ የሰው ልጅ እን ዲሁ ይሰቀል ዘንድ አለው ያመነበት ሁሉ ለዘላለም ሕያው ሆኖ እንዲኖር እንጂ እንዳይጠፋ» /ዮሐ. ፫÷፲፬/

ተብሎ ስለተጻፈለት ስለ ጌታችን መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕለ ስቅለት በሥር ዓተ አምልኮ ውስጥ ስለሚኖረው ድርሻ ምን ልንል እንችላለን። ይህ የናስ እባብ የተቀረጸ ምስል ሆኖ ሳለ እንደጌጥ ሳይሆን በዚያ ፈውስ በሚደረግበት በእግዚአብሔር ሥርዓት ውስጥ አንድ አካል ሆኖ እንደገባ እናስተውል። ሁልጊዜ እያሰብነው እንድንኖር የታዘዝነውን የክርስቶስን የማዳን ሥራ ሊያስተምሩን፣ ሊያስታውሱን የሚችሉ ቅዱሳት ሥዕላትን እግዚአብሔርን በማምለክ ሥርዓት ውስጥ መጠቀም እንዴት አምልኮ ባዕድ ሊባል ይችላል? የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አክብረው አምልኮ ባዕድን የተቃወሙ፤ እውነተኛ ምስክሮቹ ሆነው ያለፉ ቅዱሳንን በቅዱሳት ሥዕላት መዘከር ፈለጋቸውን እንድንከተል የሚያበረታታ፤ ያንንም በማሰባችን በረከትን እንድናገኝ በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ የሚረዱን ቅዱሳት ንዋያት እንጂ ጣዖት ሊባሉ አይችሉም። ስለታቦትም መስዋዕታችን ለዓለም ድኅነት ራሱን የሰጠ የጌታችን ሥጋና ደም በመሆኑ እርሱን የምናከብርበት መሠዊያ ደግሞ አለን። ይህን መሠዊያ በራሱ በእግዚአብሔር ስም አክብረን በፊቱም በሰማያት ላለ አምላካችን መስገዳችን እንዴት አምልኮ ባዕድ ይባላል? ይህ ከራሱ ከእግዚአብሔር በላይ ለአምልኮቱ አቀናለሁ እንደ ማለት ነው።

ምናልባትም ጠያቂያችን ትቃወሚ ቸዋላችሁ ያልካቸው ተቃዋሚዎች ራሳ ቸው በቤቶቻቸው ግድግዳ ወይም እና ነበዋለን በሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ዎች ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ የሚገልጹ ሥዕላትን ልታይ ትችላለህ።

ወደ ገጽ ፳ ዞሯል

መስቀሉን ስታከብሩ... ከገጽ ፲፯ የዞረ

ምልክትን ለመታሰቢያም ለምስክርነትም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲጠቀም እንደኖረ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ እናገኛለን። «ኢያሱ ከየነገዱ አንድ አንድ ሰው ከእስራኤል ልጆች የታወቁትን ዐሥራ ሁለት ሰዎች ጠራ። እያሱም አላቸው፤ በእኔና በአግዚአብሔር ፊት ወደ ዮርዳኖስ መካከል ዕለፉ፤ እያን ዳንዱ ሰው በዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ቁጥር በትከሻው ላይ አንድ አንድ ድንጋይ ከዚያ ይሸከም፤ እነዚህ ምልክት ይሆኑላ ችኋል፤ ልጅህ ነገ እነዚህ ድንጋዮች ምንድናቸው ብሎ በጠየቀህ ጊዜ ልጅህን እንዲህ ትለዋለህ፤ አንተ በምድር ሁሉ ጌታ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት ስንሻገር የዮርዳኖስ ወንዝ ስለደረቀ ነው፤ እነዚህ ድንጋዮች ለእስራኤል ልጆች ለዘላለም መታሰቢያ ይሆናሉ» የሚል ቃል ተጽፏል /ኢያ፬፡፬/። ይህ ምልክት የእግዚአብሔርን ሥራና ክብር ያስታውሳል እንጂ ሊያስረሳ የሚችልበት ምንም እድል የለም። እስራኤል ዮርዳኖስን የተሻገሩበት የምስክርነት ምልክት እንዲህ ዋጋ ካለው እኛ ከባህረ እሳት ወደ ቀደመ ርስታችን ገነት መንግሥተ ሰማያት የተሻገርንበት የክርስቶስ መስቀል ምልክትማ ምን ያህል ዋጋና ክብር ይኖረው!

በኢያሪኮ ስለነበረችው ረዓብም ስናስብ «እኔ ለእናንተ ቸርነት እንዳደርግሁ እናንተ ደግሞ ለአባቴ ቤት ቸርነት እንድታደርጉ በእውነት ምልክት ስጡኝ» ማለቷን በመጽሐፍ ተጽፎ እናነባለን። እያሱ የላካቸው ጎልማሶችም «እነሆ እኛ ወደ ሀገሩ በገባን ጊዜ ይህን ቀይ ፈትል እኛን ባወረድሽበት መስኮት በኩል እሰሪው» ብለዋት ነበር። «ኢያሱም ምድሪቱን የሰለሉ ሁለቱን ሰዎች ወደ ዘማዪቱ ቤት ግቡ፤ ከዚያም ሴቲቱንና ያላትን ሁሉ እንደማላችሁላት አውጡ» አላቸው /ኢያ. ፪፡፲፪/። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለረዓብ የሰጣት ምልክት እርሷንና ያላትንም ሁሉ ለማዳን የበቃ እንደሆነ ካየን ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ምልክትማ ምእመናንን አንድ በማድረግ ድኅነታችንንም ለማሰብ፣ ለመመስከር እንዴት የከበረ አይሆን!

በታሪክ እንደሚታወቀው ከንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመን በፊት ክርስቲያኖች የመስቀልን ምልክት ማሳየት ወይም መጠቀም አይፈቀድላቸውም ነበር። ያንን ሲ ያደርግ የተገኘም በመስቀል ተሰቅሎ ይቀጣ ነበር። እስከዚያም ዘመን ድረስ መስቀል መቅጫ ሆኖ ያገለግል ነበር። ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነበት እ. አ. አ. ከ፫፻፴፯ ዓ.ም. ጀምሮ ግን ክርስቲያኖች የመስቀልን ምልክት በግልጽ ለምስክርነት የመጠቀም ነጻነት አግኝተዋል። ከዚያን ጊዜም ጀምሮ መስቀል የመቅጫ መሣሪያ መሆኑ ቀረ። በመሆኑም ቅዱስ ጳውሎስ «ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ» የሚለውን ቃሉን እያሰቡ ትእምርተ መስቀልን ያለፍርሃት፣ ያለ ሐፍረት ይጠቀማሉ/ገላ ፮፡፲፬/።

ትእምርት ሐሳብን፣ ድርጊትን፣ ፈቃድን የሚያሳይ የሚመስክር ነው። በወንጌል እንዲሁም ጌታችን ለፍርድ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ «የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል» ተብሎ ተጽፏል /ማቴ፳፬፡፴/። ሊቃውንት የሰው ልጅ ምልክት የተባለው መስቀል እንደሆነ ያስተምራሉ። በመሆኑም ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ ለሰዎች የሠራውን መልካም ነገር የሚያስታውስ እንጂ የሚያስረሳ የሚሆንበት ምንም እድል የለም።

መስቀል መከበርም ይገባዋል። የመስቀሉን ምልክት ሰዎች ሲያዩ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን የፍቅር ሥራ በሚያዩት ሰዎች ልብ ስለሚሥል ከፉን ሐሳብ ለማራቅ፣ መልካሙንም ለማድረግ ኃይል ይሆናል። ርኩሳን መናፍስትም የዲያብሎስ ሥልጣኔ የተሻረው ክርስቶስ በመስቀሉ ለሰዎች በሠራው ሥራ መሆኑን ስለሚያውቁ ባዩት ቁጥር ይሸሻሉ፣ ይሸነፋሉ፣ ይቃጠላሉም። ያንን በሚያሳዩ፣ በዚያም በሚመሰክሩ ምእመናን ልቡና ያለው በክርስቶስ የማመን ሐሳብ በእነርሱ ፊት ኃይልን ያደርጋል። ለዚህም ነው «መስቀል ኃይላችን ነው፤ መስቀል መጽናኛችን ነው፤ መስቀል ቤዛችን ነው፤ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው፤ አይሁድ ይክዱታል፤ እኛ ግን እናምነዋለን» የምንለው። የምናምነውም ኃይል አድርጓል፤ ያደርጋልም። ክርስቶስ ከተሰቀለበት ሌላ የከበረ መስቀል የለም። ስለዚህ መስቀል የተሰቀለውን ክርስቶስን ያሳስበናል እንጂ ሊያስረሳ የሚችልበት መንገድ የለም።

ትእምርተ መስቀል ክርስቶስ ከመሰቀሉም ቀድሞ ኃይልና በረከትን አባቶች ይሰጡበት የነበረ፤ እግዚአብሔርም በዚያ ትእምርት ላይ አድሮ ሲባርክና ኃይልን



ሲሰጥ ነበር። ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች በባረከ ጊዜ ያደረገውን ማስታወስ ይቻላል። «እስራኤልም ቀኝ እጁን ዘርግቶ በኤፍሬም ራስ ላይ አኖረው፤ እርሱም ታናሽ ነበረ፤ ግራውንም በምናሴ ራስ ላይ አኖረ፤ እጆቹንም አስተላለፈ /አመሳቀለ/» ተብሎ ተጽፏል /ዘፍ. ፵፰፡፲፫/። ሌላም ተጨማሪ ቃል እንይ፤ ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ በተሰቀለበት መስቀል አምሳል ወይም ምልክት ሊቀነብያት ሙሴ የእስራኤልን ጠላቶች ድል ያደርግ ነበር። ስለዚህም መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤ «ሙሴ እጁን ባነሣጊዜ እስራኤል ድል ያደርግ ነበር፤ እጁንም ባወረደ ጊዜ አማሌቅ ድል ያደርግ ነበር፤ የሙሴ እጆች ግን ከብደው ነበር..... አሮንና ሑርም አንዱ በዚህ አንዱ በዚያ ሆነው እጆቹን ይደግፉ ነበር፤ ፀሐይም እስክትገባ ድረስ እጆቹ

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል

የአምልኮ ባዕድ ...

ከገጽ ፲፰ የዞረ

በዚህ ጊዜ ታዲያ ጣዖትን እያመለክን ነው ሊሉን ይችላሉ። ከዚያስ አልፈው በቪዲዮ ፊልሞች በፎቶግራፍ በመሳሰሉትስ እናስተምራለን ሲሉ አላስ ተዋልክ ይሆን? ስለዚህ እግዚአብሔር ሥዕላትን እንደ አምላክ አድርገን ማሰብን ለእነርሱም መገዛትን ከለከለን እንጂ እርሱ የሠራውን በእርሱም ጸጋና ረድኤት ቅዱሳን መላእክትና ሰዎች የሠሩትን የሚያሳዩ የሚዘክሩ ሥዕላትን በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ መጠቀምን አልከለከለንም።

ለእነርሱ የሚቀርብ ስግደትንም በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን ካላት አስተምህሮ አዘልሎ አዛብቶ ለሌሎች መንገር ሐሰ ተኝነት ነው ትችትም ለመሰንዘር ቢሆን ቤተክርስቲያን የምት ለውን በውል ተረድቶ መቅረብ አግባብ ነው። ሰዎች ስግደትን ሁሉ አንተ አምላክ ነህ ለማለት የሚያቀርቡት እንደሆነ አድርጎ ካሰበ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበቡን ልክ ሊመረምር ይገባል። ለሚከበሩ ለሚወደዱ ሰዎችና ለቅዱሳን መላእክት ስለተቀበሉት ጸጋ በማክበር የሰገዱ ነገር ግን አምላክነታቸውም እግዚአብሔር መሆኑን በውል አውቀው ትእዛዙን ጠብቀው የሚኖሩ ደጋጎችን በመጽሐፍ ቅዱስ እናያለን ተሳስተዋል። ለማለት በማያስ ደፍርም መልክ ደጋግመው ያንኑ ማክበር ሲፈጽሙት እናነባለን። በዚያም ግብራቸው እግዚአብሔር አዝኖባቸው ሲወቅሳቸው ወይም ጸጋን ሲያጎድልባቸው አናይም። ለዚህም ኢያሱን ሎጥን ወን ጌላዊው ዮሐንስን ነቢዩ ዳንኤልን እና ያለን። እንዲህ ከሆነ እነዚህና ሌሎች ደጋግ አባቶች ጣዖትን አመለኩ ልንላቸው እንችላለን? ታዲያ ይህን የመሰሉ ፈጣሪ ያልተቆጣባቸውን በርካታ ታሪኮች ስና ነብ ምን ብለን ልንተረጉማቸው እንች ላለን? ስለዚህ ይህን የመሰለውን ስግደት እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ስለሰጣቸው ታላቅ ጸጋ የቀረበላቸው ስግደት መሆኑን ቤተክርስቲያን ትተረጉማለች። ስለዚህ ለቅዱሳት ሥዕላት በሚቀርበው ስግደት አርቶዶክሳውያን ጣዖት እያመለኩ ነው ከማለት በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ እንዴት ይተረጎማል ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ለአንዳንዶችም እግዚአብሔርን ይህን ይመስላል ብሎ በሥዕል ማቅረብ ያንንም ማክበር አምልኮ ጣዖት እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ይህ ግን አግባብ አይደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔርን ይህን ይመስላል ያሉት የሰው ልጆች አይደሉም። እርሱ አስቀድሞም ለነብያት በብዙ ጎብርና አምሳል ተገልጿል። ለነብዩ ኢሳይያስ፣ ለነብዩ ዳንኤል፣ ለሐዋርያው ዮሐንስ፣ በሰው አምሳል መገለጹን እናነባለን። በዚህ በቻ ሳንወሰን በመጽሐፍ ቅዱስ የምናነባቸውን ለምሳሌ የመንፈስ ቅዱስን በርግብ አምሳል መገለጽ በታየበት በዚያው ምሳሌ መሳላችን የሚያስነቅፍ አይሆንም። ሰብአ ሰገል በቤተልሄም ጌታችንን ከእናቱ ጋ አይተውታል። በዚያው ገጽታ መሳልና ክብር መስጠት የሚያስተች ሊሆን አይችልም። በአጠቃላይ እግዚአብሔር ለሰዎች ያደረገውንና ከሰዎችጋ የነበረውን ግንኙነት፣ ቅዱሳኑም ከአገልግሎትና ከተጋድሎ ሕይወታቸው ጋ በተያያዘ የሠሩትን በቅዱሳት ሥዕላት ማሳየቱ በሥዕሉ ለም ናየው የእግዚአብሔር ሥራና ለእርሱ በመገዛት ቅዱሳኑ ለሠሩት መልካም ሥራ ያለንን ክብር ያንን በሚያሳዩ ቅዱሳት ሥዕላቱ ፊት ብንገልጽ የሚያስነቅፍ ሊሆን አይችልም። ይህንን በቅዱሳት ሥዕላቱ የሚታየውን ሥራቸውን

ጣዖት ቢሆን ስግድትን ሁሉ አንተ አምላክ ነህ ለማለት የሚያቀርቡት እንደሆነ አድርጎ ካሰበ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበቡን ልክ ሊመረምር ይገባል።

መጻሕፍት በምናነብ ጊዜ በሕሊናችን እንዳይከሰት ልንከለክለው አንችልም። ይህ በአእምሮ የሚሣለውን ሥዕል መከልከል አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን በሕይወታችንም ተፈላጊ ጉዳይ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የገላትያን ሰዎች ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ በዓይነ ሕሊናቸው ይታይ የነበረበት መልካም ሕይወት አልፎ ወደ ክፉትና አለመታዘዝ ዞር ያሉበትን ከንቱ ሕይወት ማን እንደጫነባቸው የጠየቀበትን መልእክቱን ሁሉ የምናነበው ነው። ቅዱሳት ሥዕላት ደግሞ በሥርዓተ አምልኮ ውስጥ ከሚኖራቸው ድርሻ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ሥራ የቅዱሳኑንም ተጋድሎ ለማሰብ የሚያግዙ የዓይነ ሕሊና ሥዕሎችን ዘወትር በሕይወታችን ውስጥ በመከሰት ያግዙናል የሚል እምነት አለን።

ተዘርግተው ነበር» በዚህ ጊዜም ይህ ትእምርት ኃይል ነበር። ጠላት የተባለ አማሌቀን ድል አድርጎበት ነበርና /ዘጸ. ፲፯፥፲፩/። ያለሑርና አሮን ድጋፍ ብቻውን እጆቹን ዘርግቶ፣ ስለእስራኤል ብቻ ሳይ ሆን ስለዓለም ለተሰቀለውና ጠላት የተ ባለ የዲያብሎስን ኃይልና ሥልጣን ለሻ ረበት የክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ብቻ ሳይሆን የትእምርቱን ኃይልም የሚመሰክር ነው። ያ ትእምርት እንደዚያ ኃይልና ክብር ካለው የክርስቶስ መስቀል ምልክትማ ምን ያህል ይከብር! ምንስ ያህል ኃይ ልን ያደርግ! የሙሴን ትእምርት አሮ ንና ሑር እንደዚያ ከተሸከሙት የክጠ ርስቶስን መስቀል ምልክትማ ካህናትና ምእመናን በጠላት ፊት ሊሸከሙት እን ዴት አይገባ! በመጽሐፍ «ከባላጋራችን የተነሣ በትእዛዝ የተጻፈውን የእዳችንን ደብዳቤ ደመሰሰልን፤ ከመካከላችንም አራቀው፤ በመስቀሉም ቸነከረው» እንዲል የክርስቶስ መስቀል ጠላት ዲያብሎስ በእውነት የተሸነፈበት ጥበብና ኃይሉ ነውና /ቆላ ፪፥፲፬/ ::

ሙሴ በሰውነቱ የሠራው ትእምርት በጠላቶቹ ፊት ኃይልን እንዳደረገለት ለሚያምኑት ሁሉ ከጠላት ፍላጻ ይድኑ ዘንድ ኃይል የሚሆን ምልክትን እንደሚ ሰጣቸው ክቡር ዳዊት «ከቀሰት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው» ሲል ተናግሯል /መዝ. ፷፬፥፬/። እርሱም የክርስቶስ የመስቀሉ ምልክት ነው። ያም የሰው ልጅ ምልክት ተብሎ በወንጌል የተጠቀሰው ነው /ማቴ ፳፬፥፴/። ስለዚህ የክርስቶስ በሆኑት ነገሮች ሁሉ እንደምንባረክ፤ ኃይልም እንደምናገኝ እናምናለን። ክርስቶስን ከመስቀሉ፣ ክርስ ቶስን ከእናቱ፣ ክርስቶስን ከነብያቱ ከሐዋርያቱ፣ መዘተ ነጥሎ ማሰብ እንደሚ ገባ ቤተክርስቲያን ልታስተምር አትች ልም። ይሔ የእምነትም ጉዳይ ነው። ሃይማኖታችን ከተራ ፍልስፍና የጸዳ ሊሆን ይገባዋል።

ዐሥራ ሁለት ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደሆነ እድናለሁ ማለቷን እናስተውል /ማር.፭፥፳፰/። ይህቺ ሴት ያላትን እም ነት እናስብ፤ «ክርስቶስ እጆቹን ጭኖብኝ፣ እግሮቹን ዳስሼ» አላለችም፤ «ልብሱን ብቻ» አለች እንጂ። ልብሱ የክርስቶስ ነውና። እርሱ/አካሉ/ ካልሆነ ኃይልን በእምነት አናገኝም አይባልም። «አካሉን እንጂ ጥላውን አልፈለግም፤ አካሉን እንጂ ልብሱን አለፈልግም፤ የተሰቀለ ውን እንጂ መስቀሉን አልፈልግም፤ ወልድን እንጂ ወላዲቱን አልፈልግም...» ወዘተ አላለችም። እነዚህ ሁሉ የእርሱ ስለሆኑ ይከብራሉ። ከእርሱም የተነሣ በጸጋ የከበሩ መሆናቸውን እንደዚያች ሴት እናምናለን። ከዚህ በወጣ ለዓለም በሚመች ከንቱ መለፍለፍ ልባችን መድከም አይገባውም። ለምናምን ሰዎች

የመስቀሉን ምልክት ሰዎች ሲያዩ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገልንን የፍቅር ሥራ በሚያዩት ሰዎች ልብ ስለሚሥል ክፉን ሐሳብ ለማራቅ፤ መልካሙንም ለማድረግ ኃይል ይሆናል።

የክርስቶስ በሆነው ነገር ሁሉ በረከት ኃይል እንደምናገኝ እናምናለን። ይህ ማለት የእርሱ የሆኑት ሁሉ እርሱን ናቸው ማለት አይደለም። የእርሱ የሆኑት ግን ከእርሱ የተነሣ የከበሩ መሆ ናቸ ውን እናምናለን። አስቀድሞም በትንቢት ስለእርሱ ብቻ ሳይሆን ከእርሱ የተነሣ ስለሚከብሩ ሁሉ ተናግሯል። ስለለበሳ ቸው ልብሶች እንኳን «ልብሶቼን ለራ ሳቸው ተከፋፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ እጣ ተጣጣሉ.»/መዝ ፳፪፥፲፰/ ማለቱን እና ነባለን።

የተሰቀለበት መስቀልና የመስቀሉ ምልክትም እርሱን የሚያሳይና ስለእርሱ የምንመሰክርበት በመሆኑ የከበረ ነው። አንዳንዶቹ የምታከበሩት ክርስቶስ የተሰ ቀለበትን ዋናውን መስቀል ሳይሆን ክፉውም ደጉም ሰው የቀረጸውን ምል ክቱን በመሆኑ አግባብ አይደለም ሊሉ ይሰማሉ። ለዚህ ግን ብዙ ሳንል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኖዳ ሣልሣዊ ክሌዎፓ ዘሩማኒያ የተባሉ ክርስቲያን በአንድ ወቅት ለዚህ ዓይነት ጥያቄ የሰጡትን መልስ ይህንን ጥያቄ ላነሡላቸው ወገ ኖች መልስ ሲሰጡ የጠቀሱትን ንግግር በዚህ አጋጣሚ እናንሣው፤ ክሌዎፓ ዘሩማኒያ እንዲህ ብለው ነበር «ይህንን በቅዱሳት መጻሕፍትም ዘንድ እናደርገ ዋለን፤ በዛሬ ዘመን ቆጥረን የማንጨር ሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች በዓለም ላይ አሉን፤ በእናንተ ሐሳብ ከሆነ እነዚ ህን በክፉዎችም በደኅችም ማተሚያ ቤቶች ወይም አሳታሚዎች ታትመው የሚሠራጩ ቅጂዎች በመሆናቸው ማክ በር የለብንም ማለት ነው፤ ዋናውን /በነብያት በሐዋርያት እጅ የተጻፉ/ ቅጂ ብቻ መያዙ /እርሱን ብቻ ማክበር፤ በዚያም ብቻ መባረክ/ አለብን ማለት ነው። ስለዚህ የቀረበው ይህ አሰተሳ ሰብ ግን ለምክንያታዊ ሰው የሚያ ሳምን አይደለም» ብለው ነበር።

በመሆኑም ጠያቂያችን በትእምርተ መስቀል ላይ አርቶዶክሳውያን ያለን እም ነት ከላይ ከጠቀስናቸው የመጻሕፍት ምስጢር የተገኙ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሠራልንን የፍቅር ሥራ /ነገረ ድኅነት/ ወይም ወንጌልን የምንመሰክርበት የምናስተምርበት በዚ ያም ኃይል የምናገኝበት በመሆኑ መጽሐ ፋዊ መሠረት ያለውና ክርስቶስንም በማሰብ የሚያጸና ነው።

መስቀል ኃይላችን ነዉ!

በጎሩይ ስሜ

ለመጀመሪያም ጊዜ በሚልቪያን ብሪጅ የጦር ሜዳ ላይ ከመሰለፉ በፊት ቅዱስ ቆስጠንጢኖስ በሰማይ ላይ የብርሃን መስቀል አይቶ ‹‹በዚህ ድል ታደርጋለህ›› የሚል ቃልን ካነበበ በኃላ በጦር ሰራዊቱ ልብስ በጋሻቸዉ፤ በጦራቸዉ፤ በፈረሶቻቸው መጣብር ላይ መስቀልን አድርገዉ ከመ ክስሚያኖስ ጋራ በገጠሙት ጦርነት ትልቁን ድል ተጎናጽፈዋል። በዚህም ድል ጣዖት አምልኮ አከተመለት፤ዘመነ ሰማዕታትም አበቃ። አብያተ ክርስቲያናት ተከፈቱ፤የክርስቲያኖች የስቃይና የእንግልት ሕይወት በሰላምና ተደመደመ።


CONSTANTIN SEEING THE FLAMING CROSS IN THE SKY.

ይህንን ፈለግ የተከተሉት አባቶቻችንም መስቀልን በሚለብሱት ልብስ ላይ በመጥለፍ፤ በቤታቸዉ ጉልላት ላይ በማድረግ፤በፈረሳቸዉ መጣብር ላይ በማስጌጥ፤በጦራቸዉ ጫፍ በመሰካት፤በአንገታቸዉ ማተብ በማንጠልጠልና በሰውነታቸዉ ላይ በመነቀስ የሕይወታቸዉ መሠረት የደኅንነታቸው ዋልታ መሆኑን መስክረዋል። እንደነ ቅዱስ ላሊበላ ያሉ አባቶቻችን መስቀሉን በአስደናቂ ሁናቴ የቤተ ክርስቲያን መሠረትና ጉልላት አድርገው በሁለመናቸው አንግሠውት በዘመናቸው ሁሉ ተመላለሱ እንጂ።

በመስቀሉ ኃይልም ድውይ የነበሩ ጤናቸዉን አግኝ ተዋል፤ እውር የነበሩ አይተዋል፤ልምሾም የነበሩ ተራምደዋል።

በመሆኑም አባቶች የክርስቶስን መስቀል የሚያፈ ቅሩት የሰይጣን ድል መነሻ፤ የጠብ ግርግዳ ማፍረሻ መሆኑን ስለተረዱ ነው። ሰይጣን እራስ እራሱ የተ ቀጠቀጠበት ነዋ... መስ ቀሉ። አምላካችን በመስ ቀል ሞት በሰው ልጆች ላይ ሰይጣን በተንኰሉ ያመ ጣውን ሞት የሻረበት በመ ሆኑ ሰይጣንም በበኩሉ አጥብቆ ይፈራዋል። ስለ ዚህም አባቶች መስቀሉን ከፊት ከኃላ ደጀን አድርገው ሰይጣን ያደረባቸውን ሰራዊቶች ድል አድርገዋል። በአድዋም የሆነው ይኸው ነው። በመስቀሉ ኃይል ተማምነዋልና መስቀል አናቱ ላይ ባለው ጦር ብቻ እሳት የሚተፋ መትረየስ ማርኩ። የመስቀሉ ጠላት የሆነው ካቶሊካዊ ወራሪ ጦር በኃይል ሰባብሮ ቤተ ክርስቲያናችንን ምሽግ ቢያደርገውም አባ ቶቻችን የተከሉት የመድፍ ጥይት በጠላት መድፍ አፍ ውስጥ ገብቶ የሠራውን ምሽግ ንዶታል። ምን ጊዜም ቢሆን ጠላት የሚንቀውን መሰቀል እኛ እናከብረዋለን ኃይላችን ነውና። ስለዚህ ጥንት በዘመነ ቆስጠንጢኖስ እንደሆነው ሁሉ ‹‹መስቀል ኃይላችን ነው!›› ያሉት እነዚህ አባቶቻችን የመሰቀሉ ባለቤት አላሳፈራቸውም።

የመስቀል ደመራ በኢትዮጵያ

በንፋይ ሰሜ

ዕሌኒ ንግሥት መስቀሉን ካገኘች ጀምሮ የመስቀሉ በዓል በድምቀት ሲከበር ኖሮአል። ለዚህም መነሻ የሆነዉ መስቀሉ ያለበትን አንዲጠቁምላት በደመራ ላይ ጸጣን አድርጋ በማጤስዋና ከቢሁ ጋር ተያይዞ በደመራ ብርሃን መስቀሉን የማግኘትዋን ነገር ስላስታወቀች ነዉ። ይህን የዕሌኒን ድርጊት ተከትሉ ደመራን ሠርቶ እጣን በመጨመርና በማንደድ በዓሉን ማክበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመጣ ትውፊት ነው።



በኢትዮጵያ ውስጥ መስቀልን ማክበርና መዘ ክር የተጀመረው በዐፄ ዘርዐያዕቆብ ዘመን የሚ መስክተው ወገኖች አሉ። በዓለ መስቀልና ክብረ መስቀል በአርሳቸው ዘመን ጎልቶ ይታይ እንጂ መሠረቱ እጅግ ቀደም ብሉ ነው። ይህንን ለማለት ከሚረዱን ዋነ ኛው አመላካች ማስረጃ ገብረ መስቀል የሚባል ስም በነገሥታት ታሪክ ውስጥ እንኳን መገኘቱ ነው። ከጥንት ጊዜ ጀምሮ መስቀል በቤተ ክርስቲያን አዕማድ ላይ እየተቀረጸ ይሰከር ነበር። እንዲሁም ካህናት የሚያሳልሙት መስቀል በክርስ ምድር ቁፋሮ ተገኝቷል። ዐፄ ላሊበላም መስቀሉን የቤተ ክርስቲያን መሠረትና ጉልላት አድርገዉታል። በዐፄ ያግብአ ጽዮን ዘመንም ለመስቀል አንሰግድም ብለዉ የተነሡ ጥቂት መናፍቃንን ሰብስበዉ ንጉሡ እራሳቸዉ ለመስቀሉ በመስገድ ፈለጋቸውን እንዲከተሉ አሳስበዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየዉ ለመስቀሉ ክብርን መስጠትም ሆነ በበዓል ማክበር ከጥንት ጀምሮ የነበረ እንደሆነ ነው።

በበዓል አከባበሩ ሁኔታ ግን በየጊዜዉ ለውጦች እያሳየ እንደመጣ የሚጠቁሙ ታሪካዊ ምንጮች ይገኛሉ። በመስከረም የነበረው በዓል በዐፄ ገብረ መስቀል የተጀመረዉ የተቀጻል ጽጌ በዓል ነዉ። ይህንን በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ በንጉሡ ፊት የተከበረው መስከረም ፲ ላይ ሲሆን የክረምቱን ማለፍ፡ የአበባውን መፍካት አስመልክቱ የአደይ ጉንጉን በስጦታ መልክ በማቅረብና በወረብ ተቀጻል ጽጌ ገብረ መስቀል ዐፄ› በማለት አክብረውታል። ይህ በዓል በመስከረም ወር ከክረምቱ መውጫ ላይ ለዘመናት እየተከበረ ቆይቶል። ከ፲፱ኛዉ ምዕት አንሥቶ ማለ ትም ዐፄ ዳዊት ግማደ መስቀሉን ወደ ኢትዮ ጵያ ካመጡ ቡኋላ በደመራ መስቀልን ማክበር እን ደተጀመረ ይወሳል። መስከረም ዐሥር ደግሞ በታሪክ ላይ እንደሚ ታወቀዉ መስቀሉን ዐፄ ዳዊት የተቀበሉበ ትና ይህንን አስመል ክቶ ቀኑ ከተቀጻል ጽጌ ጋር አብሮ በቤተ ክር ስቲያን የሚከበርበት ነው። መስቀሉን በግሸን ተራራ ላይ ያኖሩት ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብም የመስቀልን በዓል በድምቀት እንዳከበሩት በስፋት ተጽፎአል። ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ መስቀሉን ማንኛዉም ሰዉ መእጹ ላይ እንዲነተስ ጣኩትንም እንዲያወግዝ ያዘዙት። በኋላም የግራኝ ወረራን ለማሸሽ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የገዘፈዉ ካስታንሆሠ ዐፄ ገላዉዴዎስ መስቀልን ከድል በኋላ ያከበሩበትን ሁናቴ በጥሩ ሁኔታ ገልጾታል።

ይህንን ሥርዓት አባቶች ነገሥታቱ ሳያፋልሱና ሳያስቀሩ እስከ፲ኛዉ መቶ ክ/ዘ ድረስ ጠብቀውታል።

ሠስቅስ ከዮት ጠጣ

ስለ መስቀል ስንናገር ነገርን ከሥሩ ውኃን ከጥሩ እንዲሉ ከመሠረቱ ብንናገር ይቀለናል። መስቀል በገነት ውስጥ ካሉ የተለያዩ ዕፀዋት ግንድ ነው። ከዕፅ ዘይት፣ ከዕፅ ከርካህ፣ ከዕፅ ወይራ፣ ከዕፅ ሥርናይ /ምንጩ ሕማማተ መስቀል ገጽ.፴/

.....ቃኤል ወንድሙ አቤልን በቅንዓት ከገደለው በኋላ ጽኑዕ የእግዚአብሔር መርገም ባላዩ ላይ ወደቀበት። ደም ያሰከረው ቃኤል በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ሆነ። እርሱም ሰውን ባየ ቁጥር ይሸሻል። ሰውም በእርግማን የቀሰለው ሕይወቱን እያየ ይሸሸዋል።

ማኅበራዊ ሕይወት ጀርባዋን የሰጠችው ቃኤል ብቸኝነት ስለከበደችው ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል የጸጸት ዕንባውን እረጨ። «እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ከምድር ፊት አሳድደኸኝ ከፊት ህም እሰወራለሁ፥ በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ፥ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል» አለ። እግዚአብሔርም ቃኤልን ያገኘው ሁሉ እንዳ ይገድለው ምልክትን አደረገለት።



ይህ ምልክት ምንድን ነው?

ቃኤልን የሚጠብቅ መል አክ ቅዱስ ሚካኤል ነበር። እግዚአብሔር ይህንን መልአክ በያዘው የነበልባል ሰይፍ የገነትን ዕፅ ቆርጦ ለቃኤል እንዲ ያመጣለት አዘዘው። መል አኩም የተባለውን ፈጸመ። አምጥቶም ተከለለት። ቃኤልም ያየው ሁሉ እንዳይገድለው ከጥፋት የሚሰወርበት የድኅነት ምልክት ሆነለት /ዘፍ.፬÷፬-፲፭/።

የዕፀ መስቀል ምስጢር ከዚህ ይጀማል። ይህ የገነት ዕፅ እስከ ጠቢቡ ሰሎሞን ድረስ ከደረሰ በኋላ ከሰሎሞን እስከ ክርስቶስ ልደት የተነሡ ሠላሳ ነገሥታት በእየ ዘመነ መንግሥታቸው ሲነሡ በየብሮቻቸው ይለብሡታል። ከዚህ ብር የወሰደ ርገም እንዲሆን ነበር /ካህናተ አይሁድ ጌታን ከይሁዳ በገዙት ጊዜ ለይሁዳ የሰጡት ከዚህ ሠላሳ ብር ነው። ከቃኤል ጀምሮ የነበረው እርግማን በይሁዳ ላይ ወድቋል/።

ጠቢቡ ሰሎሞን ስለዚህ ዕፀ መስቀል ትንቢት ተናግሯል። /መኃ.፫/ «ዘእምኃሊ ሶን ይትገዘም ወበኅለኣታ ይተከል» ኃሲሶን ከሚባል ቦታ ተቆርጦ በኅልኣታ ይተከላል /ዮሃንስ ዳዊት ተመልከት/

እንዳለ አይሁድ ይህንን ዕፅ ኃሲሶን ከሚባል ቦታ ወስደው በኅልኣታ ተክለው ታል። በመጨረሻም አይሁድ ጌታችንን ለመስቀል ባሰቡ ጊዜ መስቀልን ከዚህ የገነት ዕፅ አዘጋጅተውታል። መስቀል ከተለያዩ የገነት ዕፀዋት የበቀለ እንደመሆኑ ክብደቱ መጠን የለውም» አይሁድ ጌታቸውን ጠልተውታልና መስቀል ተሸክሞ የቀራንዮን ዳገት ሲወጣ ወገቡ እንኩት ብሎ ይሙት ብለው ስላሰቡ ዕፀ መስቀልን ለሞቱ አዘጋጁለት።

ጌታችን ግን የመጣበት ዓላማ ነውና ሞትን /ዲያብሎስን/ በመስቀል ላይ ድል አድርጎ ለእኛ መስቀልን የድኅነት ምልክታችን፣ ከጠላት ቀስት መሰወሪያችን አድርጎ ሰጠን /ለቃኤል የድኅነት ምልክት እንዳደረገለት/ ፍጻሜው ሊሆዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የድኅነት ምልክት አድርጎ መስቀልን ሲሰጠን ነው። /መዝ.፺፱÷፬/ ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው።» ተብሏልና።

ድኅነት በመስቀል ላይ የተፈጸመበት ምክንያት

የእኛ ጌታ ለሥራው ሁሉ ምክንያት አለው።

ሞት በዕፅ /በዕፅ በለስ/ ምክንያት ስለመጣ ሕይወት በዕፅ መስቀል ምክን ያት ተገኘ። በዕፅ ምክንያት የወደቀብንን የሞት ቀንበር በዕፅ ምክንያት ሲሰብር ልን ነው።

ዲያቢሎስ በዕፅ ምክንያት አዳምን ቢያሸንፈው ጌታችን በዕፀ መስቀል አሸ ነፈለት። ዱላን በዱላ እንዲመክቱ በዕፅ የጣለን ሰይጣን በዕፅ ተመክቶበት ጭንቅ ላቱን ተቀንጥሶ ወድቋል። የሰይጣንም ጥበብ በክርስቶስ ጥበብ ተንዶ ተሸንፏል። ጠቢባን ሁኑ እንዳለ በወንጌል /ማቴ.፲÷፲፮/ አንድም ሰውን በሞተበት ነገር ማዳን ለእግዚአብሔር ልማዱ ነው። በናህ ዘመን ዓለም በውኃ ቢጠፋ ሰውን መልሶ በጥ ምቀት በኩል ውኃን ለድኅነታችን እንዳ ደረገልን ማለት ነው /ማር.፲፮÷፲፮/።

በብሉይ ኪዳን መስቀል የወንጀለኞች መቅጫ ነበር። ጌታችን እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ ተሰቀለበት። መስቀሉንም በደሙ ቀድሶ አሁን የወንጀለኞች መቅጫ ሳይሆን የወንጀለኛው የዲያብሎስ መቅጫ አድርጎ ለእኛ ሰጠን።

በብሉይ ኪዳን መስቀል የርጉማን መሰቀያ ተብሎ ይታመንበት ነበር። የር ጉማን ደም መሬትን ያረክሳል ብለው ስለሚያምኑ ከምድር ከፍ ባለ መስቀል ላይ ይሰቅልዋቸው ነበር። ጌታችን ኢየ ሱስ ክርስቶስ የእኛን እርግማን በመስ ቀል ላይ ተሸክሞ ከሕግ እርግማን ነጻ አወጣን። በቅዱስ ደሙ ቀደሰን።

በዓለ መስቀል



የአይሁድ ሊቃናት ክኅነታቱና ከሕዝቡ ጋር በሰይጣናዊ ቅንዓት ተነሣሥተው በስቅላት ያስገደሉት ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሥጋው ከተቀበረም በኋላ ቅንዓታቸው ሊበርድ፣ጭካኔውም ሊረግብ አልቻለም፡፡ ያ ያሰቃዩት ጌታ ሰለፍ ጥረቱ ቤዛነት የመጨረሻው ፋሲካ በግ ሆኖ የተሰዋበትንና ይህን የመሰለው መለኮታዊ ፍቅር ተፈጽሞ ምስጢሩ የተከሰተበትን እንጨት እንኳ በርግራጌው ትተው ሊያልፉት አልፈለጉም፤፤‹‹ደቀ መዛሙርቱ ሥጋውን ሰርቀው እንዳ ይወስዱ›› በሚል ምክንያት መቃብሩን እንዲያስጠብቁት ወደ ጲላጦስ ሂደው በመማጸንና እርሱም ፈቃቀዳቸውን በመፈጸም በድኑን ሳይቀር እንዳልተውት ሁሉ፣አሁንም በመስቀሉ ላይ የፈጸሙት ግፍ ከዚያ ያላነሰ እንዲያውም የባሰና ወደር የማይገኝለት ሆኖ እንዲቀጥል ማድረጋቸውን እነሆ እንመ ለክታለን፤፤

ይኸውም መስቀሉ ደብዛው ሳይቀር ጨርሶ እንዲጠፋ ያደረጉበት መሠረ ዕቅዳቸውና ክፉ ድርጊታቸው ነው፡፡ በዚህ ዕቅዳቸው መሠረት ማንም ሰው፣ የራሳቸው የሆኑት ወገኖቻቸው እንኳ ሳይቀሩ ሊጠረጥሩ በማይችሉት ሁኔታና ሥፍራ መስቀሉን በድብቅ አስወስደው ቀበሩት፤ ያም ሥፍራ ለከተማው የቆሻሻ መጣያ የተመደበው ቦታ ነበር፤፤በዚህ ድርጊታቸው ሦስት እኩይ ዓላማዎቻቸውን የፈጸሙ መስሏቸው ነበር፣ ከእነዚህ ዓላማዎቻቸው መካካል፡-

የመጀመሪያው፡- የሰማይና የምድር ፈጣሪና ጌታ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው የተቆረሰበትንና ክቡር ደሙ የፈሰሰበትን ምሥዋዕ/መሠዊያ/ መስቀሉን ማርከስ ሲሆን፣

ሁለተኛው ደግሞ፡- ሕዝቡ ሁሉ የቤቱንና የከተማውን ጥራጊና ቆሻሻ በየቀኑ ያለማቋረጥ በማፍሰስና በመጣል መቀበሩን ማንም ሊያውቅ እንደማይችል፣ምናልባት ቢታወቅ እንኳ ምን ጊዜም ተቆፍሮ እንዳይገኝና እንዳይወጣ ማድረግ ነው፤፤

ሦስተኛውም፡- መስቀሉን እንዲህ አድርገው በሚቀብሩበት ጊዜ፣ የክፋታቸው መጠን ምን ያህል የጸና መሆኑን የሚያመለክተው ሌላው ገጽታ ይታል፤፤ ይኸውም ዕፀ መስቀሉ ምናልባት ተቆፍሮ የተገኘ እንደሆነ የዓለም መድኀን የተሰቀለበት እውነተኛው እንጨት የትኛው እንደሆነ ተለይቶ እንዳይታወቅ ለማደናገር ሲሉ፣ በቀኝና በግራ የተሰቀሉትን ወንበዴዎች ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎች ወንጀለኞች ጭምር የተሰቀሉበትን እንጨት ከጌታ መስቀል ጋር ደባልቀው እንዲቀበር ማድረጋቸው ነው፤፤

ለመስቀል የጸጋ ስግደት እንዲገባ


ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ላዳነበት እጅንና እግሩን ለተቸነከረበት ክቡር ደሙ ለፈሰሰበት መስቀል መስገድ እንዲገባ አስቀድሞ ትንቢት ተነግሮአል። ይኸውም« ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግዚእነ የጌታችን እግር ከቆመበት ቦታ እንሰገዳለን» ተብሎ /መዝ ፻፴፩/። ይሀም ለቦታ አለ እንጂ መቼ ለመስቀል አለ? እንዳይባል ዓለሙን ስላዳነበት ክቡር ደሙን ስላፈሰሰበት በበለጠ ለመናገር ሲሆን ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር በተመላለሰባቸው ቅዱሳት መካናትም ላይ አብያተ ክርስቲያን ተተክለውባቸው ቅዱስ ሥጋው ተፈትቶባቸው ክቡር ደሙ ፈስሶ ባቸው ቅዱስ መስቀሉ ተተክሎባቸዋልና« ውስተ መካን» ቢልም አንድ ነው። አንዲሁም ሀዋርያው ቅዱስ ጳወሎስ ተስፋ መስቀል በሌለባቸው ወግኖች ዘንድ ለመስቀል መስገድ ስንፍና ነው፣ ተስፋ ባለን በኛ ዘንድ ግን መስቀል የእግዚአብሄር ኃይል ነው ባለው መሠረት መስቀል ኃይልነ፣ መስቀል ጽንዕነ መስቀል ቤዛነ ፣መስቀል መድ ኃኒተ ነፍስነ እያልን ለመስቀል እንሰግዳለን «እስመ ነገረ መስቀሉሰ ዕበድ ውእቱ በኀበ ኀጉለን ወበኀቤ ነሰ ለእለ ድኅነ ኃይለ እግዚአብሄር ውእቱ» እንዳለ ፩ቆሮ ፩።



ደግሞም እኔ በጌታቸችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንጂ በምንም በምን አልመካም ብላል ገላ፮፡፲፬። ስንካንስ ዓለሙ ለዳነበት ክቡር ደሙ ላፈሰሰበት መስቀል ያዕቆብ ለገዛ በትሩ እየሰገደ እግዚአብሔርን ስላመሰገነ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት፡ ተመሰገነበት እንጂ አልተነቀፈበትም ዘፍ ፵፯፡፴፩ ዕብ ፲፩፡፳፩ ያዕቆብ ክራሱ በትር በመስገዱ፡ አምልኮ ባዕድ ያልተቆጠረበት ክርስቶስ ለተሰቀለበት ክቡር ደሙ ለፈሰሰበት ቅዱስ መስቀል የሰገደማ እንዴት ሊመሰገን አይገባ !!

"ወይ ምን ወይ ቁም?"

ትዕግስት ታፈረ ሞላ



አፈን በምሳሌ እከፍታለሁ፣ ከቀድሞ ጀምሮ ያለውንም ተምሳሌት እናገራለሁ። /መዝ. ፸፯፥፪/

ምድር በዓል ትላለች በየቦታው የድፎ ዳቦው ጭስ ይሸታል። ዶሮዎች ለዓመት በዓል ጊዜ ሰዓት የሚጠብቁ አይመስልም። በየግቢው አሁንም አሁንም ኩኩሉአቸውን ያቀልጡታል። በዓል ሲደርስ ሰማይ ራሱ አዲስ ምንጣፍ የሚቀየርለት ይመስለኛል። እንዲህ ዓይነት ቀለም ይይዛል ማለት ባልችልም ቀና ስል ግን የተለየ ድባብ ይታየኛል።

በዚህ ሰሞን ትንፋሽ ያጥረኛል፣ የማልፈጥረው ሥራ የለም። የቤቴን ዕቃዎች አቀማመጥ እቀያይራለሁ። ገና ዓመት በዓል ወር ሲቀርው ጭን ቅላቴ በሐሳብ ይዞራል። የዳቦ እህል ከየትኛው ሱቅ ልግዛ የትኛውን የሐበሻ ልብስ ልልበስ በግ ይታረድ ወይስ ዶሮ የበቃል፣ ነው ወይስ ቅርጫ? ከድካሜ ብዛት በዓሉ ካለፈ በኋላ ሳምንት እታመማለሁ።

ዛሬ መስከረም ፲፮ ነው ለግማሽ ቀንም ቢሆን ሥራ መግባት አለብኝ እንደተመለስኩ ቡና ስለማፈላ እንኳን ቤተሰቦቼ ጎረቤቶቼም በጉጉት ይጠ ብቁኛል። ድፎውን ዶሮውን ጠላውን ስል የጠቋቆረውን ፊቴን በፓውደር አብሼ፣ ለዚህ ቀን ተበድሬ ያሰፋሁትን የሐበሻ ልብስ ለብሼ በጠዋት ቢሮ ደረስኩ። ወደቢሮ መግቢያ መተላለ ፊያው ላይ የዋና ሥራ አስኪያጁን ጸሐፊ አገኘኋት።

«ብርትዬ ዛሬ ሌላ ሆነሻል» አለችኝ እሷ ለእን ቁጣጣሽ በዓል የለበሰች ውን የሐበሻ ልብስ ዛሬም ደግማ ለብሰዋለች።

ቢሮዬ ክፍት ነው ከገባ አንድ ወር ያልሞላው የሒሳብ ሠራተኛ ቀድሞ ገብቶ ሥራው ላይ ተተክሏል።

«ደህና አደርሽ ብር ቱካን?» አለኝ፣ ገና አንገቴ ሲገባ ፈገግ ብሎ እግዜር ይመሰ ገን፣ እንኳን አደረ ሰህ አልኩና በውስጤ ደግሞ ምን በጠዋት



መጥቶ ይጎለታል፤ አቃጣሪ፤ ማንን ለማሳጣት ነው፤ አልኩ «እንኳን አብሮ አደረሰን» አለኝና ጠረጴዛው ላይ የተከመሩለት ደረሰኞች ላይ አቀረቀረ።

ሲራክ ገና አልመጣም። እሱ የእኔ ቢጤ ነው፤ እንቅልፍ ካለመጥገቡ የተነሣ ያበጡ ዐይኖቹን እየሞገተ ዘና ብሎ ረፈድ ሲል ይመጣል። ከዛም በጀ ብሎ አይቀመጥም። ወጣ ገባ ስለሚያበዛ ስልክ ለመደወልም፤ መስታውት ለማየትም ነፃነት ይሰጣል።

«ይኼማ ገጣማ አልኩ»

«እ?» አለኝ ዮሴፍ ያናገርኩት መስሎት። ሳላውቀው ድምፅ አውጥቼ ኖሯል ለካ።

«አ.. ይ ምንም» አልኩና በድንጋጤ ያልከፈትኩትን የኮምፒውተሬን ማውዝ አወዛወዝኩት። ቆይቶ .. ቆይቶ ሲራክ መጣ። እሱ መሆኑን በኮቴው ብቻ ገና ሩቅ እያለ አውቃለሁ። እንደገባ ሰላም ሰላም አለና በደፈናው ኩቱን አውልቆ ወንበሩ መደገፊያ ላይ አንጠልጥሎ ቁጭ አለ።

በተፈጥሮዬ የአፍታ ፀጥታም ይጨንቀኛል። ግዴለሽነቱን እያወኩ ወሬ ለማንሣት ያህል በዓል እንዴት ነው አልኩ፤ ሲራክን እያየሁ ግር እንዳለው ሰው ዐይኖቹን አጥብቦ ዓየኝና «በዓሉን አሳበው የቢራ ሒሳብ ይጨም ሩብናል፤ ይልቅ አንቺ አበባ መስለሻል» አለኝ።

«ተው እንጂ?» አልኩና ረዘም አድርጌ ስንከተከት ዮሴፍ በመሐል «እሷ የመስቀል በዓል እንዴት ነው? ነው ያለችህ» ብሎ ጣልቃ ገባ።

«እኮ ደመራ ዘንድሮ ደግሞ ወዴት ይወድቅ ይሆን?»

«ወዳንተ ይወድቅና ጥጋቡ ትባላለሃ/» አልኩና ብቻዬን ተንከተከትኩ። ሲራክ በይሉኝታ መሠለኝ ፈገግታ አዋጣ።

«ኸረ ተው የንግሥት ዕሌኒን ድካም አታቃሉት» ዮሴፍ ታዘበን፤ ሲራክ «እኛ ምን አለን? ዛሬ መስቀል አደባባይ ሕዝበ አዳም ተሰብስቦ የሚጠብቀውን የደመራ አወዳደቅ ሥርዐት...» ሲል ከአፉ ነጠኩና

«ወደ ምሥራቅ ነው ወደ ደቡብ ወይስ ወደ ሰሜንና ምዕራብ የሚወድቀው? የወደቀበት አቅጣጫ አገሩ የሆነ ዘንድሮ የእኛ አካባቢ ጥጋብ ይሆናል ሲል ያልወደቀበት አካባቢ ሰው ደግሞ ከርሞን በጉጉት ይጠብቃል፤ መቼም ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥ» ስል ዮሴፍ «እሱ እኮ ባህል ነው በቃ! ልማድ፤ ንግሥት ዕሌኒ ጭስ ያጨሰችው ወደየት አቅጣጫ ጥጋብ ይሆናል ብላ አይደለም» አለ።

«ዕሌኒ ናት ደመራን የጀመረችው አይደል?» አልኩት፤ ሳቄን ትቼ። እንደ እውነቱ ከሆነ በየዓመቱ በየቤተ ክርስቲያኑም በሚዲያውም ከመስቀል በዓል ጋር ተያይዞ ስሟን እሰማለሁ ልበ ብዙ ስለማላዳምጥ ግን ንግሥት ሳባና ንግሥት ዕሌኒ አንዳንዴ አንድ ሰው ይመስሉኛል።

ዮሴፍ «ብርቱካን በዛሬውለት እናት ቤተ ክርስቲያን የምታከብረው የደመራ በዓል ሌላ የተለየ ባህል ሳይሆን ነገረ መስቀሉን ነው።» ሲለኝ

ነገሩ ይበልጥ ተወሳሰበብኝ።። ጸጥ ብዬ ሳየው፤ ሲራክ «እና! መሐል አደባባይ ሰንበት ተማሪ ሁሉ እየዞረ የሚዘምርለት ደመራ ምንድን ነው?» ዮሴፍ ላይ አፈጠጠ።

«እሱ ምን መሰለህ ንግሥት ዕሌኒ ድሆች ክርስቲያኖችን ለመርዳትና አብያተ ክርስቲያናችን ለመሥራት ወደ ኢየሩሳሌም ሐዲች ኢየሩሳሌም በደረሰች ጊዜ የጌታችንን መስቀል የተቀበረበትን ቦታ የሚያሳያት አጥታ በፍለጋ ብዙ ጊዜ ሆነ። በኋላ አንድ ኪራኮስ የሚባል እስራኤላዊ ቦታውን አካባበቢውን ነግሯት ዕጣን አስጤሰች። ጢሱ ወደ ሰማይ ከወጣ በኋላ ተመልሶ በአንድ ቦታ ላይ ዐረፈ። መስቀሉ እዛ ቦታ ተገኘ። ስታስቆፍር ሦስቱን መስቀል አገኘች»

«የወንበዴዎችንም» አልኩ፤ ሳላስበው አቋርጨው፤ «አዎ! የጌታችንን መስቀል ለመለየት ሙታንን አቅርበው በየተራ መስቀሉ ላይ እንዲቀመጥ አደረጉ። የጌታችን መስቀል ላይ ሲያርፍ በድኑ ሕይወት አገኘ።

ዮሴፍ ቀጠለ «ንግሥት ዕሌኒ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላትን ፍቅር የተሰቀልበትን መስቀል በመፈለግና በማግኘት ለእሱም ክብር በመስጠት ገልጻለች። ለእኛ ለክርስቲያኖች መስቀል የዚህ ፍቅር መግለጫ ምልክታችን ነው። ክርስቶስ የሰጠን ሰላምም መገለጫ ነው «ጥልን በመስቀሉ ገደለ።» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ በመስቀል ተሰቅሎ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የጠ ብን ግድግዳ አፈረሰ፣ ፍቅርን ለዓለም ሰበከ። ከዛ በፊት ሮማውያን በመስቀል የሚቀጡት ወንበዴዎችን ነበር። ጌታችን ከተሰቀለ በኋላ ግን መስቀል የውርደት ምልክት ሳይሆን የክብር ምልክት ሆነ፣ ነብዩ ኢሳይያስ «በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን» እንዳለ የእኛን ውርደት እርሱ ለበሰ።

እኔና ሲራክ ፊታችን መቼ ወደ ዮሴፍ እንደዞረ እንጃ ብቻ ተመስጠን እንሰማዋለን።

«ታዲያ እንደ ክርስቲያን ማክበር የሚገባቸው በመስቀል ላይ ስለ ሰው ልጆች የሞተውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው እንጂ መስቀሉ ምንድነው?» ሲራክ ሙግት ገጠመ እኔ ግራ ተጋባሁኝ ዮሴፍ እንዲህ መለሰ «ምን ነካህ ሲራክ! እንኳን የክርስቶስ መስቀልና የመስ ቀሉ ምልክት ቀርቶ የቅዱሳን ሐዋርያት ልብስና ጥላ እንኳን ስለ ስንቶች ፈውስና በረከት እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ አታነብም እንዴ! በዘመነ ሐዋርያት የነበሩ ሰዎች ሐዋርያትን እንጂ ልብሳቸውን ጥላቸውን አንፈልግም፣ ሳይሉ በዚያ መንፈሳዊ ጥቅምን ነገኙ እኛ ታዲያ የጌታችን መስቀል ምን ያደርጋል ማለት እንችላለን? ዛሬ እኛም በአንገታችን መስቀሉን ስናስር፣ በመስቀል ምል ክት ስንባርክ፣ ስንስም መስቀሉ አንጨት ወይም ብረት መሆኑን አጥተነው አይደለም። መስቀሉን ከጌታችን ሥነ ስቅለት ቤዛነት ጋር ነጣጥለን ስለማናየው እንደ እም ነታችን እንድናለን።»

በአንገቴ ያንጠለጠልኩትን ትልቅ የብር መስቀል ሳላስበው እየዳሰስኩ እስማለሁ የሲራክ ጥያቄዎች አላ ባሩም «ግን እኮ አንዳንድ ሰዎች መስቀል የአባታችን ገዳይ ነው እንዴት እናከብረዋልን ይላሉ?»

ዮሴፍ ፈገግ አለ፣ መልሶ ደገሞ ፊቱ ታሰረ «መስቀል የክብር ባለቤት የፍጡራን ሁሉ ጌታ ሰውን ያለዋጋ እንዲሁ የወደደ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ሞቱ ሞትን ድል የማድረጉ ምልክት ነው። መስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ ዓለምን በአንዴ ዋጀ። የቀደሙትንም የነበሩትንም ከቀጣዩም ትውልድ በስሙ የሚያምኑትን በአንዴ አዳነ። ክርስቶስ የተሰቀለው በድንገት ወይም ቅጣት ሆኖ አይደለም ነብያት ትንቢት ተናግረው ምሳሌ ተመስሎ የቆየ ነው እርሱ ራሱ ክርስቶስ በወንጌል «የሰው ልጅ ሊሰቀል ይገባዋል» ብሏል። ስለዚህ የጌታችን የመስቀል ሞት ድንገት የመጣ አይደለም አምላክ ሆኖ እያለ አዳምን ወደር በሌለው ፍቅር እንደወደደው ለመግለጽ በፈቃዱ ተሰቀለ እንጂ፣ ቅድም እንዳልኳችሁ የውርደት ምልክት የነበረውን መስቀል የምሕረት ምልክት አደረገ እንጂ ያለ ፈቃዱስ ሮማውያን እንኳን ሊሰቅሉት እጃቸውን ሊያነሡበት ባልተቻላቸውም ነበር።»

አለና የሒሳብ ማሰቢያ ማሽኑን እየነካካ «ክብር ምስጋና ይግባውና አምላካችን በብር በአላቂ በውዳቂ ነገር አልገዛንም። በደሙ ነው። ለዚህም ነው እንግዲህ ጌታችን ላይ መስቀሉን አስረን እስከ ሞት ድረስ ስላንተ እንመሰክራ ለን የምንለው፣ ለዚህ ነው ዛሬ እንኳ እናታችን ንግ ሥት ዕሌኒ አደባባይ ላይ ደመራ እያጨስን መስቀል ኃይልነ፣ መስቀል ቤዛነ፣ እያልን የምንመሰክረው።

የሲራክ ጥያቄዎች ምንጫቸው ደረቀ መሰለኝ ዝም አለ። እኔም ምንም አልተናገርኩም። ውስጤ ግን የሆነ ነገር ሲፈላ ይታወቀኛል። ጠዋት ከቤቴ ስወጣ ላከብረው ያሰብኩት የመስቀል በዓልና የአሁኑ ሒሳቤ ተለየብኝ።

የጠዋቱ ቡና ማፍላት ድፎ መቁረስ፣ ዶሮ.. ሰው ጠርቶ መጫወት መብላት መጠጣት...

የአሁኑ- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።

ሰዓቱ ደረሰ ከሥራ ወጣሁ። ክንብንቤን አስተካክዬ መስቀሌን ደረቴ ላይ በግልጽ አወጣሁ። የጥበቤን ጥለት በፋሽን ወዳጅ ልቤ ማየት ቀረ። ጥልፋ መስቀል ነው። መስቀል ምልክቴ ነው። ስመለስ ቤቴ ቤተሰቦቼም ጎረቤቶቼም እንደሚጠብቁኝ እያወኩ ቁልቁል የመስቀል አደባባይን መንገድ ያዝኩ። ከጠዋቱ በበለጠ ምድር የዓመት በዓል ሸማ ለብሳ ታየችኝ። ሕፃን አዋቂው ወደ ደመራው ይጎርፋል። ስንቶቹ ወደ ደመራ በዓል ሲሔዱ ክርስቶስ ስለሠራልን ውለታ ምሕረት እያሰቡ ይኼዳሉ? ስንቶቹስ ይህን ለመመስከር ይጓዛሉ ብዬ ለአፍታ አሰብኩ።

ዛሬ እግዚአብሔር በዮሴፍ አማካኝነት እውነትን መክሮኛል። ቃላቶቹ ውስጤ ይንተከተካሉ። አንዳንዴ ውስጤ ሲመሰጥ አፌ ያመልጠዋል። አሁንም ሳላስበው ጮክ ብዬ መስቀል ኃይላችን ነው፣ መስቀል ቤዛችን ነው፣ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው አይሁድ ይክዱታል እኛ ግን እናምነዋለን። የምናምነው እኛም በመስቀሉ እንድናለን። ድነናልም አልኩ።» ሰዎች እንደ እብድ እየተሳሳቁ አዩኝ። አላፈርኩም። የእውነት ምስክርነት አያሳፍርም። ጌታዬ ስለ እኔ እርቃኑን በአደባባይ በመስቀል ላይ ፍቅሩን ሲመሰክር አላፈረም። ታዲያ እኔ ባለእዳው ስለ እሱ ስመሰክር እንዴት ልፈር። ቀጠ ልኩ መስቀል ኃይላችን ነው፣ መስቀል ቤዛችን ነው። መስቀል ጮክ ብዬ እየመሰከርኩ ቶሎ ቶሎ እራመዳለሁ። ወደ ደመራ ... የዘንድሮ መስቀል ከመቀጣጠሉ በፊት ወደ እኔ ወደቀ።

ሦስቱ ዛፎች

ዲ/ን ሄኖክ ኃይሌ

አራዊት መጠለያ ከሆነው ጥቅጥቅ ካለው ደን መካከል ከፍ ብለው የሚታዩ ሦስት ዛፎች ነበሩ። እነዚህ ዛፎች ከያሉበት ሆነው አንዳች ጠቃሚ ውይይት እያደረጉ ነው። እነዚህ ዛፎች ወደ ፊት ምን መሆን እንደ ሚፈልጉ የልባቸውን ምኞት በግልጽ እየተ ነጋገሩ ነበር።

‹‹እኔ መቼስ›› አለ አንደኛው ዛፍ ‹‹ፈጣሪዬ ቢፈቅድና ከአናጺዎች ምሳር ቢሠ ውረኝ ምኞቴ ትልቅ ደረጃ ላይ መድረስ ነው።›› አለ። ሁለተኛው ዛፍ በመገረም ‹‹ዛፍ ካልቆረጠና ለአንድ ሥራ ካልዋለ ዝም ብሎ ቢቆም አርጅቶ ከመውደቅ ሌላ ምን ትልቅ ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹አይ አንተ እንዳልከው አርጅቶ መው ደቅ ሳይሆን የእኔ ምኞት የዕዕዋት ሁሉ ንጉሥ መሆንና ከፍ ከፍ ብሎ መታየት ነው። ሰዎች እኔን ሲያዩ እግዚአብሔርንና ገነትን እንዲያስታውሱ እፈልጋለሁ።›› አለ በተመስጦ።

‹‹ምን ዋጋ አለው እንዲህ ረዣዥሞች ሆነን ቆመን አነጺዎች አያዩንም ማለት መቼስ ዘበት ነው፤ የአንተ ምኞት መቼስ ትንሽ ከበድ ያለ ሆነ›› አለ ሦስተኛው ዛፍ በጥሞና ሁለት ወዳጆቹን ንግግር ከሰማ በኋላ።

ሁለተኛው ዛፍ ይህንን ተከትሎ ምኞ ቱን እንዲህ ሲል ተናገረ፦ ‹‹የእኔ ምኞት እንኳን አለመቆረጥ አይደለም፤ መቆረጥስን ልቆረጥ ነገር ግን የሚወስዱኝ አናጺዎች ወደ ቤተ መንግሥቱ የእንጨት ባለሙ ያዎች ወስደው እንዲሰሙኝ እፈልጋለሁ፤ ከዚያም የንጉሡ ባለሙያዎች ለንጉሡ ዙፋን አድርገው ይሠሩኛል። የንጉሥ ዙፋን መሆን ማለት ደግሞ ትልቅ ክብር ነው።›› ሲል ለወ ዳጆቹ የልቡን አጫወታቸው።

‹‹የእኛን ምኞት ሰማህ እስቲ የአንተን ደግሞ አጫውተን ለወደፊቱ ምን መሆን ትፈልጋለህ?›› አሉት ወደ ሦስተኛው ዛፍ እያተኮሩ።

‹‹እኔ እንኳን የንጉሥ መሳፈሪያ መር ከብ ሆኜ መሠራት ነው የምፈልገው፤ ንጉሥና መኳንንቱ በእኔ እንዲሳፈሩ....›› እያለ ምኞ ቱን መዘርዘር ሲጀምር ከሩቅ የአናጺዎች ድምጽ ተሰማ። ዛፎቹ ተርበተበቱ በተለይም ከዛፎች ሁሉ ከፍ ብሎ መታየትና የዕዕዋት ንጉሥ የመባል ምኞት የነበረው ዛፍ በፍር ሃት መወዛወዝ ጀመረ። አናጺዎቹ ተልከው የመጡ ይመስል ሦስቱን ዛፎች ለይተው ቆርጠው ጭነው ይዘዋቸው ሔዱ።

‹የዕዕዋት ንጉሥ› ለመሆን ይመኝ የነ በረውን አንደኛውን ዛፍ ይዞ የሔደው አናጺ በዕቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ አስቀመ ጠው። ምኞቱ እንደማይሳካ ገና ሲቆረጥ የታወቀ ቢሆንም በግምጃ ቤት ውስጥ ይቆ ለፍብኛል ብሎ አስቦ ስለማያውቅ ይህ ዛፍ ኀዘኑ ጸናበት ፈጣሪውንም አማረረ።

ሁለተኛውን ዛፍ የወሰደው አናጺ ደግሞ ዛፉን ወስዶ ሳጥን አድርጎ ሠራው። ዙፋን ለመሆን የነበረውን ይህንን ዛፍ የክብቶች ምግብ የሚቀመጥበት ሳጥን ሆነ። ምንም እንኳን የንጉሥ ዙፋን ባይሆን ሳጥን ሆኖም ደህና ሳጥን ቢሆን አይጠላም ነበር። የተመ ኘውን ምኞት ተቃራኒ ሲገጥመውና በቤተ መንግሥት እውላሁ ሲል ለዐይን በሚከፋ ለአፍንጫ በሚከረፋ በረት ውስጥ መገኘቱ የዚህን ዛፍ ልብ ሰበረው። ስለዚህም የምኞ ቱን ተገላቢጦሽ የሰጠውን ፈጣሪውን በተስፋ መቁረጥ አማረረ።

ሦስተኛውን ዛፍ የቆረጠው አናጺ ደግሞ ዛፉ እንደተመኘው ለመርከብ ሠሪዎች ወስዶ ሰጠው። የንጉሥ መርከብ ለመሆን የጓጓው ይህ ዛፍ በደስታ ተውጦ ሠሪዎቹ መርከብ አድርገው እስኪሠሩት መጠባበቅ ጀመረ። ይሁንና መርከብ ሠሪዎቹ የዛፉን ምኞት አል ተረዱ ኖሮ የአሳ ማጥመጃ ታንኳ አድርገው ሠሩት። ስለዚህም ለጥቂት ጊዜ ተስፋው ለምልሞ እንዳልነበር ሁሉም ገም እንደመዝገን ሆነበት። የንጉሥ መርከብ ሆኖ ሊሰገኘው የተመኘውን ባሕር ታንኳ ሆኖ ያለ ዕረፍት ከአሳ አጥማጆች ጋር ሊመላለስ ተገደደ። እርሱም እንደ ጓደኞቹ ‹‹ምነው አምላኬ ምን በደልኩህ?›› አለ።

በአውግስጦስ ቄሣር ዓለሙ ሁሉ እንዲ ጻፍ ትእዛዝ በወጠበት ጊዜ እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ። ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ ፀንሳ ከነበረች ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ። በዚያም ሳሉ የመለጃዋ ወራት ደረሰ የበኵር ልጅዋ ንም ወለደች በመጠቅለያም ጠቀለለችው በእንግ ዶች ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግር ግም አስተኛችው። (ሉቃ.፪፥፫-፯) በተኛበት ግርግም ውስጥ የተወለደው ሕፃን የተኛው ጭድ በተሞላ ሳጥን ውስጥ ነበር። ይህ ሳጥን የንጉሥ ዙፋን መሆን ይመኝ የነበረውና ሳጥን ሆኖ የተሠራው ዛፍ ነበረ።

‹‹በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ፦ ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው። ሕዝቡንም ትተው በታንኳ እንዲያው ወሰዱት ሌሎች ታንኳዎችም ከእ ርሱ ጋር ነበሩ። ብርቱ ዐውሎ ነፋስም ተነሣና ውኃ በታንኳይቱ ይገባ ነበር። እርሱም በስ ተኛላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፤ አንቅ ተውም፦ መምህር ሆይ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት። ነቅቶም ነፋሱን ገሰጸው ባሕሩንም፦ - ዝም በል ፀጥ በል አለው። ነፋሱም ተወ ታላቅ ፀጥታም ሆነ። እንዲህ የምትፈሩ ስለ ምን ነው? እንዴትስ እምነት የላችሁም? አላቸው። እጅግም ፈሩና፦ እንግዲህ ነፋስም ባሕርም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? ተባ ባሉ።›› (ማር.፬፥፴፭-፵፩) ይህ ተአምር የተፈጸመበት ታንኳ የንጉሥ መሳፈሪያ ለመሆን ይመኝ የነበረውና ታንኳ ሆኖ የተ ሠራው ዛፍ ነበር።

ከፋሲካ በኋላ በዕለተ ዓርብ ከአንድ አናጺ ግምጃ ቤት የወጣን እንጨት አመሳ ቅለው ፍርድ አንድለው ጌታን ሊሰቅሉበት አበጃጁት። ከዚህም በኋላ ይህንን መስቀል ጌታ ተሸክሞ እስከ ቀራንዮ ወጣ መስቀሉም በክብረ ደመ፡ በመታጠበ ‹ንጉሠ ዕዕዋት› የዕዕዋት ንጉሥ (መስተብቁዕ ዘመስቀል) ከዛፎች ሁሉም ከፍ ከፍ ያለ ሆነ፤ ሰዎች ሁሉ እርሱን ሲያ ዩም ዛፍ ሆኖ እንደተመኘው እግዚአብሔ ርንና ገነትን ያስባሉ።

የእነዚህ ሦስት ዛፎች ምኞትና ተስፋ የተበላሸና ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ ነበር። ይሁ ንና ተስፋቸው ሲጠፋ እግዚአብሔር ሥራ ውን ጀመረ።‹‹የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ያለቀ የተቁረጠ ነገርን በምድር ሁሉ መካ ከል ይፈጽማል›› ኢሳ. ፲፥፳፫ ዛፎቹ ተስፋ አድርገዋቸው ከነበሩት አናጺዎች ይልቅ ተስፋ ያላደረጉት እግዚአብሔር ምኞታ ቸውን ባላሰቡት መንገድ ፈጸመላቸው። ሁለቱ ዛፎች የምድራዊ ንጉሥ ዙፋንና መርከብ መሆን ተመኝተው ነበር፤ የሰማይና የምድር ንጉሥ ሆኑ።

‹‹ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው።›› ሰቆ. ፫፳፮

የዚህ ታሪክ መነሻ አሳብ ‹The Three Trees› በሚል ርእስ Bishoys orthodox blog. በተሰኘ መካነ ድር ከተጻፈ ምሳሌ የተገኘ ነው። በሰውኛ ዘይቤ ዛፎች እንደሚናገሩ ተደርጎ የሚተረክ ምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስም ይገኛል። (መሳ. ፱፥፫፤ ፪ዘ. ፰፥፲፫) ይህ ታሪክ በአስተማሪ ምሳሌነቱ እንጂ ስለ መስቀል ታሪካዊ አመጣጥ የሚጠቀስ አይደለም።

ቅድስት ዕሌኒ



በኅሩይ ሰሜ

ቅድስት ዕሌኒ (Flavia Iulia Helena Augusta) የክርስቶስን መስቀል ማግኘቷ በታሪክ ይታወቃል። ነገር ግን ሙሉ ታሪክዋን የማወቅ ዕድል ጠባብ በመሆኑ ይህንኑ ለማወቅ የገጠመው ከስንት አንድ ነው። በመሆኑም ቅድስት ዕሌኒ መቼ ተወለደች? አስተዳደግዋ ምን ይመስላል? መስቀሉን ለመፈለግ ምን አነሣሣት? መስቀሉን ካገኘች በኋላስ ቀሪው ዘመንዋን እንዴት አሳለፈች? የሚሉት ጥያቄዎች በብዙ ሰዎች ጭንቅላት ዉስጥ ይጉላላል። ታዲያ ስለ መስቀሉ መገኘት ብሎም ስለ ቅድስት ዕሌኒ ታሪክ ሊነሣ እነዚህንም ጥያቄዎች አብሮ መመለስ ተገቢ ነዉና እኛም በዚህ ጽሑፍ እንደሚከተለዉ አቅርበነዋል።

ሌኒ እ.ኤ.አ በ250 አካባቢ ድሪፓኑም (ቅዱስ ቆስጠንጢኖስ ከነገሠ በኋላ ሔለናፓሊስ ብሎ ይህችኑ ከተማ ለክብርዋ ሰይሞላታል) በሚባል ከተማ ተወልዳለች። አውራጃውም ቢታንያ ይባላል። ወላጆችዋም ሀብት አልነበራቸውም። ስለዚህም ቅድስት ዕሌኒ ኑሮዋን ለማሸነፍ ሥራን ሳትንቅ በቤተ መንግሥት ውስጥ ወተት በማለብና ያንንም ወደ ተለያዩ ተዋጽዖ በመቀየር ብዙ አገልግላለች።

ድርሳነ መስቀል የተባለው መጽሐፍ ግን ዕሌኒን ተርቢኖስ ለተባለ ነጋዴ ሚስት ያደርጋታል። ተርቢኖስ ከዕሌኒ ተጣልቶ በሳጥን ውስጥ ከከተታት በኋላ ወደ ባሕር ቢጥላት ትልቅ ዓሣ ውጧት ቁስጥንጥንያ አደረሳት። ቁንስጣ በዚያም ሀገር ባሕር ዳርቻ አሸከሮቹን ዓሣ ሲያስ ጠምድ ይሄንን ዓሣ አጥምደው አመጡለት። እርሱም ቢያሳርደው ውስጡ ሳጥን አገኘ። ያንንም ቢያስከፍት ከውስጡ እጅግ ያማረች ቅድስት ዕሌኒ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተጠብቃ ምንም ሳትሆን ወጣች በማለት ትውልዷን እስራኤላዊ ሀገሯንም በዚያ ያደርጋታል።

በዚያን ዘመን በሮማ ቤተ መንግሥት ወስጥ እድገትንና ሥልጣንን የሚፈልጉ የጦር መኮንኖች እንዲሁ በቤተ መንግሥት ውስጥ ያገለግሉ ነበር። በዚያ ጣዖት አምልኮ በገነነበት ስፍራ ውስጥ ጥቂት ክርስቲያኖች ከቅዱስ ጴጥሮስና ከቅዱስ ጳውሎስ ጊዜ ጀምሮ በትጋት እግዚአብሔርን አገልግለዋል። ከቁሳር ቤተሰብ የሚወለደው ቅዱስ ቀለሜንጦስም ከቤተ መንግሥት ሕይወት ይልቅ ክርስትናን መርጦ የቅዱስ ጴጥሮስ ረድእና የሮም ክርስቲያኖች ጳጳስ ሆኖአል። እንዲሁ ከቁሳር ቤተሰብ የተወለዱ ብዙ ክርስቲያኖች ደግሞ የሮማን ቤተ መንግሥት ጣዖትንና ኃጢአትን በመጥላት ሰማዕትነትን መርጠዋል። በመጽሐፍ ቅዱስም ላይ «ከቁሳር ቤት የሆኑት ሰላምታ ያቀርቡላችኃል» የሚለው ሐዋርያዊ ቃል ይህንን ጉዳይ በቅጡ ይመሰክራል (ፊልጵ. ፬፥፳፪)።

ቅድስት ዕሌኒ እንደዚህ ላሉት ክርስቲያኖች ጥሩ ማሳያ ናት። በእንዲህ



ባለ አስቸጋሪና ከጨለማ ጋር የተባበረ ማኅበረሰብ ውስጥ እግዚአብሔርን ማምለክ እጅግ በመከራና በፈተና የተመላ ሕይወት ቢሆንም እንደ ዕሌኒ ያሉ ክርስቲያኖች ግን ኖረውታል። በመሆኑም ከእንደዚህ ዓይነት በኃጢያት የተሞላ ሕይወት ውስጥ ታዛቢ ሆኖ ከመኖር ይልቅ ሌሎች ምእመናን በግበበ ምድር (በመሬት ውስጥ) በመኖር ዘመናቸውን በሰማዕትነት ጨርሰዋል። ቅድስት ዕሌኒም በኃጢአተኞች መሐል እየኖረች የድርጊ ታቸው ተባባሪ ሳትሆን በቅድስና ተወስና ኖራለች። ከዘመናት በኃላም በአውሪሊያን ቄሳር ስር ከነበሩት ከፍተኛ መኮንኖች መካከል ቁንስጣ (Constantius Chlorus) ከተባለው ጋር ትዳር መስርታለች። በኢትዮጵያ ስንክሳርላይ እንደተጻፈውቁንስጣ ቀጥተኛና የርኅራኄ ሥራ ያለው ሰው ነበር (ስንክሳር መጋቢት ፭፰)። ቅድስት ዕሌኒምክርሱ ጋር ፳፪ የትዳር ዓመቶችን አሳልፋለች። በትዳራቸውም እጅግ በጎ ፍሬ የሆነውን ቅዱስ ቆስጠንጢኖስን ወልደዋል።

ቅድስት ዕሌኒ ልጅዋን ቅዱስ ቆስጠንጢኖስን ስለ ክርስትና ሰፊ ትምህርት እያስተማረች አሳደገችው። በዚህ መሃል አባቱ ቁንስጣ ወደ ቄሳር ማዕርግ ከፍ እንዲል የቄሳር መክስሚያንን ሴት ልጅ አገባ። በጣዖት አምላኪዎቹ ሮማውያን ዘንድ አንዳች የሥነ ምግባርና የሕግ ሥርዐት ባለመኖሩ ጥቅምን ተከትሎ ያሻውን ማድረግ የተለመደ ነበር። ስለዚህም ቅድስት ዕሌኒን ፈታት። እርሰዋም ልጅዋን ቆስጠንጢኖስን ከማሳደግ ውጪ ድጋሚ አላገባችም። በመሆኑም ቆስጠንጢኖስን በክርስትና ትምህርትና በተለያዩ ሙያዎች ዕውቀት ያለው በፈረሰኛነቱ የተመሰገነ መስፍን አድርጋ አሳደገችው። ምንጊዜም ለክርስቲያኖች እንዲራራና ርኅራኄ እንዲያደርግ ትመክረው ነበር። በዚህም ድንቅ ሥራዋ በልቡናው የዘራችው መልከም ዘር መቶ ፍሬ ያፈራላት በመሆንዋ እንደ ሐዋርያት ስትመሰገን ትኖራለች።

ለወደፊት በአባቱ ቤተ መንግሥት የሚገጥመውን የሰይጣን ፈተና በድል ተወጥቶ ለጣዖታት ሳይንበረከክ ወደ ተቀደሰው እምነትና እውነተኛውን አምላክ ወደ ማወቅ እንዲደርስ ያስተማረችው ትምህርት በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እንዲጠቀምበትና ሌሎችንም እንዲ ጠቅም አስችሎታል። ከጥቂት ዘመን በኃላ ቆስጠንጢኖስ ወደ አባቱ በመሔድ ከእርሱ ሥር በከፍተኛ የመኮንን ማዕ ረግ ማገልገል ጀመረ። የቁንስጣም ግዛት የአሁኑ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ግዛት ነበር። በዚያምበግብረ ገብነቱና በእውነተኛፍርዱ በወታደሮች ሁሉ ከፍተኛ መከበርን አተረፈ።

ቅድስት ዕሌኒ ግን በዘመንዋ ሁሉ እንዳደረገችው በክርስትና እምነትዋ ጸንታ በትህትናና በጸሎት ተግታ ኖረች። ይህ የጸሎት ሕይወቷ ለልጅዋ ተርፎ በአደጋ ውስጥ መጠበቅ በኃላም ስለ እው ነተኛው አምላክ ዕውቀትን እንዲያገኝ አድ ርጓል። ቆስጠንጢኖስ እንግሊዝ አገር ዘምቶ ሳለ አባቱ በመሞቱ ወዲያው ወታደሮቹ በአባቱ ዙፋን ላይ አስቀምጠውታል። ይህም ከሆነ በኃላ ወደ እናቱ አስልኮ ለንግሥት በሚገባ ክብር በአጠገቡ በማስቀመጥ ሕዝቡ ሁሉ እንዲያከብሩአት አድርጓል። የእናቱንም ትምህርትና ማሳሰቢያ አስታውሶ በግዛቱ ለነበሩ ክርስቲያኖች ነጻነትን ዕወጀ በሮም ለማገኘው ለመክስሚያኖስ ተመ ሳላይ ዕዋጅ እንዲያውጅ ደብዳቤ ጻፈለት።

መክስሚያኖስ ግን ጣዖት አምላኪ ነው በዚህ አልተደሰተም። ይልቁንም ላይ ላዩን በፍራቻ ተውጦ ትእዛዙን ያከበረ እያስመሰለ በክርስቲያኖችና በሌላውም ሕዝብ ላይ መከራ አጸናባ ቸው። ይህንንም ጉዳይ ለቆስጠንጢኖስ የሮም ባላባቶች ደብዳቤ በመጻፍ እንዲ ያድናቸው ስለተማጸኑት። ቆስጠንጢኖስም ከሀዲውን መክስሚያኖስን ለማስወገድ ዘመቻ ላይ እንዳለ በቀትር /፮ ሰዓት ላይ/ ሰማይ ላይ ብሩህ መስቀል ተመ ለከተ። ከእርሱም ጋር የነበሩት ሁሉ አዩት። ከሰማዩም በዮሩኒ ቋንቋ « በዚህ ምልክት ድል ታደርጋለህ » የሚል ተጽፎ በት ነበር። ይህንንም መስቀል በወ ታደሩ ጦር፤ ልብሱና ጋሻው ላይ እን ዲሆን አዘዘ። እርሱም እራሱ በዘውዱ ላይ መስቀል አሠርቶ አደረገ። በመስ ቀሉም ኃይል ታላቅ ድልን ተጎናጸፈ።

ከዚህ በኃላ ቆስጠንጢኖስ እናቱን አስጠርቶ የገጠመውን ሁሉ ነገራት። ድል ያገኘበትንሰውንሁሉ የሚያድን መስ ቀሉም እንዴት ሊገኝ እንደሚችል መከራ። ቅድስት ዕሌኒም አስቀድማ ቆስ ጠንጢኖስ በክርስትና አምኖ ከተ ጠመቀ መስቀሉን ለማግኘትና በኢየሩ ሳሌም አብያተ ክርስቲያናትን

ለመገንባት ተስላ ነበር። ቅድስት ዕሌኒም መስቀሉን ለማግኘት ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ ለማድረግና ለመመርመር ወሰነች። ቅድስት ዕሌኒ ይህንን ጉዞ ለማድረግ ስትነሣ ዕድሜዋ ወደ ሰማንያ ዓመት ይጠጋ ነበር። የመስቀሉ ፍቅር ያበረታት ቅድስት ዕሌኒ ግን ይህንን ረጅምና አድከሚ ጉዞ በአንድ ዓመት ውስጥ በሚገባ ተጉዛ ኢየሩሳሌም ገባች። ልጅዋም ቆስጠንጢኖስ የሚያስፈልጋትን ያህል ገንዘብና አገልጋይ በስርዋ መድቦላት ነበርና ወዲያውኑ ስለ መስቀሉ ታጠያይቅ ጀመር። በኢየሩሳሌምም የሚገኘውን ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ መቃርስን መስቀሉ የሚገኝበትን መንገድ ያሳያት ዘንድ አማከረችው። ይህ ኤጲስ ቆጶስ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ሊጠቁሟት የሚችሉ አረጋውያንን ፈልጋ እንድታገኝ ያዛት ነበር/:ስንክሳር ዘግንቦት ፱/ በኢየሩሳሌም ከብዙ ጥረት በኃላ ይሁዳ የተሰኘን (በእኛ ምንጭ ኪራኮስ የሚባለውና ዳግመኛም አሚኖስ በመባል የሚታወቅን ሌላ አረጋዊን ይጠቅሳል) አረጋዊ አመጡላት እርሱንም መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ይነግራት ዘንድ አዘዘችው። ይህ አይሁዳዊ ግን ይህንን ለመናገር ፈቃደኛ አልሆነም። ሰለዚህም ያለ እህልና ውሃ ስድስት ቀን ታሰረ። በመጨረሻም ለመናገር ተስማምቶ አባቶቻችን መስቀሉ የተቀበረበት ኮረብታ ይህ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ ብሎ አንዱን ተራራ አመለከታት። ያ ቦታ ግን አሰቀድሞ ጎለጎታ የሚባለውና ጌታችን አምላካችን የተቀበረበት ሲሆን ያካባቢው ሕዝብ የቤቱን ጥራጊ እየጣለበት ተራራ አክሎ ነበር።

ከተራራው በየትኛው ክፍል እንደሚገኝ ቅድስት ዕሌኒ ለማወቅ ስለተቸገረች ጽኑ ሐሳብ ገባት። በዚህ ሐሳብ ተውጣ ስትተክዝ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል በራእይ ተገልጦ መስቀሉ ያለበትን ቦታ የዕጣን ጢስ እንደሚያመለክታት ነገራት (ስንክሳር ዘ ወርሃ መጋቢት፣ ዕለት ፬)። በዚህም ምስጋና ለእግዚአብሔር ካቀረበች በኃላ ደመራ ሠርታ ብዙ ዕጣን ብትጨምርበት ጢሱ ወደ ሰማይ ወጥቶ መስቀሉ ያለበት ቦታ ላይ ተተከለ። የውጭ ሀገር ምንጮች በቦታው ላይ ስትደርስ በመሬት መንቀጥቀጥና በዕጣን ሽታ አየሩ ተሞላ። በዚያም ቪነስ የተባለ የኮከብ አምልኮ ጣዖት ቤት ስለነበር ያንን እንዲፈርስ ከአደረገች በኃላ ወዲያውኑ ማስቆፈር ጀመረች በማለት የዘገቡት ታሪክ አለ።

ያም ሆነ ይህ ቅድስት ዕሌኒ ዕጣኑ ከሰገደበት ቦታ ላይ እንዲቆፈር አዘዘች። ቦታውም ስድስት ወር ከተቆፈረ በኃላ በመጋቢት ፲ ቀን ፤፫፻፵፯ ዓ.ም ሦስት መስቀሎች አገኘች። የጌታችን መስቀል የትኛው እንደሆነ ለማወቅም የሞተ ሰው አምጥተው በሙቱ ላይ ሁለቱን መስቀሎች አድርገው ምንም ለውጥ እንደሌለ ተመለከተች። ለሦስተኛ ጊዜ በሙቱ ላይ ያሳረፉበት መስቀል ሙቱ አፈፍ ብሎ እንዲነሣ አደረገው። ይህም ብቻ ሳይሆን በሌሎች የውጭ ምንጮች እንደተጻፈው ለመሞት የቀረበች ሴት አምጥተው በጌታችን መስቀል በመፈወስዋ ታወቀ ሲሉ ሌሎች ደግሞ ጲላጦስ የጻፈው ጽሑፍ በላዩ ላይ ነበርና በዚያ ታወቀ የሚል ታሪክ አስፍረዋል።

የመስቀሉ መገኘት ታላቅ ደስታን ፈጠረ። አስቀድሞም ከልጅዋ ከቅዱስ ቆስጠንጢኖስ ጋር መስቀሉ ከተገኘ በደመራ እሳትን በማቀጣጠል ምልክት ልታደርግለት ተነጋግረው ስለ ነበር ባላገሩ ሁሉ ደመራን እየደመረ መስቀሉ የመገኘቱን ብስራት በብርሃን ገለጸ። በዚህም ቁስጥንጥንያ ድረስ ደመራዎቹ እያበሩ ስለታየ ታላቅ ደስታ ተደረገ። በመሆኑም «መስቀል አበራ» በማለት መዘመርና ደመራን መደመር ከዚህ ተያይዞ የመጣ ባህል ነው ተብሎ ይነገራል።

ይሁዳ (ወይም ኪራኮስ) የሚባለው አይሁዳዊም በበኩሉ ባየው ሁሉ አምኖ ክርስትናን ተቀብሏል ። ከዚያም በኃላ ገዳማትን የተቸነከረባቸውን አምስት ቅንዋቶች (ሳዶር፤ አላዶር፤ ዳናት፤ አደራና ሮዳስ የሚባሉ) እንደወርቅ እያበሩ አብረው ከዕፀ መስቀል ጋር ተገኝተዋል። እነዚያንም አንዱን በቆስጠንጢኖስ ዘውድ ላይ አስገጠመችው። ሌላኛውንም ለፈረሱ ልጉዋም አስደረገችለት። አንዱን ችንካር ደግሞ አድሪያቲክ ውቅያኖስ ላይ ጣሉት በማለት የውጭ ጸሐፊዎች የጻፉት ይገኛል። ስለቀሩት ሁለት ችንካሮች ግን የተዘገበ ታሪክ የለም። የመስቀሉንም ትንሽ ቁራጭ ለበረከት ለቅዱስ ቆስጠንጢኖስ ወሰደችለት።

በእየሩሳሌም እያለች በደብረ ዘይት ላይ በሚገኘው ጌቴሴማኒ፣ መስቀሉ በተገኘበት በጎልጎታ እንዲሁም በቤተ ልሄም ማለትም ጌታችን በተወለደበት ላይ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጻለች። በተመሳሳይ መልኩ በጠቅላላ ሰማንያ የሚያህሉ አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ አምላክን እንዳገለገለች ይታወቃል። ቅዱስ ቆስጠንጢኖስም በእየሩሳሌም ላይ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን እንዲገነባና በዚያም የጌታችን መስቀል እንዲቀመጥ አዘዘ። ከዚያም በኃላ መስቀሉን በጥንቃቄ በካህናት እንዲጠበቅ እያደረገች "ወደ ሀገርዋ ጉዞ ጀመረች። በተለያዩ ሀገሮች እያቋረጠች ብዙ ድውዮችንና ሙቶችን በዕፀ መስቀሉ አዳነች። በጉዞዋ ወቅትም ወደ ቆጵሮስ ደሴት በመሃሉድ በዚያ ለጥቂት ጊዜ ሰንብታለች። በዚያም ደሴት ላይ ብዙ ክርስቲያናዊ ቅርሶች እንደሰጠች ይነገራል። ዕፀ መስቀሉ በቁስጥንጥንያ በደረሰ ጊዜ ሰባ ነገሥታት መጥተው ስገዱለት። ቅድስት ዕሌኒም ዕፀ መስቀሉን በስንዝር፣ በስንዝር እየቆራረጠች አካፈለቻቸው። ለራሷም አንድ ስንዝር አስቀረች። ትልቁንም ግማደ መስቀል ቤተ ክርስቲያን አሠርታ አስቀመጠችው። ይህም በቆስጠንጢኖስ ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም ወስዶ በጎልጎታ ባሳነጸው ቤተ ክርስቲያን በክብር አስቀመጠው። በፊት እንደሆነው ሁሉ ፋርሶች ቤተ ክርስቲያኑን አቃጥለው ወደ ሀገራቸው ወስደው መሬት ውስጥ ቀበሩት። ከእነርሱም እጅ ንጉሥ ሕርቃል ኢየሩሳሌም አስመለሰው። ከዚያም ወደ ግብጽ ተሻገረ።

በመጨረሻም ቁስጥንጥንያ በደረሰች ጊዜ በታላቅ ሰልፍና አጀብ ሕዝቡ ተቀብሏታል። በቀረው ዘመንዋም ለነዳያን ምጽዋትን በመስጠት፣ እስረኞችን እንዲፈቱ በማድረግ፣ ልብሰ መንግሥትዋን በማውለቅና የሀገሩን ባህል መሠረት ያደረገ ልብስ እየለበሰች ከምእመኑ እኩል ግማደ መስቀሉ ባለበት ቤተ ክርስቲያን በመጸለይና በማስቀደስ በትህትና አሳልፋለች። በመሠረቱ ሞት ለሰብአዊ ፍጡር ሁሉ አይቀርምና ቅድስት ዕሌኒም ከዚህ ዓለም ድካም በታላቅ የቅድስና ሕይወት ውስጥ ሆና ዐርፋለች። በረከቷ በሁላችን ላይ ይደርብን አሜን።

ህር ዕንቁ ባሕርይ ቤተ ክርስቲያን ወጣቱን መጠቀም ብትችል ብዙ እንደ ምታተርፍ አበክረው ይገልጻሉ። ‹‹ጌታችን ለምን ሐዋርያትን፣ አርድእትንና ቅዱሳት አንስትን መረጠ? በአምላክነቱ ሁሉን ማድረግ መቻሉ አይበቃውም ነበር? ስለዚህ ሊቃውንትም ወጣቱን ማቅረብ ይገባቸዋል። ወጣቱ ማዕበል ነውና እናስተካክለው መንገዱን እናቅናው ማለት ጥሩ ነው። ወጣቱን መጥላትና ማሸሽ ግን ስኅተት ነው። ወጣት ሳይሆን ያለፈ የለም። ወጣቱ የቤተ ክርስቲያን የደም ሥር ነው። ወጣቱ ቆመ ማለት የቤተ ክርስቲያን የደም ሥር ዝውውር ቆመ ማለት ነው።›› ብለዋል። በማደራጃ መምሪያው ባለባቸው ሐላፊነት የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶችን የሚያቀርቡ በርካታ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችን እንዳዩና ሰንበት ትምህርት ቤቶችን የሚረግጡ፣ ወጣቶችን አለአግባብ በመክሰስ ለእስር እስከ መዳረግ ድረስ የሚነሡ ጥቂት አባቶችም እንደገጠመአቸው አል ሸሸጉም። ‹‹በነጻነት ያደጉትንና አሳባቸው እንዳይገደብ የሚፈልጉትን ወጣቶች ቀርበው ካወያዩአቸውና አሳባቸውን ከተረዱላቸው ብዙ ማሠራት የሚችሉባቸው መሆናቸውን መረዳት ይገባል›› ሲሉም ተሞክሮአቸውን አካፍለውናል።

ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችን ለምን ለበዓላት ብቻ?

በዚህ የመስቀል በዓል ላይ የሚሳተፉት በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች በበዓሉ ላይ የሚያሳዩት ጎብረት ‹‹እነሆ ያማረ እነሆ የተወደደ ነው።›› ይሁንና ሰንበት ትምህርት ቤቶች ተባብረው ሊሠሩት የሚችሉት ትልቅ ሥራ በትርዒት ማቅረብ ብቻ መሆኑና ሰንበት ትምህርት ቤቶች በቤተ ክርስቲያን ያላቸው ክብረ በዓላዊ ሚና (Ceremonial role) መሆኑ ብዙዎችን የሚያስቆጭ ነው።

‹‹ሰንበት ተማሪዎች እንደ ቁጢማ በበዓል ብቻ የምንወጣ መሆናችን እጅግ የሚያሳዝን ነው።›› ይላል የምዕራብ ክፍለ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ጎብረት ፀሐፊ የሆነው ወጣት አንተነህ አወቀ። አያይዘውም ‹‹ሰንበት ትምህርት ቤት በተለያየ መ.ያ የተማረ ብዙ የሰው ኃይል ያለበት የቤተ ክርስቲያኒቱ ክፍል ነው። ብዙ ነገሮች በሰንበት ተማሪው መሠራት ይችላሉ። ከቤተ ክርስቲያኒቱ ውክልና ወስደው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ጥብቅና የቆሙትን የደብረ ገሊላ አማኑኤል እግዚአብሔር ምስሌነ ሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሙሉ የኤሌክትሪክ ዝርጋታ ሥራ የሠሩትን የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ገጻም ሰንበት ተማሪዎች ለዚህ ምሳሌዎች ናቸው።›› ብሏል። የደቡብ ክፍለ ከተማ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ጎብረት ሰብሳቢ ወጣት ሳሙኤል እሸቱም ‹‹በማደራጃ መምሪያው በተሰጠን ዕድል በመጠቀም ጎብረቱን ከክፍለ ከተማ ደረጃ ወደ አዲስ አበባ ደረጃ ለማሳደግ በእንቅስቃሴ ላይ ነን።›› ብሏል። ይህ ዕውን ከሆነም በአዳራሽ የተወሰነውና በበዓላት ብቻ ጎልቶ የሚታየው የአብዛኞቹ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሚና ከፍ ወዳለ ደረጃ ሊደርስ ይችላል።

‹‹ሥልጣንን ወደታች በማውረድ አብዛኞቹ ጉዳዮች ወደ ክፍለ ከተማዎች አውርደናል። በአብነት ትምህርት ላይ፣ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ያለውን ሥርዓተ ትምህርት ባዘጋጀነው አንድ መጽሐፍ ውጥ እንዲሆን በማድረግ ላይ ፣ ለጎኑ መጽ ገሞጁ የሆነውን የመዘመር መጽሐፍ አሳትሞ በማሠራጨት ላይ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ሐላፊነቱን እንዲረከቡ አድርገናል። በሰንበት ትምህርት ቤቶች ላይ ይታይ የነበረው አለመተዋወቅ ተቀርፎ ጎብረቱ በመጠናከር ላይ ይገኛል።›› በማለት መምህር ዕንቁ ባሕርይ ያክላሉ። እኛም ሰንበት ትምህርት ቤቶቻችንን እንደ ስማቸው ‹ትምህርት ቤቶች› ሆነውልን መንፈሳዊ ትምህርት በሰፊው የሚሰጥባቸው እንዲሆኑና የመስቀል በዓልን ከማክበር በላይ ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት የሚያደርጉት ጥረት ከግብ እንዲደርስ ዳሰሳችንን ፈጸምን።


ን ኃይለ ኒስቂሊዝ ይናት ሀይና

(በመስቀሉ ኃይል ይጠብቀን)

(አገውኛ)

በዓለ መስቀል በቆሎ ተማሪዎች





በጌታቸው በቀለ

በየዓመቱ የመስቀል በዓል/ደመራ/ ለቆሎ ተማሪዎች ልዩ ትዝታ አለው። በዓሉንም ከመስቀል ይልቅ‹‹ተስ እነነ›› በማለት ይጠሩታል። «ተስእነነ መጣ፣ የተስእነነ ዕለት እንገናኝ›› የቆሎ ተማሪዎች ቀጠሮ ናት። ዕለቱንም በታላቅ ናፍቆትና ዝግጅት ነው የሚጠብቁአት።

የቆሎ ተማሪዎች

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዕውቀትን ሸተው ወደ እርስዋ የመጡትን ሰዎች በሚገባ ቀርጻ በዕውቀት አበልጽጋ፣ በምግባር ኮትኩታ፣ በሀገር ፍቅር ገንብታ ከፊደል እስከ ትርጓሜ መጻሕፍት ድረስ ትምህርት የምትሰጥባቸው መካናተ ጉባኤያቲ /የትምህርት ቦታዎች/ የአብነት ትምህርት ቤቶች ይባላሉ። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ደቀመዛሙርት ደግሞ የአብነት ተማሪዎች ወይም በተለምዶ ‹‹የቆሎ ተማሪዎች›› ይባላሉ።

ደቀመዛሙርቱ ከትምህርት ሰዓታቸው ውጪ በየትምህርት ቤታቸው አጥቢያ የሚገኙትን መንደሮች ተከፋፍለው ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› እያሉ ይለምናሉ። ምእመናንም ቅድስት ቤተክርስቲያን በትምህርት ለምታ ሳድጋቸው ተማሪዎች ቀድደው በማልበስ፣ ቆርሰው በማጉረስ በነበረው የነጻ ትምህርት አገልግሎት ተባባሪዎች ነበሩ። ገበሬው ጥራጥሬውን ከሜዳ፣ እመቤቲቱ ብስለን ከጓዳ ይዘክሩአቸዋል። ከጉባኤና ከአገልግሎት ውሎ በኋላ የምሳ ወይም የእራት ሰዓት ሲደርስ ሁለት ወይም ከዚያም በላይ ሆነው በቀለሱት ጎጆ ውስጥ ሆነው ጥሬውን ቆልተው፣ ብስለን አሰናድተው በሰሌን ወይም በአጎዛ አቅርበው ይመገቡታል። በዚህም የተነሣ የቆሎ ተማሪዎች የሚለው ስያሜ ተሰጣቸው።

የቆሎ ተማሪዎች ጥበብን ለማፍራት ዕውቀትን ለመገ ብየት የትውልድ ሀገራቸውን ትተው ጎራ ዞረው፣ወንዝ ተሻግረው የሞቀ የደመቀ ሳይለብሱ፣የላመ የጣመ ሳይጎርሱ ክውሻ ተከላክለው ቁራሽ እንጀራ ለምነው የተለያዩ ፈተ ናዎችን ተቋቁመው የቤተክርስቲያንን ትምህርት በመዝለቅ የነገዋ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት፣ካህናት፣ዲያቆናት የሚሆኑ ደቀመዛሙርት ናቸው።

ተማሪዎቹ የተስእነነ ዕለት በጉባኤ የተማሩትን ትምህርት ይዘው፣ ‹‹መስቀል ኃይላችን ነው፣ኃይላችን መስቀል ነው፣ የሚያዐናን መስቀል ነው፣መስቀል ቤዛችን ነው... ››እያሉ በየምእመኑ ቤት በመሔድ የመስቀሉን መገኘት ያበሰ ራሉ፣ መዝሙርም ይዘምራሉ። ከቆሎ ተማሪዎች ‹‹ተስእነነ›› ሳይል ያለፈ አይገኝም። እርስ በእርስም ሲገናኙም ‹‹ተስእነነ›› ብለሃል ተባብለው ያሳለፉትን ትዝታቸውን የሚያወጉ ጥቂት አይደሉም።

የደመራ በዓል አከባበር

የቆሎ ተማሪዎቹ ‹‹ተስእነነ››ን ማክበር የሚጀምሩት የደ መራ ዕለት ነው። ደመራ የክርስትና ሃይማኖት ወደ ሀገራ ችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ሲከበር መኖሩን አበው ይናገ ራሉ። ደመራ በየዓመቱ መስከረም ፲፮ ቀን የሚከበር በዓል ነው። የደመራ ዕለት ሕዝበ ክርስቲያኑ ከየቤቱ ችቦውን፣ እንጨቱን እያመጣ ይደምራል። ካህናቱም እጅግ በተዋበና ባማረ ልብሰ ተክህኖ ተሸልመው ቀሳውስትና ዲያቆናት፣ ድርብና ካባ ላንቃ የለበሱ መዘምራን በሕዝቡ መካከል በማሸብሸብ ይዘምራሉ። አድባራትም በየተራቸው አንዱ ከሌላው አብልጦ የበዓሉን አከባበር በጋለ ድምቀት ለማ ሳየት በሚያደርጉት መንፈሳዊ ውድድር ዝግጅት አድርገው ስለሚጠባበቁ፤ በዚህ ዕለት በካህናቱ ላይ የሚታየው ጥንግ ድርብ፣ ኩታና ነጭ ልብስ፣ የዝማሬው ጣዕምና የንባብ ስልት፣ የትርጉሙ ምስጢር፣ የሽብሸባው ትርዒት የተመ ልካችን መንፈስ በተመስጦ የሚማርክ ነው። ለውጭ ሀገር ኅብኚዎችም ሃይማኖታችንን እንደ ዕንቁ አብርቶ የሚያ ሳይ ከመሆኑም በላይ፣ ቤተክርስቲያናችን የሥልጣኔና የባህል ምንጭ መሆኗን በጉልህ የሚያስረዳ ነው። ካህናቱም በቅዱስ ያሬድ የተደረሰውን ዋዜማ ‹‹ዘበንቲሃ ለቤተክርስቲያን›› ቆመው ሲጨርሱ ሥርዐተ ቅዳሴው /እንዘ ነአኩቶ ተደርሶ/ ወንጌል ከተነበበ በኋላ ስለ ዕለቱ በዓል ትምህርት ይሰጣል ። ጸሎቱ እንዳበቃ በበዓሉ የተገኙት ፓትርያርክ ወይም ሊቀ ጳጳስ ለሕዝቡ ቡራኬ ይሰጣሉ። በዓሉን

የሚያከብሩት በገጠር ከሆነ ሥነ ሥርዐቱ እንደተጠናቀቀ በዕለቱ ከተገኙት አባቶች መካከል ይለኩሱታል። በከተማ ከሆነ ግን የተገኙት ፓትርያርክ ወይም ሊቃነ ጳጳሳት፣ በካህናት፣ በመዘምራን፣ በአበው፣ በምእመናንና ምእመናት እንደታጀቡ ደመራውን አንድ ጊዜ ወይም ሦስት ጊዜ ዙረው ከምዕራብ አቅጣጫ ሲደርሱ ችቦውን በእሳት አያይዘው ይለኩሳሉ። በበዓሉ ላይ የማዘጋጃ ቤቱ ሹም / ሓላፊ/ ከተገኘ ለእርሱ ይሰጡታል፣ እርሱም ተቀብሎ ደመራውን ይለኩሳል። ስለዚህ በየዓመቱ የመስቀልን በዓል ስና ክብር ደመራ የምናደርገውና ችቦ የምናቀጣጥለው እሌኒን አብነት አድርገን ነው።

ዕሌኒን ሠራዊቷ የመስቀሉን መገኘት በየሀገሩ ለመግለጥ ችቦ በማብራት ይኸው፣ ይኸው፣ ያው፣ ያው (ኢዮሃ፣ ኢዮሃ) መስቀሉ ተገኘ፣ መስቀሉ አበራ እያሉ እየዘመሩ ዜናውን እንዳስተላለፉ ሁሉ፣ ካህናቱ፣ የቆሎ ተማሪዎች ክቡር መስቀሉ የተገኘበትን ሃይማኖታዊ ታሪክ ለማስታወስ ችቦ እያበሩ ‹‹መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሥርገወ ሰማየ እምኩሉሰ ፀሐየ አርአየ፣መስቀል አበራ እንደ ከዋክብትም ሰማይን አስጌጠ እንደ ፀሐይ አሳየ›› እያሉ እንደ ቅዱስ ያሬድ በዝማሬ፣ በዕልልታና በሆታ ደመራውን እየዞሩ በዓሉን ያከብራሉ። ሕዝቡም ‹‹ኢዮሃ አበባዬ፣መስከረም ጠባዬ›› እያሉ በደመራው ዙሪያ ተሰባስበው መስቀልን እንደ ሙሽራ በአበባ፣ በደመራ፣ በልዩ ልዩ ገጸ በረከት ይቀበሉታል። የቤተክርስቲያኑ ሥርዐት ካበቃ ደመራውም ተቃጥሎ አመድ ከሆነ በኋላ የበዓሉ ፍጻሜ ይሆናል። ደመራው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ፣ ሕዝቡ አመዱንና ትርኳሹን እያነሣ ለበረከት ይወስዳል። ከዚያም ሕዝቡ ወደየቤቱ በመሔድ በየደጁ ችቦውን እያበራ ደስታውን ሲገልጥ ያመሻል።

የደመራ በዓል አከባበር በቆሎ ተማሪዎች

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ለዓለም‹‹ሂዱና አስተምሩ››ሲል ለሐዋርያት እንዳዘዛቸው ሁሉ፣ የቆሎ ተማሪዎችም የደመራው ሥርዐት እንደተጠ ናቀቀ ተመራርጠው አምመው፣ ጠምጥመው ከበሮና ጸናጽል፣ መቋሚያና መስቀል ይዘው ከምሽቱ አንድ ሰዓት ጀምረው በየመንደሩ በሕዝበ ክርስቲያኑ ቤት በመሔድ ‹‹ተስእነነ ዘወንጌል ቃለ ኀቡረ ተመርኩዘነ መስቀል፣ የወንጌልን ቃል ተጫምተን በአንድነት መስቀሉን ተመርኩዘነ መጣን›› እያሉ ነገረ መስቀሉን ይሰብካሉ «እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስ እንሰብካለን » እንዲል /1ኛቆሮ.፩÷፲፫/።

የክርስቶስ መስቀል ልዩ ልዩ ተአምራትን አደረገ፣ ዕውር አበራ፣ ጎባጣ አቀና፣ ሙት አነሣ፣ ደንቆሮዎች መስማትን፣ ድዳዎች መናገርን አንካሶች መሔድን አገኙ፣ በማለት የመስቀሉን አዳኝነት እየመሰከሩ በዓሉን በድምቀት ያከብራሉ። መዝሙርም ይዘምራሉ ‹‹ጽጌ ገነት ደብረ መድኃኒት ሰላማዊት መዓዛ አፉሃ ከመኮል፣ወጼና አልባሲሃ፣ ከመጼና ስሒን...›› በማለት እየዘመሩ፣ እያሸበሸቡ፣ ግጥም እየደረደሩ የእንኳን አደረሳችሁ ዜና ያበስራሉ። የቤቱ ባለቤቶች ምእመናንም በደስታ ተቀብለው የተማሪ ዎቹንና የካህና ቱን ወረብ በማዳመጥ፣ በጣዕመ ዜማው በመመሰጥና ከመደ ሰታቸው የተነሣ የአቅማቸውን ስጦታ ያበረክታሉ።

ስጦታውም የተለያየ ሲሆን ቀደም ባለው ጊዜ አሞሌ ጨው፣ ጠገራ ብር ሲሰጥ የቆየ ሲሆን፣ከዚያም በኋላ እንደየ ሁኔታው ሴቶቹ ጋቢና ኩታ፣ ወንዶቹ ደግሞ ካባና ሻሽ እንዲሁም የፍየል ሙክት፣ወይፈንና በሬ ሳይቀር የሚሰጡ እንደነበር አባቶች ይናገራሉ። ሀብት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች ግን በዕለቱ ከሚሰጡት ስጦታ ሌላ ቀን ቀጥረው ሰንጋ አርደው፣ ጠላ ጠምቀው፣ ጠጅ ጥለው ግብዣ አዘጋጅተው ‹‹ተስእነነ›› በማለት በቤታቸው የመጡትን ተማሪዎችና ካህናት ይጋብዙ እንደነበርም አባቶች ያስረዳሉ።

ተማሪዎቹ ‹‹ተስእነነ›› የሚሉት መስቀልን አስቀድመው ክርስቶስን እየሰበኩ ከበሮና ጸናጽል ይዘው እየወረቡ ወደ ምእመናኑ ቤት በመሔድ ነው። ተማሪዎቹ በሚዘምሩበት አካባቢ የአንዱን ሰው ቤት አልፈው ሲሔዱ ‹‹እኔ ቤት ለምን ሳትመጡ ቀራችሁ››ብለው የሚቀየሙ ምእመናን አሉ። እንደውም በየዓመቱ ተማሪዎች እኔ ቤት‹‹ተስእነነ››ሊሉ ይመጣሉ ብለው ተዘጋጅተው የሚጠብቁ ምእመናን አሉ። ምእመናኑም ለተማሪዎቹ ያላቸውን ከመስጠት ወደ ኋላ አይሉም።

ምክንያቱም፡-



፩. መስቀል ከቤታቸው ድረስ በመም ጣቱና ቤታቸው በመስቀል በመባረኩ ነው። ዓለም በኃጢአት ምክንያት የተረገመ ነበር፣ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ለተረገመው ዓለም በረከትን አጎናጽፎ ታል። ስለዚህ መስቀል በክርስቶስ ለሚያ ምኑ ሁሉ በረከት ነውና።

፪. ከቤታቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ስም እየጠሩ በማመስገናቸው ነው። ‹‹አቤቱ ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ የተመሰገነ፣ ምስጋናህ በሰማዮች ላይ ከፍ ከፍ ብሏልና። ...አቤቱ ጌታችን ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ የተመሰገነ ነው››እንዲል/መዝ.፰÷፩-፱/።

፫. በቤታቸው መዝሙር በመዘመሩና በጣዕመ ዜማው ልባቸው ስለሚመሰጥ ነው። መዝሙር የባሕርይ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ነውና‹‹በምስጋና ቃል እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑት መላእክት እንሁን›› እንዲል /አትናቴ ዎስ ቁ.፱፯ ገጽ፩፻፲፫/።

፬. ተማሪዎቹን ለመርዳት በጎ ፈቃድ ስላላቸው ነው። መስቀል ይዘው ስመ እግዚአብሔርን እየጠሩ ለመጡ ተማ ሪዎች ይቅርና በደቀመዛሙርቱ ስም እንኳ ለመጡ በጎ ማድረግ በረከት ያሰጣል። ‹‹እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀ በል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፣ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል››እንዲል/ማቴ.፲÷፵፩/።

ምእመናን የእግዚአብሔር ቃል በቤታቸው በመነገሩና መዝሙር በመ ዘመሩ ረድኤተ እግዚአብሔር በቤታችን ያድራል ብለው ፍጹም ተስፋ ስለሚ ያደርጉ፣ በእምነታቸው መጠን አዝመ ራቸው፣ ቤታቸው፣ ከብቶቻቸውና ልጆ ቻቸው ይባረካሉ። ቤታቸውም የበረከት ቤት ይሆናል።

ተማሪዎቹም የአቀዱአቸውን መን ደሮች ሁሉ አዳርሰው ካበቁ በኋላ በስጦታ ያገኙትን ገንዘብ ባንድ ላይ ይሰባስባሉ። እህሉን ፣ጥጡን፣ ከብ ቱንና የመሳሰለውንም ሁሉ ሸጠው መጽሐፍ ለሚጽፉም ብራና ይገዙበታል።

የተረፋቸውንም ገንዘብ እኩል ተካፍለው ልብሳ ቸውን ይለብሳሉ፣ ለችግራቸው ያውሉታል። ዛሬም እንደ ጥንቱ አይጉላ እንጂ አልፎ አልፎ ይደረጋል።

እኛም በየዓመቱ የምናከብረው ይኸ የመስቀል በዓል፣ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከባርነት ወደ ነጻነት የተሸጋገርንበትን በዓል ነው። ስለዚህ ከጥንት ተያይዞ በመጣው መሠረት አዲሱ ትውልድም የመስቀልን /ደመራን/ በዓል ዛሬም እንደ ጥንቱ ያክብራል። ‹‹መስቀል ኃይላችን፣ ጽንአታችን፣ ቤዛችንና መድኃኒተ ነፍሳችን ነው›› በማለት ልዩ ልዩ የነገረ መስ ቀሉን ታሪክ የሚያበስሩ ጥቅሶችን በመያዝ ሕፃናትም ሆኑ አረጋውያን ደስታቸውን በዕልልታና በሆታ ይገልጻሉ። ቅዱስ መስቀል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ቤዛ የተሰዋበት ክቡር ደሙ የነጠበበት፣ ጠላት ዲያብሎስ ድል የሆነበት ሰላምና ዕርቅ የታወጀበት ስለሆነ እናከብ ረዋለን፣ እንሰግድለታለን፣ እንሳለመዋለን።

የቆሎ ተማሪዎችም የደመራው ሥርዐት እንደተጠናቀቀ ተመራርጠው አምመው፣ ጠምጥመው ከበሮና ጸናጽል፣ መቋሚያና መስቀል ይዘው ‹‹ተስእነነ ዘወንጌል ቃለ ኅቡረ ተመርኩዘነ መስቀል፣ የወንጌልን ቃል ተጫምተን በአንድነት መስቀሉን ተመርኩዘን መጣን›› እያለ ነገረ መስቀሉን ይሰብካሉ

ካህናትና ምእመናን በጎነ ረት ሆነው ጌታችን መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኃይል የፈጸመ ውን ድንቅ ተአምር በማው ሳት ‹‹በልደቱ ፍስሐ፣ በጥም ቀቱ ንስሐ፣ በመስቀሉ ኢዮሃ›› እያሉ በዓሉን በተድላና በደስታ ያከብራሉ። ሕዝቡም የክብረ በዓሉን ሥነ ሥርዐት በዐይኑ አይቶ፣ ታሪኩን በጆ ሮው ሰምቶ በመረዳቱ እምነ ቱን ለማጠንከር ያስችለዋል። ይህም በዓል በየትኛውም ዓለም የሌለ ልዩ ሃይማኖታዊ በዓል ነው። እንደ ቅዱስ ያሬድ‹‹መስቀል መልዕልተ ኩሉ ነገር ያድኅነነ እምዐር፣መስቀል ከጠላት ያድነን ዘንድ ከሁሉ ነገር በላይ ነው›› እያልን እየዘመርን በመስቀሉ ስለ እኛ ኃጢአት ተላልፎ የሞተልንን እስከ መስቀል ሞት ድረስ ያፈቀረንን የክርስቶስን ፍቅር ልናስታውስ ያስፈልጋል። ‹‹ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ዋልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው›› እንዲል /ኤፌ.፪÷፲፮/።

በዚህ ሁኔታ የጥንቱ ትምህርት ትውፊት ሲወርድ ሲዋረድ ከእኛ ደርሷል።አዲሱ ትውልድም ይህን ሀገርንና ቤተክርስቲያንን የሚያኮራ ለረጅም ጊዜ የበለጸገና የዳበረ የክርስትና በዓልና ሥርዐተ ትምህርት ጠብቆና ተንከባክቦ ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላላፍ ታሪካዊ ግዴታና ሓላፊነት አለበት።

ደመራ

እንደ መስከረም አሥራ ሰባት
እንደ መስቀሉ ዋዜማ
በሱስንዮስ አደባባይ
በዮዲት ጉዲት ማማ
በግራኝ አሕመድ መንደር
በዚያ በግፍ አውድማ
በሰማዕታቱ ሀገር
በኢሊባቡር በጅማ
የደመራው ሥነ ሥርዓት
ደምቆ ታየ ተሰማ
ቤተ ክርስቲያን እምነ
ቤተ ክርስቲያን እማማ
ከንዋየ ቅዱሳቷ
ከመጻሕፍቷ ጋር ቆማ
ደመራ ሆና ተለኮሰች
በአረማውያን በጨለማ
ልጆቿ ምእመናን
በፍቅሯ የሰከሩ
መስቀልን በመስቀል
በመከራ አከበሩ
ለደመራ እናታቸው
ችቦ ሆነው ተደመሩ!

(ለሰማዕታቱ መታሰቢያ)
ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

‹‹የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ነው፤ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።››
፩ቆሮ. ፩፥፲፰
የዚህ ቃል ትርጓሜ ዘርፈ ብዙ ነው።

፩. ‹የመስቀሉ ቃል› ሲል በመስቀል ላይ የተሰቀለው ወልደ እግዚአብሔር (በኩነት ስሙ ‹ቃል› /ዮሐ.፩፥፩/) ለሚጠፉት ሰው መሆኑና መሰቀሉ ሞኝነት ነው። ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር አብ ኃይል ነው። (ሉቃ.፩፥፴፫)

፪. ‹የመስቀሉ ቃል› ሲል ‹ነገረ መስቀሉ› (ስለ መስቀሉ የሚነገረው ቃል) ለሚጠፉት ሞኝነት ነው፤ ለእኛ ለምንድን ግን እግዚአብሔር ኃይሉን የገለጠበት ነው።

፫. ‹የመስቀሉ ቃል› ሲል ጌታችን በመስቀል ላይ ሳለ የተናገራቸው ሰባቱ ቃላት ለሚጠፉት የሞኝነት ንግግሮች ናቸው፤ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫዎች ናቸው። ሰባቱ አጽራሐተ መስቀል የሚባሉትም የሚከተሉት ናቸው።

- አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
  ማቴ.፳፯፥፵፮
- አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ።
  ሉቃ. ፳፫፥፵፮
- እነሆ ልጅሽ እነኂት እናትህ።
  ዮሐ. ፲፱፥፳፯
- ተጠማሁ
  ዮሐ.፲፱፥፳፰
- እውነት እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ።
  ሉቃ.፳፫፥፵፫
- አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።
  ሉቃ.፳4፥፴፬
- ተፈጸመ
  ዮሐ.፲፱፥፴፩

ቤተ ቅኔ

በመ/ር ደሴ ቀለብ

ይህ የአቡጊዳ ክፍለ ዐምድ የአብነት ትምህርቱ የፍልስፍና መሠረት ስለሆነው «ቅኔ» አመጣጥ፣ ዐይነት፣ ይዘት እና ዜማ ልክ የምንማማርበት ክፍል ነው። በክፍለ ዐምዱ የቅኔ ቆጠራ፣ ቀመር እና መንገድ ስልት ይቀርብበታል። በመሆኑም ምሳሌያት የሆኑ ቅኔያትን ለአብነት በማቅረብ፣ በመተርጎም እና በማራቀቅ አንባብያን ቅኔ እየቆጠሩ በመላክ ወይም በአጥቢ ያቸው ባሉ ሊቃውንት ዘንድ በመቅረብ የቅኔ ዕውቀትን እንዲረዱ እና እንዲችሉ ለማድረግ የቅኔ ትምህርትን በርቀት የማስተማር ዐላማ እና ዕውቀቱን የማስፋፋት ግብን ዐቅዶ የተነሣ ክፍለ ዐምድ ነው።

በዚህ ክፍለ ዐምድ የሚከተሉትን ዐበይት አርእስት መሠረት በማድረግ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንማማራለን።

፩. ጥንተ ቅኔ

ሀ. ቅኔ ምንድን ነው?
ለ. ቅኔ መቼ ተጀመረ? ማንስ ጀመረው? የትስ ተጀመረ?
ሐ. የቅኔ ዐይነቶች ምን ምን ናቸው?
መ. የቅኔ ጠባይዕ እና ይዘት በየዘመኑ ምን ይመስላል?
ሠ. የቅኔ አገልግሎት በቤተክርስቲያን
ረ. ታዋቂ የቅኔ መምህራን ሲዘከሩ

፪. ትምህርተ ቅኔ በሰም እና ወርቅ

ሀ. የቃላት አመሠራረት /የግስ አወራረድ
ለ. መደብ
ሐ. የዜማ ልክ /ምጣኔ
መ. ቅኔ ቆጠራ ከጉባኤ ቃና እስከ ዕጣነ ሞገር
ሠ. ቅኔን መቀኘት
ረ. ቅኔን ማስነገር
ሰ. ቅኔን መዝረፍ
ሸ. የቅኔ ጎዳና እና አገባብ

፫. ቅኔን ማስተማር

ቅኔ ምንድ ነው?

ቅኔ «ቀነየ» ገዛ ካለው የግእዝ ግስ የተገኘ ጥሬ ዘር ሲሆን መገዛት የሚለውን ቀጥተኛ ፍቺ ይይዛል። ቅኔ በውስጣዊ ትርጉሙ ለፈጣሪ መገዛትን መታዘዝን ምስጋና በማቅረብ መግለጽ ነው። ቅኔ ጎበረ ሐሳብን በተመስጦ በአርምሞ በተደሞ በአንክሮ የሚደርሱበት የሚያመነጩበት ሕዋሳተ አፍአን እና ሕዋሳተ ውስጥን ለሕሊና የሚያስገዛ ጎዳይ ነው።

ቅኔ ከልቡና የሚፈልቅ፣ የሚገጠም /በደንቡ መሠረት/፣ የሚደረስ፣ የሚነገር ስባሔ የአእምሮ ርቀት የሚታወቅበት በየጊዜው አዲስ የሆነ ዕውቀት ፍልስፍና ነው። የቅኔ ቋንጣ የለውም እንዲሉ። ዘርዘር ባለ መልኩ ሲገለጽ ቅኔ የሚከተሉትን ትርጉሞች ይይዛል።

- ☐ ቅኔ እምነት የሚገለጽበት ነው።
- ☐ ቅኔ ውዳሴ ለአምላክ የሚቀርብበት ነው።
- ☐ ቅኔ ባህል የሚጠበቅበት ነው።
- ☐ ቅኔ ተግሣፅ የሚቀርብበት ነው።
- ☐ ቅኔ ምክር የሚሰጥበት ነው።
- ☐ ቅኔ ለቅድስና ለማስተዋል መንገዱ ነው።
- ☐ ቅኔ ዜማ «የሚታረምበት» ነው /የንባቡ ወሰን የሚታወቅበት/
- ☐ ቅኔ ዜማው ግእዝ፣ ዕዝልና አራራይ ነው።
- ☐ ቅኔ አዳዲስ አስተሳሰቦች የሚገለጹበት ነው።
- ☐ በቅኔ ትምህርት ባህል የሌላውን ሰው ቅኔ አምጥቶ መቀኘት ብሂል ነው ያስብላል። ስለሆነም ይህን ማድረግ ጸያፍ ነው። ነገር ግን በሊቃውንቱ ቅኔ ዜማን ማጥናት ይቻላል። የቅኔን መንገድም መማር ይቻላል።
- ☐ ቅኔ አስተሳሰብ የሚለካበት ነው።
- ☐ አንድ ባለቅኔ ቅኔ ሲያደርግ መጻሒውን ስንኝ ወይም በተከታይ የሚያመጣቸውን ስንኞች ሌላው ቀድሞ ሲልበት «ነጠቃ» ይባላል። ቅኔ በስንኝ፣ በሐረግ እና በመደብ የተወሰነ ነው።
- ☐ ቅኔ መንፈሳዊ ልዕልና ወይም እድገት የሚታወቅበት ነው።
- ☐ ቅኔ ማኅበራዊ እና አስተዳደራዊ ሐሳቦች ይቀርበብታል።
- ☐ ቅኔ ታሪክ የሚጠናበት፣ የሚዘከርበት እና የሚጠበቅበት ነው።
- ☐ ቅኔ የፍልስፍናው ሰዎች ወይም የሞያው ባለቤቶች መጋቤ ምሥጢር የሚል ማዕርግ የሚያገኙበት የተከበረ ሞያ ነው።
- ☐ ቅኔ ስሜቶች /ኀዘን ወይም ደስታ/ የሚን ጸባረቁበት ነው።

- ቅኔ በቤተክርስቲያን የማመስገኛ ስያሜ አለው።
  ቅኔ ማኅሌት፣ቅኔ ደብተራ
- ቅኔ ትንቢት ይነገርበታል።
- ቅኔ ባለብዙ መንገድ ነው።

ቅኔ ለግእዝ ነፍሱ ነው እንዲሉ ከግእዝ ቋንቋ ዕሤቶች ወይም በረከቶች መካከል አንዱ ቅኔ ነው። ቅኔውንም ለማወቅ መሣሪያው ግእዝ ነው። ቅኔን መማር እንደሚገባ እና የግእዝን እና የግእዝ ቅኔን ግን ኹነት ሊቀ ሥዩማን አክሊሉ ገብረ ኪሮስ /በኋላ አፈሊቅ/ በሚከተለው «ጉት» ቅኔያቸው እንዲህ ይገልጹታል።

ግእዝ ዳቦ ሲፈተት፣
እንዳይቀርባችሁ በረከት
የቅዱስ ያሬድ ጠዲቅ ነውና እባካችሁ ቅመሱት።
ግእዝ መብራትን አብርተን
እንፈልግ የጠፋ ዕቃችንን።
በዕቃም ዕቃ የአባቶቻችን ጋሻ
ቅኔን መዝራት ነበር እንዳሻ።
ድንቁርና እንዲያጣ መድረሻ
ቅኔያቸው ነበርና የልቡናቸው መታሰቢያ
ግዙፍ ድንቁርናን ገፍቶ ለመጣል
እንዲኖራችሁ ወኔ
ለመመራመርም ደጎና አድርጎ እንዲሰጣችሁ መጥኔ
እሹሩሩ ማሙየ እያላችሁ እደግ ተመንደግ ለኔ
መልካም አድርጋችሁ አሳድጉት የያሬድን ሕፃን ቅኔ
/አዲስ ዘመን፣ መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፷፫ ዓ.ም/

በግእዝ እንማማር

አባ ገብረ ማርያም

ዑቁኬ ኢያስሕቱክሙ!
እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ!
ዘይብሉ ንሔድሳ ለቤተክርስቲያን
ቤተክርስቲያንን እናድሳታለን የሚሉት
እም አውሮጳ
ከአውሮፓ
በኢያእምሮ
ባለማወቅ
እስመ ይገብሩ ግብረ ሉተር/መናፍቅ/
የመናፍቁን የሉተር እና የተከታዮቹን
ሥራ ይሠራሉና
ይተርፉ እንበለ ሃይማኖት ወምግባር
እስመ ወፅአ ልቦሙ እም ቤተክርስቲያን
ያለ ሃይማኖት እና ምግባር ይቀራሉ ልባቸው
ከቤተክርስቲያን ወጥታልና
ወይመርሐሙ መንፈስ ዕኩይ
ክፉ መንፈስ ይመራቸዋል
መንፈሰ ዲያብሎስ /አቡሃ ለሐሰት/ ውእቱ
የሐሰት አባቷ የዲያብሎስ መንፈስ ነው
ኢየአምኑ በገድለ ቅዱሳን
ወበድርሳን እስመ አልቦሙ
ትምህርት ወቢፅ ሐሳውያን ውእቶሙ
በገድል/በቅዱሳን አያምኑም በድርሳንም።
ትምህርት የላቸውምና ሐሰተኛ ወንድሞችም ናቸው

አርድእተ ሰንበት /የሰንበት ተማሪዎች/

እለ መኑ?
እነማን?
እም አይቴ መጽኡ?
ከወዴት መጡ?
ለምንት ውእቱ ከመዝ ዘይብሉ?
እንደዚህ የሚሉ ለምንድን ነው?
እፎ?
እንዴት?
ምንት ውእቱ ፍጻሜሆሙ ለእሉ ወተላውያኒሁ
የእነዚህ መጨረሻቸው ምንድን ነው?

እወ ይከውኑ ዝርዋነ እስመ ተንሥኡ ላዕለ ቅዱሳን

አዎ ዝርዋን ይሆናሉ በቅዱሳን ላይ ተነሥተዋልና

ምንት ውእቱ ዝንቱ?
ይህ ምንድን ነው?
ምንት ውእቱ ትምህርቶሙ?
ትምህርታቸው ምንድን ነው?
አምላከ ቅዱሳን ይዕቀባ ለሀገሪትነ
ወለርስትነ ኢትዮጵያ ወለውሉዳ
የቅዱሳን አምላክ ሀገራችንን ይጠብቃት
ኢትዮጵያ ርስታችን እና ልጆቿንም።
በመስቀል ንወግአሙ ለኵሉሙ ፀርነ
ጠላቶቻችን ሁሉ በመስቀል እንወጋቸዋለን።

አሜን።

መስቀሉን በመሰለቂያ ሥፍራ!?

ሕይወት ዘፍሬ ቅዱሳን

እንደምን ከረማችሁ? እኔ መንገደኛው ዝዞን ሳልጊታ ይኸው! መስከረም እየሄደ መስከረም ይተካል። ለምን እንደሆነ ባይገባኝም መስከረም በመጣ ቁጥር ከመደሰቴ በተጨማሪ ካለፈው የበለጠ በየአብያተ ክርስቲያናቱና ገዳማቱ የመጓዝ ወኔዬ ይጨምራል።

እንዳልኳችሁ መስከረም ወር በሌላም ምክንያት በጣም የምደሰትበት ወር ነው። ታላቁን የመስቀል በዓል እናከብርበታለንና!! በቃ! ለመስቀል በዓል ልዩ ስፍራ አለኝ።

«መንገደኛው በመስቀል በዓል ታላቅ ደስታን የሚያደርገው የመስቀልን በዓል ምንነት በሚገባ ጠንቅቆ አውቆ ይሆን እያላችሁ የምታሙኝ እንዳይመስለኝ ስለመስቀል ክቡርነት የማውቀውን ልንገራችሁ። ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ውሎ እኛ ለሠራነው ኃጢአት ካሣ እንደሆነን እያሰብን እንደምንሰግድለት እንዲሁም በልብሳችን፣በሰውነታችን፣ በቤታችን እንደምናደርገው እና በአብዙኃኑን እንደምንባረክበት ጠንቅቄ አውቃለሁ። በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥም በዚያ በመስቀል ምልክት ሃይማኖታቸውን በመመስከራቸው ምክንያት ሰማዕትነትን የተቀበሉ ክርስቲያኖች እጅግ በርካቶች አይደሉምን? ዛሬ ታዲያ በዝዞ እንደታዘብኩት በርካቶች ትእምርተ መስቀልን በአንገታቸው በማሰር ሃይማኖታቸውን ሲመሰክሩ አንዳንዶች ደግሞ ከአንገታቸው በማወቅም ባለማወቅም በመበጠስ ወይም ባለማሰር ከዚህ የምስክርነት ሕይወት ቦዝነው አይቻለሁ። አንዳንዴም አንገታቸው ላይ መስቀል ማድረግ እንዳላዋቂነት የሚያስቆጥራቸው መስሏቸው ማተባቸውን የሚበጥሱም እንዳሉ ሰምቻለሁ። በእውነት እነዚህን ዓይነት ሰዎች ክርስቲያኖች ሆነው በጉዞዬ ባገኛቸው ክርስትና ክርስቶስ «ምስክሮቼ ሁኑ» ብሎ ተልእኮ የሰጠበት ሃይማኖት በመሆኑ ማተባቸውን ሲበጥሱ ከዚህ የሰማዕትነት ሕይወት እየራቁ መሆኑን ልነግራቸው ተዘጋጅቻለሁ።

ከዚህ ሌላም ለመስቀላችን ካለኝ ታላቅ አክብሮትና ፍቅር የተነሣ አንዳንዶች መስቀልን ባልተገባ ሁኔታ ሲጠቀሙበት አይቼ በዝምታ አላልፋቸውም። «ከክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ....» የሚለውን የሐዋርያውን ቃል ጠቁሜ፣ ስለመስቀል ክብር መስክሬ ዘክሬ አልፋለሁ።

አዲሱ ትውልዱ ለመስቀል ያለውን ክብርና ቦታ በጥናት አስደግፌ ባላውቅም አብዛኛው የመስቀልን ክብርና የድኃኒት ምክንያትነት ባለማስተዋል



የዘፋኞች ፋሽን፣ ቀለበትና የጆሮ ጌጥ አልፎም በእግር ላይ ለሚጠለቅ ጌጥ /አልቦ/ ማዳመቂያነት መጠቀምን እንደ ትክክለኛነት ይቆጥረዋል። ጌጥ ማድረጉ ባልከፋኝ ያንን የምንጠቀምበት ግን ለሥጋዊ ዓላማ ከሆነ ከሃይማኖታዊ ዓላማው እጅግ በሚቃረን መንገድ የመስቀልን ምልክት ይዘነዋል ማለት ነው።

ታዲያ ቅዱሳን፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት በመስቀል ኃይል ስንት ተኣምራትን እንደሠሩና ለታመመት ፈውስን እንደሰጡበት፣ ኃይለ አጋንንትን እንዳ ራቁበት አልገባቸው ይሆን፣ እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ።

አንድ ቀን ያጋጠመኝን ልንገራችሁማ ነገሩ እንዲህ ነው። ታክሲ ውስጥ ነው። ከተሳፈርነው ሰዎች መካከል አንድ ወጣት አለባበሱ ከጥቁር አሜሪካውያን ዘፋኞች "ኮፒ ፔስት" የተደረገ ነው። ከአንገቱ እስከ ጉልበት የደረሰው መስቀል ተሳፋሪዎችን ሳይሆን በእግር የሚጓዙ መንገደኞችን ቀልብ እየሳበ ወደ ታክሲው ያስፈጥጣል። በአጠቃላይ በቀለም የተዥጎረጎረ ሱሪው ከመቀመጫው ሊወድቅ ሰከንድ የቀረው ይመስላል። በዚህ ሁሉ ሁኔታው ይመስላል ከሁላችንም እሱን በማየት ጥቂት ደቂቃ ባክኗል።

በሦስተኛው የታክሲው መቀመጫ ላይ የነበሩት አዛውንት ግን ሁኔታውን በዝምታ ማለፍ የፈለጉ እንዳልሆኑ ስለተረዳሁ ካሁን.... አሁን ምን ሊናገሩ ነው እያልኩ መንገደኛው በአንክሮ እያስተዋልኳቸው ነበር።

እሳቸውም እንዲህ አሉ «ልጄ እንደው አትታዘበኝና ባህልህንም ማንነትህንም እርሳው ነገር ግን፣ ጉልበትህ ድረስ የለቀከው መስቀል ምንነቱንና ክብሩን ታውቀዋለህ?» ወጣቱ በዝምታ አለፋቸው። የአዛውንቱ ጥያቄ ግን ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበበት ወጣት በስጨት ባለ መልኩ «What's up man? ምን ችግር አለው? አቦ አይጨቅጭቁና ሩዙርዬ» በማለት መለሰ።

የወጣቱ ምላሽ እንኳን አዛውንቱን መንገደኛውንም አበገነኝ። ግን ከመናገር ዝምታን መርጬ የሚሆነውን መከታተል መርጫለሁ።

አዛውንቱ ንዴት በተቀላቀለበት አንደበት «ልጄ መስቀል እኮ የሕይወታችን መዳኛ ነው፣ የጌታችን ደም የፈሰሰበት፣ የክርስትናችን መለያ አርማችን ጭምር ነው፣ ልጄ ካህናት ያለምክንያት መሰለህ መስቀል የሚያሳልሙን፣ ትርጉም አለው ልጄ! ታላቅነቱን፣ ክብሩንና የድኃኒታችን ምክንያት ስለሆነ ነው ልጄ.....» ወጣቱ ድንገት አቋርጧቸው «ምን ችግር አለው ሩዙር? እንኳን እኔ በዓለም ስመጥር የሆኑ ቱጃክን የመሰሉ ዘፋኞችም አድርገውታል።

«ይገርማል! ደግሞ የመስቀልን አያያዝ ከዘፋኞች እንማር? የመስቀሉን ክብርና ምስጢር ከሰማዕታት እንማራለን እንጂ እንዴት የመስቀል ጠላት ከሆነ ግብር ውስጥ ካልወጡ ወገኖች እንማራለን?...በል ንገረኝ?» አዛውንቱ በጥያቄ አፋጠጡት ከዚህ በኋላ ወጣቱ በፍጥነት ከታክሲው ወረደ።

መንገደኛው በአዛውንቱና በወጣቱ ክርክር ተመስጬ ፍፃሜውን ለማየት ብጓጓም በዘመንኛው ወጣት ሽሽት ተገድቤ እኔም መውረጃዬ ደርሶ ከታክሲው ወረድኩ። ነገር ግን ሐሳቤ ካዛውንቱ ተቆራኝቶ ታክሲ ውስጥ የሰማሁት ያዋቂና ያላዋቂ ክርክር በግለሰቦች የተወሰነ የደቂቃዎች ችግር ሳይቃጠል በቅጠል የሚባል መሆኑን ተረዳሁ።

ማተባችን፣ ክርስትናችን፣ ክብራችን፣ ድኃኒታችን የሆነው መስቀል አሁን አሁን ለተለያዩ ጌጣጌጦችና ማዳመቂያዎች ሆኖ መመልከት እየተለመደ በመጣበት ሁኔታ ስለመስቀል ክብርና ኃይል ከማስተማር ይልቅ ዝምታን የመረጡት የቤተ ክርስቲያን አካላት ምነው ከእኚህ አዛውንት በተማሩ የሚል መንፈሳዊ ቅናት እየኮረኮረኝ ዝዞን ቀጥያለሁ።

«የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና። የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ....።» /፩ኛ ቆሮ. ፩፥፲፰/ እንዲል ቅዱስ መጽሐፍ ጥበብና ማስተዋል መስላቸው ያለምንም መሠረታዊ አንድምታ መስቀልን በጆሮዋቸው? በእጃቸው፣ በእግራቸውና በፀጉራቸው ባጠቃላይ ባልተገባ ቦታ የሚያውሉት ሰዎች ታሰቡኝና «አቤቱ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ማለትን መረጥኩ። ሕገ እግዚአብሔር ተከብሮ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሞ የማየት ናፋቂ ነኝና ራሳቸውን ሳይክዱ መስቀልን ለተሸከሙት ድኃኒትን ተመኘሁ። ጊዜው መሸ ዝዞ የማይገደብ መንገደኛ አሁንም እየተጓዘ ነው ...ቸር እንሰንብት።